# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ሐምሌ / ነሐሴ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.




“ኅሡ ሰላመ ወዴግንዋ፤
ሰላምን ሿት ፥ ተከተሏትም”
/መዝ.33፥14/


www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ይታሰብበት

በብዛት በሀገራችን ጾመ ነቢያት አልፎ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉት ወራት እና ከጾመ ዐቢይ /ትንሣኤ/ በኋላ በሚገኙት ወራት የሰርግ ሥነ ሥርዓት ይበዛል:: ከዚሁ ጋር በተያያዙ ሁለት ነገሮች እየተለመዱ መጥ ተዋል:: እነዚህም በተክሊል ወይም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚጋቡ ሙሽሮች በቤተ ክርስቲያን ቆርበው /ሥጋ ወደሙን/ ተቀብለው ከወጡ በኋላ በዳንስና በጭፈራ ይውላሉ:: ይህ ነገር ለበረከትና ለድህነት የታሰበው ለመቅሰፍት እንዳይሆንብን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የማታዝዘው አጉል ልማድ ነውና ይታሰብበት::

*እስክንድር መሥፍን*
*/አዲስ አበባ/*

## «የሞት ራዕይ÷ የሞት ሕልም÷ የሞት ትንቢት»

መናፍቃን በእምነት ያልተጉ ህብታሞችን የሚያስፈራሩበት የዘመኑ ስብከት ነው:: ሥራ ማስኬጃ እያጠረ ሲሄድ የማይታሰብ ነገር የለም:: በዋነኛነት የተፈለገው የህብታሙ ነፍስ ይሆን? ወደ ህብታሙ ጠጋ ይሉና «ስለ አንተ ሕልም አይቻለሁ፣ ራእይ አይቻለሁ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ብለህ ንገረው:- "ትሞታለህ እንጂ አትድንም" ብሎኛል» የሚል ቃል ለከተማው ህብታሞች እየተነገረ ነው:: ለአብነትም የሞቱ ህብታሞች ስም እየተጠቀሰ «እገሌኮ የእግዚአብሔርን ጥሪ አልሰማ ስላለ ተቀሰፈ» እያሉ ያስፈራሯቸዋል:: «ህብትህ ሁሉ ሊበተን ነው» ይሏቸዋል:: ትሞታለህ... ትሞታለህ... ትሞታለህ ብቻ ነው ስብከታቸው:: የሞት ራዕይ÷ የሞት ሕልም÷ የሞት ትንቢት! አንባቢ ሆይ፤ አንተስ ምን ሰምተሃል? ምን ታዝበሃል?

*ኃይሌ ይልቃል*
*አዲስ አበባ*

## ምርጫና ቤተ ክርስቲያን

በ1997 ዓ.ም በአገራችን የተካሄደውን ሦስተኛው ዙር አገር ዓቀፍ ምርጫ በተመለከተ ቤተ ክርስ ቲያናችን ቅድመ ምርጫና ድኅረ ምርጫ የመታዘብና የቅዝብቷን ዘገባ በተመለከተ በመገናኛ ብዙኃን መልእክት ተላልፏል:: በመልእክቱ እኔና ጓደኞቼ ቅር ብሎናል:: ምክንያቱም እኛ ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታችን እንጂ ስለ ዓላማዊ ፖለቲካ ምን አገባን:: በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: ስለዚህ በመታዘብም ይሁን በሌላ መልኩ በፖለቲካ ጣልቃ መግባት ከእምነታችን ጋር አይጻረርም ወይ?

*ተክሊት ኪዳኑ*
*ደብረ ዘይት መከላከያ*

## ቤተ መጻሕፍት በአብያተ ክርስቲያናት

በየአጥቢያችን በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የጥበብ /ዕውቀት/ና መረጃ የሚሰጡ የኅትመት ውጤቶች መገኘት ባለመቻላቸው ያገኘን ጉዳት እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ምእመናን በተለይም ደግሞ ወጣቶች ስለ ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነት፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጥልቀትና በስፋት የማንበብ ዕድል ሊፈጠርላቸው ይገባል:: ስለሆነም ይኸው ታውቆ በተቻለ መጠን አነስተኛም ቢሆን በየአጥቢያችን በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ መጻሕፍት መከፈት አለባቸው:: በምእመናን በኩል ደግሞ በየቤታችን ተመልካች /አንባቢ/ አጥተው አቧራ የለበሱ ጠቃሚ የኅትመት ውጤቶችን መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ መጽሐፍ፣ የሬድና የቪድዮ ካሴቶች እያመጣን ብናበረክት መልካም ነው::

*ተክለ ሥላሴ*
*ከቅድስት ሥላሴ*


## በሐመር መጽሔት እና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ያስተዋውቁ !!

### በመላው ዓለም በሚሠራጩት በእነዚህ ኅትመቶች:-

- ምርትዎን እና አገልግሎትዎን
- ሰርግዎን
- የእንኳን ደስ አለዎ መልእክትዎን
- ጉዞ፤ ጉባኤ
- የሐዘንና የደስታ መግለጫ እንዲሁም
- የሥራ ማስታወቂያ

**እና ሌሎች እርስዎ እንዲተዋወቅልዎ የሚሹትን በመረጡት መንገድ በተመጣጣኝ ዋጋ እናስተዋውቅልዎታለን ይኅብኙን !!**

**ስልክ 23-45-30/22-57-29/(09)64-27-28**

**E-mail MK_distribution@yahoo.com**

### የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com ይጻፉልን::

የእሳትና የመሬትንም አገልግሎት በማስተዋል ለተመለከተው ሰው፥ ዋጋ የማይገኝለትና ለሕይወት መሠረት መሆኑ ብዙም ትርጓሜ የማያስፈልገው እውነታ ነው:: ከእነዚህም መሠረታዊ ሀብቶች አንዱ ክረምት (ውኃ) ነው:: ክረምት ከሌለ ልምላሜ የለም:: ልምላሜ ከሌለ ፍሬ የለም:: ፍሬ ከሌለ ፍጥረት የለም:: ስለዚህ ከሀብት በላይ የሆነ ክረምትን የሰጠንን እግዚ አብሔርን ከማመስገን ጋር የተሰጠንን ሀብት በሚገባ መጠ ቀም ይገባናል::

## ከሰሞኑ በረከት

ይህ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የትሕትናና የመልካም አርአያ ባለቤት የሆነ በኋላም በቅዱስ ዮሐንስ አስተማሪነት በትምህርተ መለኮት ተኮትኩቶ ያደገና የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የሆነ ቅዱስ አግናጥዮስ አንጾኪያን በታላቅ ትምህርቱ ወንጌል አዳርሷት ነበር:: በትምህርቱ የተመለሱ በትምህርቱ ጣዕም ሲደሰቱና እግዚአብሔርን ለማገልገል ሲ ነሣሱ፤ ጣዖትን የሚያመልኩቱ ደግሞ ስሕተታቸውን ስለ ገለጠባቸው ተቆጡ::

## ትምህርተ ሃይማኖት

ሰው በደፋርነቱ የኃያሉን አምላክ ትእዛዝ ተላልፎ ትካዘ ዓ ለም ሲያስጨንቀው ሸክሙን የሚያቃልልበትና የሚያስወግድበት መንፈሳዊ ጥበብ ከቸሩ ፈጣሪ ተሰጥቶታል:: ይኸውም በጥቂት ድካመ ሥጋ ያልተወሰነ ጸጋ እግዚአብሔ ር የሚያገኝበት ሥርዓት ሱባዔ ነው:: ከጥንት እስከ ዛሬ አንድ ሰው በትካዜ ዓለም መንፈሱ ሲታወክ የነፍስና የሥጋ ጸጥታውን ለመመለስና ለማስከበር መጾምና መጸለይ ግድ ይሆንበታል:: በዚህ ጊዜ አመክሮ /ሱባዔ/ ይገባል::

## የጥያቄዎቻችሁ መልሶች

ከዘመነ ኦሪት ማለትም የጽሑፍ ሕግ በሙሴ አማካይነት ከመሰጠቱ በፊት በነበሩት አበው ዘመን መሐላ አልነበረም:: በአብርሃም ዘመን ብዙ ቃል ኪዳን ተደረገ፥ መሥዋዕት ተ ሠዋ፤ ሆኖም ግን መሐላ መማል አልነበረም:: ነገር ግን ክፋት እየበዛ፥ ነገ ሮች እየተደባለቁ፥አምልኮ ጣዖት እየተስፋፋ በአጠቃላይ ሰዎች ለመታመን ብቁ አልሆን እያሉ ሲመጡ ለነገራቸው አሳማኝ ዋስ ወይም ማስረጃ ይሆናቸው ዘንድ እግዚአብሔርን እንደ ምስክር መጥራት ጀመሩ::

## ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
ሪፖርተር - ዲ/ን ፋሲል አስረስ
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
- ጸዳሉ ሁንዴሳ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org

«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

ሐመር
፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፬
ሐምሌ/ነሐሴ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

# ይዘት

**የማኅበሩ መልእክት**
- እርስ በርሳችሁ ጨው ይኑራችሁ፤ ተስማሙ»...... ፪

**ደብዳቤዎች** ........................................ ፬
- ቅርሶቻችን፦ ይመለሱ? ወይስ ........................ ፭

**ከሰሞኑ በረከት**
- ክረምት ........................................ ፯

**ትምህርተ ሃይማኖት**
- ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ........................ ፱
- ቅዱስ አግናጢዎስ........................ ፲፪

**የጥያቄዎቻችሁ መልሶች**
- ሱባኤ........................................ ፲፭

**ኪነ ጥበብ**
- አባ ነዋል ........................................ ፲፱

**እናስተዋውቃችሁ**
- <ውዳሴ> ቅዱሳት መካናት........................ ፳
- አቡነ ፊልጶስ........................................ ፳፫
- ባሕረ ሐሳብ........................................ ፳፯

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
- መሐላ........................................ ፳፰
- ሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን?........................ ፴፩

**ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ**
- «ናሁ አነ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኅልቀተ...... ፴፫
- ቀደምቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዋፅዖ ዛሬም በዘመናዊ........................ ፴፯

**ወቅታዊ ጉዳዮች**
- ቀደምቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዋፅ........................ ፴፰

**ስዑጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**
- የግስ አርዕስት........................................ ፵

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡፡

**«ጼወ ርከቡ በበይናቲክሙ ፤ ወተሰነአው፤**
**እርስ በርሳችሁ ጨው ይኑራችሁ፤ ተስማሙ»**

/ማር. 9 ÷ 50/

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነፍሳቸውን ሕመም በወተት ቃሉ፣ የሥጋቸውንም ደዌ በልዩ ልዩ አምላካዊ ተአምራት እየፈወሰ ቅፍርናሆም በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን በአንድ ቤት ሰብስቦ ሳለ የመከራቸው ታላቅ ምክር ነው፤ ዓለም ይጣፍጥ ዘንድ በነሱ ነፍስ ውስጥ ጨው ሊኖር ይገባልና፡፡ እነርሱ ከጣፈጡ ዓለሙ ይጣፍጣል፤ እነርሱ ከተስማሙ ዓለሙ ይስማማል፡፡

ሰላም ለሰው ልጆች የተሟላ ሕይወት መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ነገር ደግሞ እርስ በርስ ከመስማማት ይመጣል፡፡ እርስ በርስ ለመስማማት ደግሞ የሰዎች ሕይወት በጨው በተመሰሉት ሰላምና ፍቅር ሊጣፍጥ ይገባል፡፡ የሰዎች ሕይወት በሰላምና ፍቅር ከጣፈጠ እግዚአብሔር ይደሰታል፡፡ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ማስደሰት ከቻለ የሰላም ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህ ከፈጣሪው የተቸረው ሰላም እንዳይናጋ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት መትጋት ይኖርበታል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም ተምሳሌት የሆነውን ጨውን መሠረት በማድረግ «በነፍሳችሁ ጨው ይኑርባችሁ» ሲል ያስተማረው ትምህርት ሰላም ሕይወታችንን የሚያጣፍጥ መንፈሳዊ ቅመም መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ ከምንም በላይ ሰላምን በቁርጥ ኅሊና መሻት ይኖርብናል፡፡

ሰላም ለአንድ ሀገር ሁሉን ዐቀፍ ደኅንነት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ሰላሙ የተናጋ ሕዝብ እርስ በርሱ አይተሳሰብም፡፡ የራሱን ደኅንነት ያስባል እንጂ የወንድሙ ደኅንነት አደጋ ላይ መውደቅ አያሳስበውም፡፡ የራሱን ገቢ መዳበር ያስባል እንጂ ለወንድሙ መራቆት ግድ የለውም፡፡ ለራሱ የጣመውን ይበላል÷ ያማረውን ይለብሳል እንጂ የወንድሙ መታረዝና በጠኔ መሞት ጉዳዩ አይደለም፡፡

ሰላም የራቀው ሕዝብ እግዚአብሔርን በአግባቡ አያመልክም፡፡ /ማቴ.22÷37-39፤ ማር.12÷28-31/፡፡ በመሆኑም ሰላም ለአንድ ሀገር ሕዝብ መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ዛሬ በምድራዊው መመዘኛ በሀብት በልጽገው ከእነርሱ አልፈው ለእኛ የሚያጉርሱን ሕዝቦች አለመታደል ሆኖ በሃይማኖት አላጠነከራቸውም እንጂ ሠርተው መበልጠግ የቻሉት ባገኙት ሰላም ነው፡፡

በዚህ መልእክታችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ዘር ልቡና ሁሉ ይዘልቅ ዘንድ በንግግርም በሥራም ያስተማረውን ሰላም በርእስነት ያነሣንበት ምክንያት የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ነው፡፡ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ መሰንበቻዋን ሰላሟ አደጋ ላይ ወድቆ፤ አልፎ አልፎም ተናግቶ አነሰም በዛ የደከመችባቸውንና ተስፋ የምታደርጋቸውን ልጆቿን አጥታለች፡፡ በተናጋው ሰላም የተነሣም በወጣትነታቸው ተግተው በመሥራት ራሳቸውንም ሆነ ሀገራቸውን እንዲያሳድጉ የሚጠበቁ ዜጐች የሕይወት፣ የአካልና የሞራል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

በዚህ አሰቃቂ ክስተትም እንኳን በተግባር ሆኖ በዐይናችን ልናየው፣ በኅሊናችን ልናስበው የማንፈልገው ነገር ሆኗል፡፡ በአሳዛኝ ሁኔታ ያረፉትን ወገኖቻችንን ነፍስ በጻድቃን አባቶቻችን ነፍሳት አጠገብ እንዲያኖርልን፣ አብረው ሊኖሩ ሲገባ ባልጠበቁት መንገድ ልጆቻቸውን፣ ወንድም እኅቶቻቸውን፣ እናት አባቶቻቸውን ያጡ ወገኖቻችንን መጽናናቱን ይሰጥልን ዘንድ አብዝተን እንጸልያለን፡፡ ነገር ግን ይህንን እያደረግን ዛሬ ከሚታዩት አንዳንድ እስጥ አገባዎች ነገ ሊመጣ የሚችለውን ስንገምት በእጅጉ እንሸማቀቃለን፡፡ በትላንቱ በእጅጉ ብንደነግጥና ብናዝንም ነገ የባሰ እንዳይመጣ በእጅጉ እንሰጋለን፡፡ በመሆኑም በእኛው ኃጢአት አልፎ አልፎ የተከሰቱ ተግሣጾች ቢኖሩም ቅድስት ሀገራችንን ለመጠበቅ የማይታክት አምላክ ዛሬም የእናቱን ዓሥራት ሀገር እንዲጠብቅ ወደ አምላክ እየጮኽን የሀገራችን ሰላም እንዲረጋገጥ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የሚችሉትን ያህል ጥረት እንዲያደርጉ እናሳስባለን፡፡

ትናንት በተፈጠረው ሁኔታ የምናዝን፥ ነገም ሊመጣ በሚችለው የምንጨነቅ ዜጐች እንደ መሆናችን «ይህ ሁሉ ችግር እንዴትና ለምን ተከሰተ?» ብለን እንድንጠይቅ ተገደናል፡፡

በመሠረቱ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆኑ በርካታ ነጥቦችን ለማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ጥያቄያችንን ራሳችን ለመመለስ በእኛ እምነት የሚከተሉት ምክንያቶች ዋና ዋና የሚባሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዛሬ ለደረስንበት አለመረጋጋትና ጭንቀት መንሥኤ የሆነው እንቀስቃሴዎች ሁሉ በእውነት መሠረትነት አለመከናወናቸው ነው፡፡ የዚህ መሠረታዊ ነገር መጥፋት ደግሞ ሌሎች ከመሠረታዊነት የሚተካከሉ ለግጭትና ላለመረጋጋት መንገድ የሚከፍቱ መንሥኤዎች ሲፈጥሩ እንመለከታለን፡፡

ሁሉም አካላት የሚናገሯቸውም ሆኑ የሚተገብሯቸው ነገሮች በሙሉ በእውነት ላይ ብቻ የተመሠረቱ ቢሆኑ ኖሮ ፍቅር እንጂ አምባጓሮ አይኖርም ነበር፡፡ ለሕዝቡ ሲባል ልዩነቶችን አጥብቦ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለጋራ ብሔራዊ ዓላማ መንቀሳቀስ እንጂ በየዕለቱ የምትፈጠረዋን ጥቃቅን ስሕተት አጉልቶ እርስ በርስ በመናቆር በጦሱ ሕዝቡ እንዲጐዳ ማድረግ ባልታሰበ ነበር፡፡ ከአንተ ይኸ ይሻላል፣ ከእኔ ደግሞ ይኸኛው ለሕዝብ ይበጀዋል፣ ያኛውን መልካም ሐሳብ ደግሞ ከዚያኛው እንውሰድ በመባባል የእኔ ብቻ ነው ደግ ከሚለው መጥፎና ግትር አቋም ነፃ ወጥቶ ወደ ደገኛውና ለሀገራችን ወደ ሚበጀው አሠራርና አመራር በተገባ ነበር፡፡

በመሆኑም ትላንት በእጅጉ ያዘነበት ነገም እንዳይደገም የማድረግ ችሎታም ሆነ ሐላፊነት ያለባቸው አካላት በፍጥነት እየሄዱበት ያለውን መንገድ ተመልክተው እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ በእውነት ስለ እውነት ማድረግ አለባቸው እንላለን፡፡ አሁን በምንገኝበት የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የምንመለከተውንም ሆነ የምንሰማውን ነገር ሁሉ እውነት



'
www.eotcmk.org

ካልጐሰመችውና ካላረቀችው የባሰ እንዳይመጣብን እንሰጋለን።

ከላይ በመሠረታዊ መንሥኤነት ያነሳነው ጉዳይ በቀጥታ የወለደው ሌላው መሠረታዊ መንሥኤ ደግሞ በእነዚህ አካላት መካከል መተማመን አለመኖሩ ነው። ጐን ለጐን ተቀምጠው ሲወያዩም ሆነ በተናጥል ሆነው ሲናገሩ አውነት በመሠረትነት ስለሌለች በመካከላቸው መተማመን ጠፍቶ እናያለን። እንኳንስ ሀገርን የሚያህል በሰፊ መልክዐ ምድር ያለን ሰፊ ሕዝብ የያዘ ተቋም፥ በአንድ ቤተሰብ ዙሪያ ተወያይቶ የተሻለውን ነገር ለልጆች ለማድረግ የእናትና አባት መተማመን በእጅጉ ያስፈልጋል። እናት ለልጆች ይኽ ነገር ይደረግላቸው ብላ ሐሳብ ስታቀርብ አባት «እንዲህ ያልሽው ኪሴ እንዲራቆት ነው» ካለ ችግር ይፈጠራል። አባት ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ገንዘብ እንቆጥብ ሲል እናት ለግልህ መጨፈሪያ፣ ወይ ሌላ የምትቆጥብላት ብትኖር ነው እንጂ ካለች ጨዋታው ፈርሷል።

ዛሬ በሀገራችን ሥልጣን ለመያዝ በሚፎካከሩት አካላት መካከልም የምናየው ይህ ዓይነት አለመተማመንና እሱ የወለደው ነገርን አጣሞ የመተርጐም አባዜ ነው። አንዱ ምንም ያህል መልካምና ለሀገር የሚጠቅም ነገር ቢናገር ሌላው ጠቃሚ ነው ብሎ አይወስደውም።

ስለዚህ እነዚህ አካላት እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ሀገርን ያህል ትልቅ ነገር ለመምራት መሆኑን በሚገባ ተረድተው በመካከላቸው ፍጹም መተማመንንና መረዳዳትን ይፍጠሩ እንላለን።

ዛሬ ላጋጠመን ችግር ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ እነዚሁ አካላት ተቀራርበው መነጋገር አለመቻላቸው ነው። ይህ ምክንያትም የላይኞቹ ቀጥተኛ ውላጅ ነው። እውነት ላይ ተመርኩዘው ስለማይንቀሳቀሱ መተማመን አልቻሉም፣ ስላልተማመኑም ተቀራርበው በመወያየት ችግሮቻቸውን ለመፍታት አልሞከሩም። በእርግጥ እነዚህ አካላት በተለያዩ አካላት ሰብሳቢነትና ጋባዥነት በተለያዩ ጊዜያት በጠረጴዛ ዙሪያ ሲሰባሰቡ እናያለን። ይሁን እንጂ መሰባሰባቸው ልዩነታቸውን ሲያሰፋና የበለጠ ችግር ሲጨምርብን እንጂ ሰላማችንን ሲያረጋግጥልን አላየንም። ስለዚህ መቀራረብ ስንል በእውነት ላይ ተመርኩዞ በፍጹም መተማመን ተቀራርቦ የሚደረገውን ውይይት ነው።

በዚህ ዓለም የሚከናወን ማንኛውም ተግባር ውጤቱ ያማረ ይሆን ዘንድ ተቀመጠ የአከናዋኞቹ መተማመንና በሰከነ መንፈስ መወያየት ይጠይቃል። ይህ የሆነ እንደሆነ ውይይታቸው ሰምሮ ለእነሱም የአዕምሮ ዕረፍትን፥ ለሕዝቡም ሰላምንና መረጋጋትን ይፈጥራል። እንደ ምናየውና እንደ ምንሰማው ከሆነ ተፎካካሪዎቹ ተቀምጠው ይወያዩ እንጂ ከስሜት ጸድተው እርስ በርስ ተማምነው በሰከነ መንፈስ መወያየት የቻሉ አልመሰለንም። መልካም ነገር እናምጣ ብለው የሠሩት ጉባኤ በጭቅጭቅና በንትርክ ታውኮ ይበተናል። ወይም አንዳች ተስፋ የሚደረግ ነገር ጠብ ሳይለው ይፈጸማል።

ስለዚህም እነዚህ ወገኖች ዛሬም ቢሆንም በነገር ሁሉ ተስፋ ሳይቆርጡ፣ የደፈረሰ ሰላማችንን በማጥራት፣ የተጫነንን ፍርሃት እና ጭንቀት በመግፈፍ ከባድ ሐላፊነት እንዳለባቸው ተገንዝበው በሀገር ልጅነት መንፈስ በፍጥነት ተቀራርበው እንዲወያዩ አደራ እንላለን።

በአራተኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ሌላው ምክንያት ደግሞ ያለውን ችግር ግራ ቀኝ አይቶ ሁሉንም አካላት አቀራርቦ የሚያስታርቅ መጥፋቱ ነው። ከአህጉር አልፎ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ እንደ ተመሰከረው ሀገራችን በሚፈጠሩ ውስጣዊ አለመግባባቶች ዙሪያ ተወያይቶ የመተራረቅና የማስታረቅ የዳበረ ባሕል ያላት ሀገር ናት። ወደ ወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ ስንመጣ ግን ያ መልካም ባሕላችን የተዘነጋ ይመስለናል። የተለያዩትን አገናኝቶ ለማስታረቅ ብቃቱም ሆነ ብሔራዊ ሐላፊነቱ ያለባቸው ተቋማት ሀገራችንንም ሆነ ሕዝቧን ለአደጋ የዳረገ ጉዳይ ተፈጥሮ እያዩና እየሰሙ ዝምታን የመረጡበት ምክንያቱ ግልጽ አይደለም። ምንም እንኳን የተፈጠረው ችግር ይወገድ ዘንድ ከተፎካካሪዎች ጀምሮ እስከ ሕዝቡ ድረስ ቀላል የማይባል ሐላፊነት ያለ ቢሆንም ወቅቱ ተፎካካሪዎች ጐራ ለይተው ያዋጣናል ባሉት መንገድ ሁሉ እየተንቀሳቀሱ ያሉበት በመሆኑ በመካከል ገብተው ልዩነቶችን አጥብበው የሚያስታርቁ ግለሰቦችና ተቋማት ያስጠፈልጋሉ እንላለን።

ተፎካካሪዎችም «የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ» እንዲሉ ቋንቋቸውን የሚናገሩትንም ኢትዮጵያውያን ሽማግሌዎች መጋበዝና እናስታርቅ ብለው ሲቀርቡም ለእርቅና ለድርድር የተመቹ መሆን ይኖርባቸዋል።

የሁሉም ማሰሪያው ፈሪሃ እግዚአብሔር ነው። በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን መፍራት ካለ ፍቅር አለ፥ ሰላምም አትርቅም። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው እውነት አለው። በዚህ ዘመን፣ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፣ አስተዋይም የለም፣ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፣ ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፣ .... ጥፋትና ጕስቍልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም» እንዳለ /መዝ.13፥1-3/ ዛሬ ከሁሉም ወገን ፈረሃ እግዚአብሔር የራቀ ይመስለናል። በመሆኑም ሁሉም አካላት እግዚአብሔርን ፈርተው፥ እውነትን ገንዘብ አድርገው፥ እርስ በርስ በመተማመን ሊንቀሳቀሱ ይገባል እንላለን።

ሀገር ሰላም ቢሆን የሚጠቀመው ሕዝቡ ነው። በአንጻሩ በሰላም ፈንታ አለመረጋጋትና ኹከት በሀገሪቱ ቢነግሥ የሚጐዳው ሕዝቡ ነው። በመሆኑም በሀገራችን ትላንት የታየው እንዳይደገም፥ ነገ የምንፈራውም እንዳይከሰት በመከላከል በኩል ሕዝቡ ማንም ሊሰጠውም ሆነ ሊነሳው የማይችለው ሥልጣን፣ መብትና ኃይል አለው። ሀገር ዐቀፍም ይሁን አህጉር ዐቀፍ አልፎም ዓለም ዐቀፍ በሆኑ የታሪክ ማስረጃዎች በግልጽ እንደ ተመሰከረው ኢትዮጵያውያን ሰላምን የሚወዱ ታላቅ ሕዝቦች ናቸው። ሰላማቸውን አደጋ ላይ ለመጣል የሚመጣ ካለ በቸልታ አይመለከቱትም። በዚህም ሉዐላዊነታቸውን ደፍሮ ነጻነታቸውን ለመግሰስ በተለያየ ጊዜ የመጣን ኃይል ሰላም ናፋቂነታቸውን ሰንቀው በአንድነት ተባብረው አሳፍረው መልሰዋል።

ይህንን እያደረጉም በውስጣቸው አለመግባባቶችና ሰላምን የሚያናጉ ነገሮች ሲከሰቱ ባኗቸው ሀገር በቀል ችግሮችን የማስወገጃ ባሕሎች ተጠቅመው የደፈረሰ ሰላማቸውን ያጠራሉ። የተጣመመውን ያቃናሉ። የራቀውን ያቀርባሉ። የጓጐለውን ያደቃሉ። በመሆኑም ይህ ነባር የሀገራችን ጠቃሚ ባሕል ዛሬም ተግባር ላይ ሊውል ይገባል። ከነባሮቹ የኢትዮጵያውያን ችግር ማስወገጃ መንገዶች አንዱ ጸሎትና ምሕላ ነው።

ኢትዮጵያውያን የማይፈልጉት አለመረጋጋትና ኹከት በመካከላቸው ሲከሰት የሰላም አምላክ ሰላማቸውን ይመልስላቸው ዘንድ በጸሎትና ምሕላ ይጠይቃሉ። ዛሬም ይህ የሰላም እጦት አደጋ ክፉኛ ያንዣበበብን ኢትዮጵያውያን እንደ ቀደምቱ አባቶቻችንንና እናቶቻችን አምርረን ልንጸልይ ምሕላ ልንይዝ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሕዝቡን በጸሎት የማትጋት ሐላፊነት ያለባቸው በየደረጃው ያሉ አባቶቻችን የበለጠ ሊተጉ ይገባል እንላለን።

በመጨረሻም እግዚአብሔር የቅድስት ሀገራችንን ሰላም ይጠብቅልን ዘንድ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ምልጃ፣ የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት፣ የጻድቃን ሰማዕታት ጸሎትና ምልጃ አይለየን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

## ኑና እዩ

መጽሔታችሁ እኛ ዘንድ አትደርስም ነበር:: አሁን ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት በሥራ እየተመደቡ መምጣት በመጀመራቸው በእርሱ አማካይነት እየደረሰችን እያነበብናት ነው:: በእውነቱ መጽሔቷ ያልተጠሩትን በመጥራት፣ የተጠሩትን በማበርታት ከፍተኛ አገልግሎት የምትሰጥ ሆና አግኝተናታልና በርቱ::

በመጽሔቷ ከተካተቱት ዓምዶች አንዱ የተለያዩ ቅዱሳት መካናትን የምታስተዋውቁበት የ«እናስተዋውቃችሁ» ዓምድ ነው:: በርካታ ቅዱሳት መካናትና መካናተ ተኣምራት ባሏት ቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ዓይነት ዓምዶች በእጅጉ ያስፈልጋሉ:: ይህን ካልን ዘንድም በእኛ አካባቢ አንዲት ጥንታዊትና ሰፊ ታሪክና ቅርስ ያላት ገዳም አለች:: ደብረ ወይላ ማርያም ገዳም ትባላለች:: ይቺን ገዳም ጐብኝታችሁ የተቀደሰ ታሪኳን ለምእመናን እንድታቀርቡ እጠይቃችሁአለሁ::

*አባ ገ/ሚካኤል*
*ደብረ ወይላ*

__ከአዘጋጁ፡-__ አባ፤ መጽሔታችንን አንብበው አስተያየትዎን ስለ ቸሩን በአንባብያን ስም እናመሰግናለን:: በዚሁ ይቀጥሉ:: ገዳሚን በሚመለከት እርስዎ በአካባቢው ካሉ የማኅበራችን አባላት ጋር በመተባበር ታሪኳን በስፋት ዘግበው ከፎቶ ግራፍ ጋር ቢልኩልን ለማስተናገድ ዝግጁዎች ነን:: ነገር ግን ታሪኩ በሚገባ የተቀናበረና በመረጃ የጠገበ መሆን አለበት::

## ኮራሁባቸው

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም በዓምደ ወራዙት ዓምድ በቀረቡት በአባ ወልደ ትንሣኤ እጅግ ኮራሁ:: ብዙም ተማርኩ:: በእውነቱ እናንተም በቃለ ምልልሱ መጨረሻ እንዳላችሁት እንደነዚህ ዓይነት አባቶች በቤተ ክርስቲያናችን ሊበዙልን ይገባል:: እርሳቸውንም የሚያገለግሉት አምላክ ያሰቡትን መልካም ሐሳብ ሁሉ እያሳካ ረጅም ዕድሜን ከሙሉ ጤና ጋር እንዲሰጥልን ከልብ እመኛለሁ::

*ዮናስ መሥፍን*
*ወላይታ ሶዶ*

## ወጣቱ ለቀርሶቹ

ምንም እንኳን ሁሉም የዚህ ዘመን ወጣት ነው ለማለት ባልደፍርም ባለንበት ዘመን የወጣቱ ለቅርሶች ያለው አመለካከት ደካማ ነው:: ይህም የሆነው የማንነቱ መገለጫ የሆኑትን ቅርሶች ቀርቦ ባለማየቱ፣ ሊወስደው ከሚፋጠነው የዘመናዊነት /ቴክኖሎጂ/ ተጽዕኖ እና ትውልዱ ቅርሶቹንና ታሪኩን ዐውቆ ዘብ እንዳይቆም በሚፈልጉ አካላት ስውር ሴራ የተነሣ ነው:: ስለዚህ ምንም እንኳን የኢትዮ ጵያና ኢትዮጵያዊነት መገለጫ የሆኑ ቅርሶችን በማወቅ በኩል ቀዳሚውን ድርሻ የሚይዘው ወጣቱ ቢሆንም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ወጣቱንና ቅርሶቹን በማስተዋወቅ በኩል ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል እላለሁ::

*በዛብህ መኮንን*
*ደሴ ቤተ አብርሃም*
*ሰንበት ት/ቤት*

## ተማርኩ

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር 2 መጋቢት - ሚያዝያ እትም በ«እናስተዋውቃችሁ» ዓምድ ላይ «ለንጊኖስ ሰማዕት» በሚል ርእስ የቀረበውን የቅዱስ ለንጊኖስ የሕይወት ታሪክ አንብቤ በመደሰቴ ይህንን ደብ ዳቤ ጻፍኩ:: በእውነቱ ለንጊኖስን በሚመለከት የተሳሳተ ዕውቀት ነበረኝ ማለት ይቻላል:: እንደ እኔ ሁሉ ሌሎችም ተመሳሳይ ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚችል አልጠራጠርም:: ይኸውም ለንጊኖስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ጐኑን በጦር መውጋቱን ብቻ እንጂ በመጨረሻ በሰማዕትነት ያለፈ ቅዱስ መሆኑን አላውቅም ነበረና ነው:: በእውነቱ እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች በርካታ ታሪኮች እንዳሉ አስባለሁና በዚሁ አቅጣጫ ቀጥሉበት እላለሁ::

*ወለተ ወልድ*
*ሐረዋጫ*

## ትጉኅ አባት

መምህሬ ምትኩ ይባላሉ:: የህገረ ማርያም ደብረ ገነት ቅ/ማርያም ደብር ቀዳሽ ናቸው:: እኒህ አባት በወር ሁለት ጊዜ የንስሐ ልጆቻቸውን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ እየሰበሰቡ ያስተምራሉ፤ ይመክራሉ:: በዚህም ልጆቻቸው ከነጣቂ ተኩላዎች ተጠብቀው ይኖራሉ:: ይህ አርአያነታቸው ለሌሎች አባቶችም እንዲሆን ያስፈልጋል::

*ዲ/ን በጋሻው ለገሠ*
*ሀ/ማርያም*

## አርአያ

በሀገራችን በበረሃነቱ በሚታወቀው የአፋር ክልል በአብዛኛው አካባቢ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የክርስትና እምነት በምንፈልገው መንገድ የተስፋፋ አልነበረም:: ነገር ግን በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ዮናስና ረዳቶቻቸው አማካይነት ስብከተ ወንጌሉ እየተጠናከረ መጥቷል:: በዚሁ ክልል በአሚባራ ወረዳ የምትገኘው የወረር ደ/መ/መ/ዓ/ቤ/ሰ/ት/ቤት እንቅስቃሴ መልካም ነው:: ሰንበት ት/ቤቱ ከማኅበረ ቅዱሳን አፋር ግ/ጣቢያ ጋር በመሆን ከግንቦት 20 -21 1997 ዓ.ም ታላቅ ጉባኤ አዘጋጅቶ ነበር:: በእውነቱ ሰንበት ት/ቤቱ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር ተቀናጅቶ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊደነቅ የሚገባና ለሌሎች ሰንበት ት/ቤቶችም በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል ነው:: እግዚአብሔር ሁላችንንም ያበርታን::

*ዲ/ን ሲሳይ ዳምጠው*
*አ.አ.ዩ- 6 ኪሎ*

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን አስተያየታችሁን፣ ጥቆማችሁንና ጥያቄዎቻችሁን ያዘሉ ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: እግዚአብሔር ይስጥልን:: በተሳትፎአችሁ ቀጥሉ::

ዲ/ን ሲሳይ ዳምጠው /አ.አ.ዩ/፣ ቢ.ኤ /ጅጅጋ/፣ ቸር አምላክ ሃይማኖት /ዓለም ከተማ/፣ ሙሉ ጌታ ዓለማየሁ /ሰቆጣ/፣ ትዕግሥቱ ምጋ ስናው /ጐንደር/፣ አብርሃም ተድላ /ጊዶሌ/፣ ባለው ሙኔ /ሞጣ/፣ አንተነህ ማትያስ /ባ/ዳር/፣ ንብረት በጅጋ /ተፍኪ/፣ መ/ር ኃ/ኢየሱስ መርሻ /ደ/ብርሃን/፣ ሳህለ ሚካኤል ዘመካነ ሕይወት፣ጸጋዬ ዘውዴ /ወልዲያ /፣ሰሎሞን ገ/መድኅን /መኮይ/፣ ዘካር ያስ ዓለሙ /ያቤሎ/፣ዲ/ን እሱባለው ደምስ /እንጭኒ/፣ጋዲሳ ቢፍቱ /መቀሌ/፣ መ/ር ሙሉታ አንተነህ /አሰላ/፣አሳዬ ዓለማየሁ /ሻሸመኔ/፣ኃ/ኢየሱስ ጌታሁን /ሶያማ/፣ይመሰል አለ ባቸው /ወልድያ/

ክቡራን አንባብያን ባለፈው እትማችን አልፎ አልፎ ለተፈጠሩት የፊደላት ስሕተቶች ከፍ ያለ ይቅርታ እንጠይቃለን::

*ዝግጅት ክፍሉ*



www.eotcmk.org

# ቅርሶቻችን፡- ይመለሱ? ወይስ ለደህንነታቸው ሲባል በዚያው ይቆዩ?

*በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሀገር የወጡ ቅርሶቻችን ይመለሱ? ወይስ ለደህንነታቸው በዚያው ይቆዩ? በሚሉ የመወያያ ነጥቦች ዙሪያ አንባብያን አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልን ባለፈው እትም መጋበዛችን ይታወሳል:: ይህንኑ ግብዣችንን በመቀበል በርካታ አንባብያን አስተያየቶቻችሁን ልካችሁልናል:: አሁንም ቀጥሉበት እያልን ለዛሬው የአንድ አንባቢያችንን አስተያየት አቅርበናል::*

በቅርሶቻችን ዙሪያ እንድንወያይ መድረኩ መከፈቱ በራሱ ስለ ቅርሳችን እንድንቆሮቆርና «ከእኔ ምን ይጠበቃል?» የሚለውን እንድናስብ ያደርገናል:: ማሰብም ብቻ አይደለም የድርሻችንን እንድንወጣ ያነሣሣናል:: ስለዚህ ይህ ዓይነቱ የውይይት መድረክ በሌሎችም ጉዳዮች ቢቀጥል መልካም ነው::

ወደ ተያዘው ርእሳችን ስመጣ የቅርሶቹ ባለቤቶች እኛ ነንና ወደ እኛ መምጣት አለበት የሚለው ነገር አጠያያቂ ጉዳይ አይሆንም:: አነጋጋሪ የሚሆነው እንደ እኔ ግምት «መቼ ነው መመለስ ያለበት?» የሚለው ይመስለኛል::

በአሁኑ ሰዓት የአገራችን ቅርሶች የሚገኙት በውጭ ብቻ አይደለም፤ በአገራችንም ጭምር እንጂ:: ዛሬም በርካታ የብራና መጻሕፍት፣ ንዋያተ ቅድሳት፣ የነገሥታት ዘውዶች የግራኝ ካባ ሳይቀር ወዘተ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ::

እነዚህ በእጃችን ያሉ ቅርሶች ግን በትክክል ክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛሉ ወይ? ለመሆኑ ያሉትስ መኖራቸውን እንጂ ቁጥራቸው በትክክል ይታወቃል ወይ? የመጻሕፍቱስ ዓይነት ምን ምን እንደሆነ ይታወቃል ወይ? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቤተ ክርስ ቲያን መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች መጻሕፍትም አሉ:: እነዚህ ሁሉ ተለይተው ተቀምጠዋል ወይ? በአን ዳንድ የጥንታዊ አብያተ ክርስቲ ያናት ዕቃ ቤት ብዙ የብራና መጻሕፍት በአቀማመጥ ችግር የተጎዱ የሉ ምን? ስለዚህ እና መሰል ችግሮች ዛሬ ምንድን ነው የተሰጠው መፍትሔ? በእጃችን ያለው ንበወጉ ያልያዝን ሰዎች የውጭዎቹ ቅርሶች ላይ ትኩረታችን እንዴት ሊበረታ ቻለ? በውስጥ ያሉት ላይስ ለምን አልተበረታምና ሥራ አልተሠራም? ምናልባትም እነዚህ የተዘረፉ ቅርሶች እኮ ባይዘረፉና ኢትዮጵያ ውስጥ ኖረው ቢሆን በከፊል የተወሰነው በተለይ ብራናው ወይ ይበላሽ ነበር፤ ወይ ይቃጠል ነበር... በመጽሔቱ በጋዜጣው መጻሕፍት ወደሙ፣ ንዋያተ ቅድሳት ተቃጠሉ፣ ተበላሹ ወዘተ የሚል ዜና ጆሮአችን እየጠገበ አይደለም ወይ?

ተዘርፈው ያሉት ቅርሶቻችን በአብዛኛው የብራና መጻሕፍት ናቸው:: እኔ እንደ ማስበው ብዙ ምሁራንን ወደ ቤቱ የጠራበት /የሚጠራበት/ መንገድ ሊሆን ይችላል:: ስለ ሃይማኖታችን ስለ ቋንቋችን /ግእዙን/ ስለ ሥርዓታችን ዐውቀው እንዲጽኑበት አድርጎ ሊሆን ይችላል:: በገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደ ተገለጸው ታሪክ ዓላዊው ትራስ አድርጎት የነበረው ጽሌ ኋላ ንጉሡ ራሱ እንዲድንበት ምክንያት ሆአል::

ሚዛን ባይደፋም ዛሬ «የግእዝ ቋንቋ እየሞተ ነው» ለሚሉ የተሳሳተ አመለካከት ላላቸው ጥቂት ምሁራን በውጭ ዓለም የግእዝ ቋንቋ መታወቅ፥ መጠናት እንደ አንድ ቋንቋ በጥልቀት መታየቱና ብዙ ምርምር መደረጉ እኛ ስለ ሰነፍን እግዚአብሔር ለበጎ አድርጎት እኮ ሊሆን ይችላል:: ይህን ስል ብራናው ሁሉ በውጭ ይቀመጥ ማለቴ እንዳልሆነ ልብ ይባል:: ቋንቋውን አጥንተው ምን አመጡ ማለት ያለብን አይመስለኝም:: እኔ እንኳ ገጠር ያለሁት ለመጀመሪያ ግዜ ስንክሳርን በሚገባኝ ቋንቋ በአማርኛ ከመተርጎሙ በፊት ያነበብኩት በእንግሊዝኛው ነው:: በእንግሊዝኛ ብቻ አይደለም በሌሎች

ቋንቋዎችም እንደ ተተረጎመ የጽሑፍ መረጃ ልጠቅስ ባልችልም ሰምቻለሁ::

ስለዚህ በእኔ ግምት መጀመሪያ እስቲ ከውስጣችን ያለውን ቅርስ በአግባቡ እንያዝ፣ እንከባከብ:: የውስጡ ከተስተካከለ እኮ የውጭውም ችግር ይስተካከላል:: የውጭው ቅርስ የትም አያመልጠንም፤ ካሰብንበትስ እያመለጠን በቃጠሎ በዝናብ... እየወደመ ያለው እዚህ አገር ውስጥ ያለው ነው:: አስተያየታችንን እንድንሰጥ በጋበዛችሁበት ጹሑፍ ላይ «ማን ይከባከባቸዋል ...» የሚለው አሳማኝ ምክንያት አይደለም» የሚል ሓሳብ ቀርቧል:: ያለንን መች ተከባከብን? ከሌባስ መች ጠበቅን? ምናልባትም ከውጭ ያለው ቢመጣ ተመልሶ መሰረቁ አይቀርም፤ «እውነት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ቅርሶቻችን ተገቢ ክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛሉ ወይ? ስለዚህ ያም ቢመጣ መከባከብ ከሌባ መጠበቅ እንችላለን?» ብለን ደፍረን የምንናገርበት ምክንያት አለን?

ምናልባት ውጭ ያለው ቢመጣ ዓለም ስላወቀው ለጊዜው ሽርጉድ ብለን እንይዘዋለን የሚል ታሳቢ ይዘን ከሆነ ጥሩ አይመስለኝም:: ለምን? ኋላ ያው ቅርሱ ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላልና:: ቅርሱ እኮ ከመጣ በባለቤትነት መረከብ ያለባት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ታድያ ቤተ ክርስቲያን እውን ያለውን በወጉ ቆጥራ፥ ቦታ አዘጋጅታ፥ ጠባቂ አኑራ ያላትን በትክክል ያልያዘች እንዴት ተደርጎ ነው መጭው ቅርስ እፎይ የሚለው?

ይልቅ መምጫው ጊዜ እስኪደርስ እዚያው ሃይማኖታችንን ሥርዓታችንን እያመሳጠረ ሲያስተምር ይከረም:: ከዚያ ሐዋርያዊ ግዴታውን ጨርሶ ይመለሳል:: ብራናውን አንቦ እኮ ክርስቲያን የሚሆን አለ:: ያልሆነም ለፍርድ:: እኛ ዐሥሬ እንደሚሰበክልን እነርሱንም ሲሰብክ ሲገሥጽ ይሰንብት:: ሁሌ እኮ በውስጣችን ያለው ነገር ሲስተካከል የውጭውን ለማሣመር የሚያውቅበት አምላክ ነው ያለን:: ስለዚህ መጀመሪያ በቅርብ ያለው ትኩረት ይሰጠው:: አበቃሁ:: ካጠፋሁ ይቅርታ፥ አሳማኝ ተቃራኒ ሐሳብ ካለ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

*ኃይለ ኢየሱስ መርሻ*
*ደብረ ብርሃን*



www.eotcmk.org

# ክረምት

> *«ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ፤ ክረምትና በጋን የፈጠርኸ አንተ ነህ»*
>
> *መዝ.73÷17::*

*መሪ ጌታ ተስፋ ሚካኤል ታከለ*

ክረምት ቃሉ ግእዝ ነው:: ሥርወ ቃሉም «ከርመ»÷ ከረመ የሚለው የግእዝ ግስ ነው:: ይኸውም ወቅቱ ቆይቶ በዓመት የሚመጣ ስለሆነ ነው:: ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ዓመቱን ከአራት ከፍሎ ፍጥረቱን የሚመግብ መሆኑን ለምእመናኖቿ ታስተምራለች:: እነዚህም መፀው፣ሐጋይ፣ጸደይ፣ክረምት ይባላሉ:: መፀው (መከር) ከመስከረም 26 ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 25 ያለው ነው፤ ሐጋይ (በጋ) ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ያለው ነው ጸደይ (በልግ) ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ያለው ነው፤ ክረምት ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ያለው ነው:: ከነዚህ አራት ክፍላተ ዓመት አንዱ ወርኃ ክረምት ነው:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የክረምትን ወቅትና ምሳሌዎቹን እንደሚከተለው እንመለከታለን:: መልካም ንባብ::

ክረምት ማለት ምን ማለት ነው? ክረምት ማለት:– «ዝናም፣የዝናም ወራት በጸደይና በመፀው መካከል የሚገኝ ክፍለ ዓመት» ማለት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ክረምት «ዓመት፣ዘመን፣ዕድሜ» የሚል ትርጉምን ይሰጣል:: «ወናሁ መጽአት ብእሲት እንተ ደም ይውኅዛ እም፲ቱ ወክልኤቱ ክረምት፤ ደም መፍሰስ ከጀመራት ዐሥራ ሁለት ዓመት (ዘመን) የሆናት ሴት መጣች» ሲል ይገኛልና:: ማቴ.9÷20:: ክረምትን አስገኚው በመግቦቱ ከፍጥረታቱ የማይለይ አምላካችን እግዚአብሔር ነው:: የዘመናት ባለቤቱ፣ ሠሪው፣መሪው እርሱ ብቻ ነውና:: ይህን የተገነዘበው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት:– «ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ፤ ክረምትና በጋን የፈጠርኽ አንተ ነህ» በማለት የበጋና የክረምት ባለቤቱ፣አስገኚው እግዚአብሔር መሆኑን መስክሯል:: መዝ.73÷17::

እግዚአብሔር ክረምትን ሲያመጣ÷ ዝናምን ሲያዘንብ ዓላማ አለው::

1. የእርሱ መግቦት ከፍጥረቱ እንዳልተለየ÷ በዚህ አማናዊ መግቦቱ ፍጥረቱን ለማስተማር ነው:: ዝናመ ምሕረትን፣ጠለ በረከትን የሚያወርድ እግዚአብሔር መሆኑን የተመለከተ ምእመን በየዓመቱ ከማያቋርጥ ከዚህ አምላካዊ ሥራ ታላቅ ትምህርትን ይማራልና::

2. ብዝኃ ትዕግሥቱን (የትዕግሥቱን ብዛት)፣ይቅርታውንና ርኅራኄውን ለፍጥረቱ የሚያስተምርበት አንዱ የማስተማሪያ መጽሐፍ ነው:: ከሌላው ፍጥረት ይልቅ ግእዛን ሰጥቶ የፈጠረው የሰው ልጅ ከዚህ አምላካዊ ሥራው ቻይነቱን፣ርኅራኄውን፣ ይቅርታውን የሚያነብበት የሚያውቅበት አማናዊ መጽሐፍ ነውና:: ምክንያቱም የበደሉትን እንደ በደሉኝ ልበድላቸው፣በአምልኮት ከእርሱ የራቁትን እንደ ራቁኝ ከመግቦቴ ላርቃቸው ሳይል መዓልትና ሌሊቱን ማፈራረቁ፣ነፋሳትን ማንፈሱ፣በጋና ክረምትን ማመላለሱ በጥልቀት ለሚያስተውል አእምሮ ቻይነቱን፣ታጋሽነቱን ያስረዳናል:: «እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይም ዝናምን ያዘንማልና» /ማተ.5÷45/ በማለት ይህን ቀጣይነት ያለው አማናዊ ድርጊት ምሳሌ በማ ድረግ እኛም እንደ ርሱ የበደሉንን ሳንበድል÷ የራቁንን ሳንርቅ ሰው ከእኛ የሚሻውን እንድናደርግ ፣ ቸሮች፣ ይቅር ባዮች፣ታጋሾች እንድንሆን በምሳሌ አስተምሮናል::

ክረምት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ በሕይወታቸው እንዲቀጥሉ የሚያደርግ መሠረተ ሕይወት ነው:: የፍጥረትን ሕይወት እንጂ ጥፋት የማይፈልግ ሕያው እግዚአብሔር ለፍጥረታት ሕይወት መሠረት የሆኑ፣ወርቅ፣ ብር የማይመዘንላቸው÷ ቢመዘንላቸው ስንኳን ዋጋቸው የማይሆን አራቱን ሀብታት ለፍጥረቱ ሁሉ ያለ ዋጋ በከንቱ በልግሥና ሰጥቷል:: እነዚህም ነፋስ፣ እሳት፣ መሬትና ውኃ ናቸው:: ፍጥረት ከፍጥረት የሚገኘውን ነገር በወርቅ ገዝቶ የእርሱ ማድረግ ይችል ይሆናል:: ከፈጣሪ የሚገኘው ይህ ዓይነት ሀብት ግን ዋጋ አይገኝለትም:: መግዛት ቀርቶ መተመኑ (መገመቱም) ከአእምሮ በላይ የሆነ ከባድ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ:– «ከዚህ ቀን ጀምሮ በዚህ ዓለም ያለህ ፍጥረት ሁሉ ነፋስን (አየርን) ገዝተህ መጠቀም አለብህ» ቢባል ለሰዓት ቀርቶ ለቅጽበት (ሰከንድ) የሚጠቀምበትን ነፋስ (አየር) ለመግዛት የሚከፍለው ዋጋ ባላገኘም ነበር፤ ከዋጋ በላይ ነውና:: ነገር ግን እጅግ የሚያስፈልገንን ሀብት የሚያውቅ እግዚአብሔር እኛን ከመጥቀም አልፎ እኛ የምንጠቀምባቸው ዕፅዋት፣ አትክልት፣ አዝርዕት በቅለው ከፍሬ እንዲደርሱና ዘአፈሩም በኋላ ገለባውን ከፍሬው እንድንለይበት የተትረፈረፈ ነፋስን (አየርን) ሰጥቶናል:: ይህን የማያልቅ የሀብት መሠረት ለሁሉም አትረፍርፎ ባይሰጠው ኑሮ አንድ ቀበሌ ሕዝብ ወጥቶ ቢተነፍስ አንድ ኩንታል ጤፍ ማጥራት የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው::

የእሳትና የመሬትንም አገልግሎት በማስተዋል ለተመለከተው ሰው÷ ዋጋ የማይገኝለትና ለሕይወት መሠረት መሆኑ ብዙም ትርጓሜ የማያስፈልገው እውነታ ነው:: ከእነዚህም መሠረታዊ ሀብቶች አንዱ ክረምት (ውኃ) ነው:: ክረምት ከሌለ ልምላሜ የለም:: ልምላሜ ከሌለ ፍሬ የለም:: ፍሬ ከሌለ ፍጥረት የለም:: ስለዚህ ከሀብት በላይ የሆነ ክረምትን የሰጠንን እግዚአብሔርን ከማመስገን ጋር የተሰጠንን ሀብት በሚገባ መጠቀም ይገባናል::

*የክረምት (የዝናም) ምሳሌዎች:–*

ሀ. *ቃለ እግዚአብሔር:–* የምንኖርባት ዓለም (ምድር) ያለ ዝናም ሥጋዊ ምግብን ማስገኘት አትችልም:: ስለሆነም ነው አምላካችን እግዚአብሔር ለምድር ዝናምን ያዘጋጀው:: «ወያስተዴሉ ክረምተ ለምድር፤ ለምድር ክረምትን ያዘጋጃል::» እንዲል:: መዝ.146÷10:: እግዚአብሔር መሬትን በዝናመ ምሕረት በጐበኛት ጊዜ እርሷ ከመርካቷም በላይ ለሰው ልጅ ዐይን በሚያስደስቱ ልምላሜያት÷ ልቡናን በሚስቡ ጽጌያት አሸብርቃና ደምቃ ትታያለች:: ይህን እውነታ የተመለከተው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ምድርን ጎበኘሀት÷ አጠጣሀትም፤ ብልጥግናዋንም እጅግ አበዛህ፤ ምግባቸውን አዘጋጅህ እንዲሁም ታዘጋጃለህ፤ ትልንም ታረካለህ» በማለት ተናግሯል:: መዝ.64÷9::

አምላካችን እግዚአብሔር ምድርን በዝናም ምክንያት እንደሚያረካት፣ በልምላሜ፣ በጽጌ እንደሚያስጌጣት ሁሉ ዓለምን አንድ አድርጎ ቢገዛ፣ቢነዳ የማይረካ የሰውን ልቡናም በቃሉ አማካይነት እንዲረካ÷ በምግባረ ሠናይ እንዲያሸበርቅ ያደርገዋል:: በቃሉ የረኩ ቅዱሳን:– «ሐዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባዕለ ጠጐች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው» /2ቆሮ6÷10/ በማለት በሕ



www.eotcmk.org

ይወታቸው ያለውን ርካታ በግልጽ ተናግረዋል:: ይህን ከማለት ያደረሳቸው በዝናም የተመሰለ የእግዚአብሔር ቃል እከብር ባይ ልቡናቸውን ሰብሮ ገብቶ ስላረካው መሆኑን ልብ ማለት ይኖርብናል:: በቃሉ የረኩ ቅዱሳን ፍሬ ሃይማኖትንም ይዘው አፍርተው ተገኝተዋል:: «ሃይማኖቴን ጠብቂያለሁ፤ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል::» 2ጢሞ.4÷7:: እንዲል:: ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ፍሬ ያደረሰው የቃሉ ዝናምነት ነውና:: ሐዋ.9÷4::

ከገዳማውያን መነኮሳት አባ እንጦንስን በምናኔ ሕይወት እንዲያሸበርቅ÷ የምንኩስናን ፍሬ እንዲያፈራ ያደረገው ሰማያዊው ዝናም ቃለ እግዚአብሔር ነው:: አባ እንጦንስ ከዕለታት አንድ ቀን ቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ሲያስቀድስ «ምንት ይበቁእ ለሰብእ ለእመ ኩሎ ዓለመ ረብሀ ወነፍሶ ኃጕለ፤ ሰው ዓለሙን ቢገዛ በነፍሱ ግን ከተጐዳ ምን ይረባዋል፤ ምን ይጠቅመዋል፤» /ማቴ.17÷26/ የሚለውን ቃል ካህኑ ሲያነቡ በሰማ ጊዜ ከዚህ ዓለም ሀብት፣ ከሚች ዘመድ ተለይቶ የምናኔ ሕይወትን ገንዘብ ለማድረግ ወሰነ::

ይህ ሁሉ የቃለ እግዚአብሔር ውጤት መሆኑን አንባቢው ልብ ይበል:: ዛሬም የምእመናን ሕይወት ከቃለ እግዚአብሔር ያልተለየ ከሆነ በሥነ ምግባር ይለመልማል፣ፍሬ ክብር÷ ፍሬ ሃይማኖትንም አፍርቶ ይገኛል:: ስለዚህ የምእመናን ሕይወት ዘወትር ከቃለ እግዚአብሔር መለየት የለበትም:: ሕይወቱ ቃለ እግዚአብሔርን ከማጣቱ የተነሣ ከመድረቁ በፊት እርሱነቱን በንስሐ ማረሻ እያለሰለሰ ዝናም ቢዘንምለት ለማብቀል የተዘጋጀ እርሻ አድርጐ መዘጋጀት ይኖርበታል:: ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ፡- «ጥጋቱን መሬት እረሱ÷ በእሾኽ ላይ አትዝሩ» በማለት የኢየሩሳሌም ሰዎችን ያስጠነቀቃቸው ለዚህ ነው:: ኤር.4÷3::

መሬት ጥጋቱ ሳይታረስ እሾኹ ሳይመነጠር /ሳይቆረጥ/ ቢዘሩባት ዘረ ቆርጥም ከመሆን በቀር የሚፈለግባትን ፍሬ አታስገኝም:: ነቢዩ ኤርምያስ እስራኤል ጥጋቱን እንዲያርሱ መምከሩ እስራኤል በሥጋዊ ሕይወታቸው ተቸግረው ስለ ተመለከተ በሚገባ አርሰው፣ዘርተው ከሥጋዊ ችግራቸው እንዲላቀቁ ፈልጐ አልነበረም፤ በምሳሌ ለማስተማር እንጂ:: መሬት የተባለ ሰው ነው:: የሰውን መሬትነት ቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ይመሰክራሉ:: «ኦ አዳም÷ መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት፤ አዳም ሆይ÷ አንተ መሬት ነህ፤ ወደ መሬት ትመለሳለህ::» ዘፍ.3÷19፤ መዝ. 102÷14፤ 3መቃ.5÷1::

ጥጋት የተባለው ደንዳና ልቡና ÷ ንስሐን የማይሻ ልቡና ነው:: እሾኽ የተባለ ቂም፣ በቀል (ኃጢአት) ነው:: «ንስሐ የማይሻ ደንዳና ልቡናን አስወግዳችሁ ከኃጢአት አርቃችሁ በቃሉ ዝናምነት መልካም ፍሬን ለማፍራት ተዘጋጁ» ሲላቸው ነው:: ስለዚህ እውነተኛውን ፍሬ እንዲያፈራ በአርባና በሰማንያ ቀን ከቤተ ክርስቲያን የተተከለ ምእመን ጥጋት የተባለ ደንዳና ልቡናን እሾኽ የተባለ ኃጢአትን በንስሐ አስወግዶ ክረምቱን፣ጭቃውን፣ብርዱን ሳይሰቀቅ ከቃሉ (ቃል ከሚነገርበት ቤተ ክርስቲያን÷ ከሠርክ ጉባኤ) መለየት የለበትም:: የዝናም መግቦት የተለየው ተክል የሚፈለግበትን ፍሬ ማፍራት ይቅርና ደርቆ ለእሳት ማገዶ እንደሚሆን ሁሉ ከቃለ እግዚአብሔር ምግብነት የተለየ ምእመንም ፍሬ ምግባር ፍሬ ሃይማኖት ሳያፈራ በመንፈሳዊ ሕይወት ደርቆ ሲያል ከመውደቅ በእግረ አጋንንት ከመጠቅጠቅ ይደርሳልና:: ስለዚህ ለሕይወት የተፈጠረ የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር መሠረት የሆነ ሰማያዊ ምግብ ቃለ እግዚአብሔርን ዘወትር መመገብ ይኖርበታል:: ማቴ.4÷4፤ዘዳ.8÷3::

### ለ. ጥምቀት

ክረምት ወርኃ ማይ (ውኃ የሚገኝበት ክፍለ ዓመት) ማለት ነው:: ጥምቀትም የሚፈጸመው በውኃ ነው:: ክረምት የሚጠቅመው ለሁሉም ፍጥረት ነው:: ጥምቀት የሚጠቅመው አምኖ ለመጣው ሁሉ ነው:: ክረምት የሚጠቅመው ዝናሙን ጭቃውን ሳይሰቀቅ ለሠራ ሰው ብቻ ነው:: ጥምቀትም የሚጠቅመው ሥርዓተ ጥምቀትን በሚገባ ዐውቆ ጾሙን ጸሎቱን ሳይሰቀቅ በተግባር ከተረጎመ ብቻ ነውና:: ክረምት ለፍጥረተ ዓለም ቀጣይነት ሕይወት÷ መሠረት ነው:: ጥምቀትም ግእዛን ተሰጥቶት በሕይወት እንዲኖር ለተፈጠረ ለሰው ልጅ ሁሉ መሠረት ነውና:: «ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ማር.16÷16:: «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም::» ዮሐ.3÷3:: «ሳንጠመቅ ዘለዓለማዊ ሕይወትን መምራት እንችላለን» የሚሉ ቀልደኞች (ኢጥሙቃን አማሌቃውያን) ቢኖሩም ክረምት ከሌለ የምድራውያን ፍጥረታት ሕይወት በሙሉ ቀጣይነት እንደሌለው ሁሉ ያልተጠመቀ ሰውም ዘለዓለማዊ ሕይወት የሌለው መሆኑን ከቃሉ መገንዘብ ይኖርብናል::

ሐ. ሃይማኖት:- የክረምት ልምላሜ ፍጥረተ ዓለም ለወደፊት ያለውን ተስፋ ከሩቅ ያመለክታል:: ሃይማኖትም ሰው በእምነቱ ቢጸና ለወደፊት ያለውን ተስፋ ከሩቅ ሆኖ እንዲመለከት ታደርገዋለችና:: «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውን ነገር የሚያስረዳ ነው::» ዕብ.11÷1:: «እግዚአብሔር በሰጠኝ አካል፣ለሥራ ባዘጋጀልኝ ክረምት ጠንክሬ በመሥራት ለእኔም፣ለወገኔም፣ለጦም አዳሪዎችም የሚተርፍ ሀብት አገኛለሁ» የሚል ጽኑ ዓላማ ለሌለው ሰው የክረምቱ ጭቃው፣ብርዱ፣ዝናሙ ያሰቅቃል፤ ሃይማኖትም «ነገ የሚፈርስ የሚበሰብስ አካሌን ለሥርዓተ ሃይማኖት ማስገዛት አለብኝ» የሚል ጽኑ ዓላማ የሌለውን ሰው ጾሙ፣ጸሎቱ፣ስግደቱ፣ምጽዋቱ፣ሥርዓተ ቁርባኑ ያሰቅቃልና ክረምት ላልተረዳው ሰው ያስጠላል:: የሚጎዳም ይመስላል:: በማስተዋል ለተረዳው ግን ይወደዳል እንጂ አይጠላም:: ያከብራል እንጂ አይጐዳም:: አባቶቻችን በወርቃማ አነጋገራቸው «ክረምት ሲጠሉት ያከብራል» የሚሉትም ለዚህ ነው:: ሃይማኖትም «በጠባብ በር ግቡ» /ማቴ.7÷13/ ማለትም «አስቀድሱ÷ ደካሞች አትሁኑ» ሲል ላልተረዳው ሥጋዊ ሰው ያስጠላል:: «ጹሙ፣ ከንብረታችሁ መጽውቱ» ሲል የሚጎዳ ይመስላል:: በጥልቀት ለተረዳው ግን ሃይማኖት ያስደስታል፤ ያከብራልም:: «እናንተስ የተከተላችሁኝ /ያመናችሁብኝ/ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብር ዙፋን በሚመጣበት ጊዜ እናንተም ደግሞ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ልትፈርዱ በዐሥራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ::» ማቴ.19÷28:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአስተማረን ከዚህ ቃል እንደ ምንረዳው መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስገኘው ውጤት ክቡር መሆኑን ነው:: የሰው ልጅ ግን ምርጫ ዐያውቅም፤ የሚያከብረውን ይጠላል፤ የሚያዋርደውን ይወዳልና:: በዚህ ዓለም የሚኖር አንድ ባዕለ ጸጋ ሰው ነበር:: ሦስት ወዳጆች ነበሩት:: አንዱን ከራሱ አብልጦ ይወደው ነበር፣ሁለተኛውን እንደ ራሱ አድርጐ ይወደው ነበር:: ሦስተኛውን ግን ከሌሎች አሣንሶ÷ ንቆ አጥቅቶ ይወደው ነበር:: ሦስት ወዳጆች ለነበሩት ለዚህ ባዕለ ጸጋ ሰው የነበረው ሀብት አለቀበት:: የዚህ ዓለም ሀብት ከመታየቱ መጥፋቱ ይፈጥናልና:: የአገሩ ንጉሥ ያውቀው ስለነበር ላግኝህ ብሎ ላከበት፤ እርሱ ግን ከማጣቱ የተነሣ ከንጉሥ ፊት ቀርቶ ከተራ ሰው ፊትም ለብሶ ለመቆም የሚያበቃ ልብስ አልነበረውም:: የነበረው አማራጭ ወደ ወዳጆቹ ሄዶ ለልብስ የሚሆነውን መለመን ነበር:: መጀመሪያ ከራሱ አስበልጦ ወደሚወደው ወዳጁ ሄዶ ያጋጠመውን ነገር ነገረው:: ከራሱ አስበልጦ የሚወደው ወዳጁም «ያለችኝ ይህች ናት» ብሎ ድህው ሰው እንደ ጠበቀው ሳይሆን ትንሽ ሰጥቶ ሰደደው:: እርሱም የማይበቃው መሆኑን ተረድቶ እስኪ ከሁለኛው ወዳጄ ዘንድ ልሂድ ብሎ አስቦ ሄዶም ያጋጠመውን ችግር ነገረው:: እርሱም ላሰበው ነገር የሚሆን ስላልነበረው አልቅሶ አዝኖ ሸኘው:: ከሁለተኛው ወዳጁም



www.eotcmk.org

እንዳልተሳካለት በተገነዘበ ጊዜ አሣንሶ ንቆ አጥቅቶ ከሚወደው ከሦስተኛ ወዳጁ ዘንድ ሄደ:: ይህ ወዳጁም በፈገግታ ፊቱ በመደሰት ተቀብሎ ዛሬስ «እንዴት ወደኔ ልትመጣ ቻልህ» አለው:: «እርሱም ንጉሥ እንገናኝ ብሎ ስለላከብኝ ከእርሱ ዘንድ ስሄድ የምለብሰው ልብስ ስለሌለኝ ብትሰጠኝ ብዬ ነው» አለው:: እርሱም «ለዚህማ ምን ችግር አለ?» ብሎ ችግረኛው ከጠበቀው (ካሰበው) በላይ የሚያስፈልገውን ሰጥቶ ሰደደው:: ከንጉሡም ጋር ያለ ማፈር ተገናኘ::

ይኸውም ምሳሌ ነው:: የመጀመሪያውና ከራሱ አብልጦ የሚወደው የተባለው ገንዘቡ ነው:: ሰው ገንዘብን ከራሱ አብልጦ ከመውደዱ የተነሣ ለገንዘቡ ተላልፎ ሲሞት ይታያልና ከራሱ አብልጦ የሚወደው ወዳጁ ለለመነው ወዳጁ የጠበቀውን ያህል እንዳልሰጠው ሁሉ ከዚህ ዓለም ገንዘብም ሰውን የሚከተለው የከፈን ያህል ብቻ ነውና:: ሁለተኛ እንደ ራሱ አድርጐ ይወደው የነበረው ቤተ ሰብእ /እናት፣አባት፣እኅት፣ወንድም.../ናቸው:: ያ ምንም ላደርግልህ አልችልም ብሎ አዝኖ አልቅሶ እንደ ሸኘው ቤተሰብም /ዘመድም/ አዝኖ አልቅሶ እስከ መቃብር ይሸኛል እንጂ ሌላ የሚያደርገው የለምና:: ሦስተኛውና እንደ ተራ ይመለከተው የነበረው ወዳጁ የተባለው ሃይማኖት ነው:: እንደ ተራ ይመለከተው የነበረው ወዳጁ በደስታ ተቀብሎ ከንጉሡ ፊት ለብሶ የሚቆመውን ልብስ እንደ ሰጠው ሁሉ ሃይማኖትም እንደ ተራ ነገር ሲመለከቱት ሲጠሉት ቆይተው የሚሰጠው ጸጋ እንዳለ በማወቅ ወደ እርሱ ከሄዱ ከሰማያዊ ንጉሥ ከእግዚአብሔር ፊት ለብሰው የሚቆሙትን ልብሰ ጸጋ ያጐናጽፋል:: ስለዚህ የሰው ልጅ ምርጫውን በማስተካከል ያለውን ጥሪት ከሚጨርስበት በጋ ይልቅ ክረምትን÷ ለጊዜው ደስ እያሰኘ ከሚጐዳ ከዓለም ይልቅ የሚጐዳ መስሎ የሚጠቅም፣ የሚያከብር፣ የሚያበለጽግ ሃይማኖትን ወዳጅ ማድረግ ይኖርበታል::

### ከክርስቲያን ምን ይጠበቃል?

ሀ. ፈጣሪውን ማመስገን:– ፍጥረቱ በረኀብ አለንጋ እንዲገረፍ የማይሻ አምላካችን እግዚአብሔር ቸርነቱ ስለሚያራራው ገንዘብ የማይተመንለት ክረምትን ለፍጥረቱ እንዲሁ ይሰጠዋል:: ስለዚህ ይህ ጸጋ በነጻ የታደለው የሰው ልጅ ምስጋና የባሕርይው የሆነ ፈጣሪውን ሊያመሰግነው ይገባል:: «ሥዕው ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ ስብሐት፤ ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕትን ሠዋ::»

መቶ ሁለት መቶ ሰው ቢሰባሰብ አንድ ሄክታር መሬት ማርካት ይቅርና ማረስ የማይችል መሆኑን የሚያውቅ እግዚአብሔር የማጠጫ መሣሪያዎች ሳያስፈልገው በመለኮታዊ ኃይሉ ኢትዮጵያን በቅጽበት ያረካታል:: እንዲህ አድርጐ የሚመግበንን ፈጣሪ ብናመሰግነው ቢያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም:: ቅዱሳን:– «ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን» በማለት የእግዚአብሔርን ስጦታ የሚመጥን÷ ሌላ የሚከፍሉት ውለታ ባለመኖሩ በምስጋና ያጠቃለሉት ለዚህ ነው:: ስለዚህ መዓልትና ሌሊቱን የሚያፈራርቅልን፣ነፋሳትን የሚያነፍስልን፣ በጋና ክረምቱን የሚያመላልስልን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል::

*ለ. ፈጣሪው ባደለው ሀብት መጠቀም ይጠበቅበታል:–* አምላካችን እግዚአብሔር ከሀብት በላይ የሆነ መሠረተ ሀብት ክረምትን ሲሰጠን ዓላማ አለው:: ፍጥረቱ እንዲጠቀምበት ስለሚፈልግ ነው:: ይህን ታላቅ ጸጋ የተቀበለ ሁሉ የወደፊት ተስፋውን ከሩቅ በመመልከት ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል:: «ለወደፊት የሚሆነኝ በቂ ሀብት አለኝ:: በዚህ ክረምት ማረፍ አለብኝ» በማለት በተሰጠው በዚህ ጸጋ የማይጠቀም ሰው ሰነፍ ከመባሉም በላይ በፈጣሪ መጠየቁ አይቀርም:: በፊት የተሰጠውን እየተጠቀመ አዲሱን የእግዚአብሔርን ስጦታ በአኮቴት ሊቀበል ይገባል:: ሉቃ.12÷19:: «አንቺ ነፍሴ ግን ለብዙ ዘመን የሚሆን ብዙ በረከት አለሽ፤ እረፊ÷ ብዪ ጠጪ÷ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ:: እግዚአብሔር ግን አንተ ሰነፍ ዛሬ ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዷት ይሿታል?» በማለት ተቆጥቶታል:: ይህ ሰው ቢኖረው ያለውን እየመጸወተ÷ እግዚአብሔር በሰጠው አካል ተግቶ መሥራት ነበረበትና:: ስለዚህ «መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ» 2ተሰ.3÷13፤ ተብሎ በቅዱሳን ሐዋርያት የተመከረ ሕዝብ የጽድቅ ሥራ መሥራት፣ ትጋትን ገንዘቡ አድርጐ ተግባሩን ማከናወን መሥራት ይጠበቅበታል:: እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ በሚገባ ተጠቅሞበት የሚሠራ ሰው ራሱን፣ቤተሰቡን ከመርዳት አልፎ ነዳያንን መርዳት ለቤተ ክርስቲያንም ዘቢብ፣ዕጣን፣መብራት...ወዘተ መስጠት ይችላል:: በዚህም ታላቁን ሀብት ልምላሜ ገነትን ያገኛል:: ለዚህ ነው ነቢዩ ሰሎሞን፤ «ለሰው የከበረ ሀብቱ ትጋቱ» ያለው:: በተቃራኒው ስንፍናን ገንዘቡ አድርጐ ፈጣሪው በሰጠው ጸጋ የማይጠቀም ሰው ደግሞ ችግረኞችን መርዳቱ ይቅርና እርሱና ቤተሰቡም በችግር ባሕር የተዋጡ ችግረኞች ይሆናሉ:: ሰነፍ ነውና ጨካኝ÷ የቤተሰቦቹ መቸገርም አያሳዝነውም::

*«ጭቃውን ፈራና ክረምት እንዳይሠራ ልጆቹ ቢያለቅሱ በጅብ አስፈራራ»*

እንዲሉ ስንፍና ከዚህ ደረጃ የሚያደርስ በሽታ ነውና ልናስወግደው ይገባል::

ስለዚህ ፈጣሪያችን የሰጠንን ክረምት ተጠቅመን ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ሕይወት መሠረት የሆኑ ተግባራትን ተግተን መሥራት ይኖርብናል:: ካልሠሩ አያገኙምና ካላገኙ አይመጸውቱም፤ ካልመጸወቱ ክብር የለምና::

ሐ. ጸሎት:– ዘወትር ጉድለት የሚስማማው ፍጥረት በተሰጠው ነገር ሊያመሰግን ያልተሰጠውን ለማግኘት ጸግሞ ሊጸልይ /ሊለምን/ ይገባዋል፤ ይህን ያደርግ ዘንድ ፈጣሪው አዝዞታልና:: «ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችኋል» የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና በማለት:: ማቴ.7÷7:: የሰው ልጅ ከቤት ያለውን ዘር አውጥቶ ለመሬት አደራ የሚሰጠው «ለወደፊት የበለጠ አገኛለሁ» የሚል ተስፋ ስላለው ነው:: ነገር ግን ተስፋ ማድረጉ ብቻ በቂ አይደለም:: ሰው በጸሎት መታገዝ ይኖርበታል እንጂ ምድር የዘሩባትን እንድታበቅል፣የበቀለው እንዲያድግ፣እንዲያብብ 30፣90፣100 ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርግ ፈጣሪ ብቻ ነው:: «ለምኑ ታገኛላችሁ» ያለን ፈጣሪዋም የአገራችንን ጸሎቷን ሰምቶ ከሌሎች ሀገራት በተለየ ሁኔታ በወራቱ ገብቶ በወራቱ ይወጣል:: ለቀሪ ሕይወታችን ዋስትና ያለው ክረምት ነው:: ይህም ቤተ ክርስቲያናችን በቅዳሴ ጊዜ ሥርዓት አድርጋ የምትጸልየው የጸሎቷ ውጤት መሆኑን ልብ ልንለው ይገባናል:: ስለዚህ ክረምቱን የሰላም እንዲያደርግልን ÷ አዝርዕቱን፣አትክልቱን ከናዳ ከበረዶ እንዲጠብቅልን ÷ «ዝናም እናወርዳለን ÷ በረድ እናቆማለን» ከሚሉና የሰይጣን ማደሪያ ከሆኑ ቃልቻና ጠንቋይ ዘንድ ከመሄድ ይልቅ የሁሉ ባለቤት የሆነ እግዚአብሔርን በጸሎት መማፀን ይኖርብናል:: «ዝናም እንዳይወርድ ሰማያቱን ወይም ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ባዝዘው ወይም በሕዝብ ላይ ቸነፈር ብሰድ በስሜ የተጠሩ ሕዝቤ /ክርስቲያኖች/ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ÷ ፊቴንም ቢፈልጉ÷ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ÷ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ ይላልና::» 2ዜና.መዋ.7÷13:: ለመልካም ሥራ ተነሣሽነትን÷ የሰላምና የጤና ክረምትን÷ለአገራችን ፍቅር አንድነትን እንዲያድለን የአምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን:: የእግዚአብሔር ቸርነት÷የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን:: አሜን::



www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

መምህር ደጀኔ ሽፈራው

*መምህር ደጀኔ ባለፈው እትም የቅዳሴን ምንነት በአጭሩ ካቀረቡልን በኋላ የቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ አገልግሎት ሦስት ክፍሎች ያሉት መሆኑን በመግለጽ፤ የመጀመሪያውን ማለትም ግብዓተ መንጦላዕት /የዝግጅት ቅዳሴ/ የተሰኘውን ክፍልና በዚህ ጊዜ የሚደረጉትን ጸሎቶች ከተያዘው ርዕስ አንጻር በዝርዝር ተንትነውልናል:: በመቀጠልም በዚሁ የዝግጅት ክፍል ካህኑ ለቅዳሴው ሥርዓት ማከናወኛ የሚሆኑትን ንዋየ ቅድሳት እያለበሰና አልብሶም ከጨረሰ በኋላ የሚጸልየውን ጸሎትና የሚፈጽመውን ሥርዓት ከነትንታኔው አቅርበውልናል:: በዚህ እትም ደግሞ ቀጣዩን ትምህርት ያቀርቡልናል:: ተከታተሏቸው::*

## 4.1 የሥጋ ወደሙ ዝግጅት

የአዲስ ኪዳን ቁርባን የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው:: ይኸንን ሥርዓተ ቁርባን ሠርቶ ያሳየ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በዚህም ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን አሳይቷቸዋል:: ይኸውም:- «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፤ አለ:: ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህ አለ:– ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::» በሚለው ታውቋል:: ማቴ.26÷27–29:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብናያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ ቈርሶም እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ:: እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ:- ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን የአዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት» አለ:: ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና:: ማለቱ:: እዚህ ላይ ይኸንን የአዲስ ኪዳን ቁርባን ምሥጢር ባስተማራቸው ጊዜ:- «ይኸንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት::» ማለቱ:: ሥጋውን በበላችሁ ደሙንም በጠጣችሁ ጊዜ መከራ መስቀሉን ታስባላችሁ ነገረ መስቀሉን ትናገራላችሁ የሚለውን ምሥጢር ለማምጣት እንጂ ኅብስቱና ወይኑ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ መታሰቢያ ነው ማለቱ አይደለም:: ሐዋርያዊው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን ያውቃል÷ ያምናልም:: ለዚህም ነው:– «ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት:: ሰው ግን ራሱን ይፈትን÷እንዲሁም ከኅብስቱ ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለ ማይለይ (አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ብሎ ስላላመነ) ለራሱ ፍርድ ይበላልና÷ ይጠጣልምና::» ያለው:: 1ኛቆሮ.11÷23–30:: ከዚህም ጋር «በቆረባችው ጊዜ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፤» ማለቱ በራሱ በቂ መልስ ነው::

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳንን ቁርባን ከማስተማሩ በፊትም :– «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ ከእኔ ጋር አድን ሆኖ ይኖራል እኔም በእርሱ አኖራለሁ በጸጋ ተዋሕጄው እኖራለሁ::» ብሏል:: ዮሐ.6÷53–56:: ይህ የጌታችን ቃል የሚያስተምረን ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት÷ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን ነው:: ስለዚህ ሕይወት የሚሆነውን÷ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃውን÷ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገውን የአዲስ ኪዳን ቁርባን «መታሰቢያ ነው» ማለት አይገባም::

እንግዲህ ከዚህ ተነሥተን ነውበሥርዓተ ቅዳሴው ያለውን የሥርዓተ ቁርባን አዘገጃጀት የምንመለከተው::

### 4.1.ሀ የኅብስቱ ዝግጅት

ኅብስቱ የሚዘጋጀው ከስንዴ ብቻ ነው:: ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን በስንዴ እንደ ሰጠን ለማጠየቅ:– «የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ (የሚሰቀልበት ጊዜ) ሰዓቱ ደርሷል:: እውነት እውነት እላችኋለሁ÷የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች::» ብሏልና:: ዮሐ.12÷24–25:: በዚህም ራሱ በስንዴ ቅንጣት መስሎ ተናግሯል:: እዚህ ላይ መከራ መስቀሉን ክብር ያለው እኛ ስለምንከብርበት ነው:: ከዚህም ሌላ:- «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤» ዮሐ.8÷12 ካለ በኋላ ደቀ መዛሙርቱንም «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሏቸዋል:: ማቴ.5÷14:: ልክ እንደዚሁ እርሱ ስንዴ ስለሆነ ነው ጻድቃንን በስንዴ አዝመራ የመሰላቸው:: «ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ፤» እንዲል:: ማቴ. 13÷30:: በትንቢትም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «እህልም የሰውን ጉልበት ያጠነክራል::» ብሏል:: መዝ. 103÷15:: ነቢዩ እህል ያለው ስንዴን ነው:: ምሥጢሩም የክርስቶስ ስንዴ ሥጋው÷ጽንዓ ነፍስን ይሰጣል (ነፍስን ፈጽሞ ያጸናታል)፤ ማለት ነው::

እንግዲህ ባለፈው ለመግለጥ እንደ ሞከርነው በሚገባ ተፈትጐ ከረቀቀ ስንዴ በዕለተ እሑድ አራት ኅብስት ይዘጋጃል:: ይህም በዕለተ እሑድ:- 1ኛ/ ጌታ 2ኛ/ ስምዖን ጴጥሮስ 3ኛ/ ዮሐንስ 4ኛ/ ያዕቆብ በደብረ ታቦር የመገኘታቸው ምሳሌ ነው:: በዚህ ምሳሌ መሠረት በደብረ ታቦር ከተገኙት ከአራቱ መካከል አንደኛው ጌታ ለድኅነተ ምእመናን እንደ ተሰቀለ÷ ከአራቱ ኅብስትም አንዱ ለሕይወተ ምእመናን ይፈተታል:: በሌሎች ቀናት ሲሆን ደግሞ ሦስት ኅብስት ይዘጋጃል:: ይህም አንዱ የጌታ ምሳሌ ሲሆን ሁለቱ ደግሞ በጌታ ግራና ቀኝ ለተሰቀሉ ወንበዴዎች ምሳሌ ናቸው::

ስንዴው መፈተጉ ለክርስቶስ መከራ ምሳሌ ነው:: ከዚህ ሌላ ኅብስቱ በሚዘጋጅበት ጊዜ ዐሥራ ሦስት ክፍል ባለው የመስቀል ቅርጽ ይታተማል:: ይህም ጌታ ለድኅነተ ምእመናን ዐሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል በፈቃዱ እንደ ተቀበለ የሚያጠይቅ ነው::





www.eotcmk.org

## 4.1.ለ የወይኑ ዝግጅት

ደሙ የሚዘጋጀው ከወይን ነው:: ይኸንንም ያደረገው ጌታችን ነው:: ደሙን በወይን እንደ ሰጠን ለማጠየቅም:– «እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤» ብሏል:: ዮሐ.15÷1:: ስለ ወይን በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ተብሏል::

የወይን ጠጅ ለማውጣት የወይን ፍሬ በመጥመቂያ ውስጥ ይረገጣል:: ኢሳ.16÷10፤ አሞ.9÷13:: ይህ ወይን በመጥመቂያ ውስጥ መረረጡ ወይም መታሸቱ ክርስቶስ በዚህ ዓለም መከራ ለመቀበሉ ምሳሌ ነው:: የወይን ፍሬ በመጥመቂያ ውስጥ እንደሚረገጥ:– ጌታችንንም በአንገቱ ገመድ አስገብተው÷ መስቀል አሸክመው÷ ከፊት ከኋላ÷ ከግራ ከቀኝ እየጐተቱ ወደ ቀራንዮ ሲወስዱት በአፍጢሙ ሲደፉ ጀርባውን÷በጀርባው ሲወድቅ ደግሞ ደረቱን ረግጠውታል:: ፊረስ በቅሎውንም ነድተውበታል::

የደረቀ የወይን ፍሬ (ዘቢብ) ለምግብ ይሆናል:: 1ኛ ሳሙ.25÷18:: እንደ ወይን መድረቅ በመስቀል ላይ የሞተልን ክርስቶስ:– «ሥጋዬን ብሉ÷ ደሜንም ጠጡ፤» በማለት ምግበ ሕይወት ሆኖልናል::

የወይን ብዛት የእግዚአብሔር በረከት ምልክት ነው:: ለዚህም ነው ይስሐቅ ያዕቆብን:– «እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ::» በማለት የመረቀው:: ዘፍ.27÷28:: በዚህም ዓለም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ተወግዶ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ለማግኘታችን ምልክቱ የአምላክ ሰው ሆኖ ከድንግል ማርያም መወለድ ነው:: «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል÷እነሆ ድንግል ትፀንሳለች÷ ወንድ ልጅም ትወል ዳለች÷ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች::» እንዲል:: ኢሳ.7÷14:: እርሱም በረከትን በልግሥና የሚሰጥ የበረከተ ሥጋ የበረከተ ነፍስ ጌታ ነው:: መንፈስ ቅዱስ አድሮባት የሚኖር ቅድስት ኤልሳቤጥ:– «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ÷የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው::» እንዳለች:: ሉቃ.1÷42::

በብሉይ ኪዳን ወይን መሥዋዕት ሆኖ ይቀርብ ነበር:: «ለመጠጥ ቁርባን የወይን ጠጅ ታቀርባለህ::» እንዲል:: ዘዳ.29÷40:: የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት ደግሞ ክርስቶስ ነው:: የመጠጡም ቁርባን ደሙ ነው:: «ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ፤ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::» እንዲል:: ማቴ.26÷27:: ጌታችን የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት በመሆኑ ነው÷ መጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስ ደጋግሞ:– «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤» በማለት ስለ ክርስቶስ የመሰከረው:: ዮሐ.1÷29–30:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ፋሲካችን (ψመሥዋዕቱ በግ) ክርስቶስ ታርዶአልና (በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶልና ልና÷ ደሙንም አፍስሶልናልና)፤» ብሏል:: 1ኛ ቆሮ.5÷7:: በተጨማሪም በዕብራውያን መልእክቱ ላይ:– «አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ (5500 ዘመን ሲፈጸም) ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገል ጧል::» ብሏል:: ዕብ.9÷26:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ :– «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን÷ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ::» ብሏል:: 1ኛ ጴጥ. 1÷18–19::

ወይን ሰውን ደስ ያሰኛል:: ይኸንን በተመለከተ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት:– «ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፤» ብሏል:: ይህም ስለ ክርስቶስ ደም የተነገረ ቃለ ትንቢት ነው:: በመስቀል ላይ የሚፈሰው የክርስቶስ ደም ሰውን ደስ ያሰኛል ማለት ነው:: ምክንያቱም የአዳምና የልጆቹ ሐዘን ወደ ደስታ የተለወጠው ወይን በተባለ በክርስቶስ ደም ነውና:: ጠቢቡ ሰሎሞንም:– «ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፤ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት፤ ይጠጣ÷ ድኅነቱንም ይርሳ÷ ጉስቁልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ::» ብሏል:: በዚህም ቃለ ትንቢት «ለጥፋት ለቀረበው ሰው÷ነፍሱ የመረረው» የተባለ አዳም ነው:: ምክንያቱም በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ÷በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተጨምሮ ተፈርዶበት ወደ ሲዖል ወርዶ ስለነበረ ነው:: «ወይን ይጠጣ» የተባለው ደግሞ የክርስቶስን ደም ይጠጣ ማለት ነው::

*ወይን ሰውን ደስ ያሰኛል:: ይኸንን በተመለከተ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት:– «ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፤» ብሏል:: ይህም ስለ ክርስቶስ ደም የተነገረ ቃለ ትንቢት ነው:: በመስቀል ላይ የሚፈሰው የክርስቶስ ደም ሰውን ደስ ያሰኛል ማለት ነው:: ምክንያቱም የአዳምና የልጆቹ ሐዘን ወደ ደስታ የተለወጠው ወይን በተባለ በክርስቶስ ደም ነውና:: ጠቢቡ ሰሎሞንም:– «ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፤ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት፤ ይጠጣ÷ ድኅነቱንም ይርሳ÷ ጉስቁልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ::» ብሏል::*

በተጨማሪም በመጽሐፈ መክብብ ላይ:- «እንጀራን ለሳቅ /ለደስታ/ የወይን ጠጅንም ለሕይወት ደስታ ያደርጉታል::» ብሏል:: መክ..10÷19:: በዚህ ንባብ እንጀራ ያለው የክርስቶስን ሥጋውን ነው:: ይኸንንም ራሱ ባለቤቱ:- «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ:: አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ÷ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው:: ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::» ብሏል:: ዮሐ.6÷51:: የወይን ጠጅ የተባለው ደግሞ የክርስቶስ ደም ነው:: «ለሕይወት ደስታ ያደርጉታል፤» ማለቱም:- ወይን የተባ ለው የክርስቶስ ደም ከሞት ወደ ሕይ ወት ማሸጋገሩን÷ ሐዘንን ወደ ደስታ መለወጡን የሚያመለክት ነው::

ወይን መድኃኒት ይሆናል:: ይኸንንም ጌታችን በምሳሌ ካስተማረው ትምህርት እንገነዘባለን:: «አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ÷ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት÷ ደበደቡትም÷ በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ:: ... አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ፤ አይቶም አዘነለት÷ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው÷ በራሱ አህያም ላይ



www.eotcmk.org

አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደሪያ ወሰደው፥ ጠበ ቀውም:: በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፡- ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው::» ይላል:: በዚህ ጽሑፍ፡- «አንድ ሰው በወን በዴዎች እጅ ወድቆ ቆሰለ፤» የተባለው አዳም ነው:: «ወንበዴዎች» የተባሉት አጋንንት ናቸው:: «አይቶ አዘነለት፥ ቀርቦም ዘይትና ወይን በቊስሎቹ ላይ አፈሰሰለት፤» የተባለው ጌታ ነው:: ይህም አዳምን ከቊስለ ኃጢአቱ ለመፈወስ ወይን የተባለ ደሙን በመስቀል ላይ ማፍሰሱን ያመለክታል:: «የእንግዶች ማደሪያ» የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ናት:: «ሁለት ዲናር የተቀበለው» ደግሞ ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የተሰጣቸው መምህራን ናቸው:: «ከዚህ በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ::» ማለቱ ደግሞ መምህራን ሁለቱና ዲናር /ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳንን/ መሠረት አድርገው ገድላትን፥ ድርሳናትን፥ ተኣምራትን እየጻፉ ቢያስተምሩበት በዕለተ ምጽአት ዋጋ እንዳላቸው የሚገልጽ ኃይለ ቃል ነው:: ሉቃ.10፥

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በመንፈሳዊ ትምህርት ለወለደው ለልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፡- «ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ::» ብሎታል:: 1ኛጢሞ.5፥23:: በዚህም ወይንና ውኃ ቀላቅሎ እንዲጠጣ መክሮታል:: በሽታው የአፍአ ሳይሆን የውስጥ ነበርና:: የአዳምም ኃጢአት የአፍአ ሳይሆን የውስጥ ነበር:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የአፍአው ኃጢአት በጸሎትና በእንስሳት መሥዋዕት ይሰረይ ነበር:: ዘሌ.16፥20-22:: የውስጥን ኃጢአት ያስተሠረየ መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ስለዚህ ወይን ለጢሞቴዎስ የውስጥ በሽታ መድኃኒት እንደ ሆነው ሁሉ የውስጥ ኃጢአት ለተባለ ለአዳም ኃጢአትም መድኃኒት የሆነው ወይን የተባለ የክርስቶስ ደም ነው::

እንግዲህ የክርስቶስ ደሙ በወይን መሰጠቱ በዚህ ሁሉ ምክን ያት መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል:: ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት እንደ ሚሆን ማመን ይገባል:: ዲያቆኑ ወይን ደሙን እየጸለየ በሚያ ዘጋጅበት ጊዜ ማስተዋል አለበት:: ይኸውም ወይኑ ወፍ ያልመጠጠው፥ በጊዜው የደረሰ መሆኑን ነው:: ምክንያቱም ጌታ ሰው የሆነው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በጊዜው ነውና:: ይኸንንም ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- « ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ /አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም/ እግዚአብሔር ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድ ልጁን ላከ፥ ከድን ግልም ተወለደ፤» ብሏል:: ገላ.4፥4::

ዲያቆኑ በጊዜው የደረሰውን ወይን ለደሙ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሁለት እጅ ወይን አንድ እጅ ውኃ ያደርጋል:: ይህም ሁለት ሦስተኛው (2/3) ወይን አንድ ሦስተኛው (1/3) ውኃ ይሆናል ማለት ነው:: ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው:: ሁለት እጅ ወይን መሆኑ ሁለት ጊዜ ደሙን እንዳፈሰሰልን ያጠይቃል:: ይኸውም አንደኛው ከመሞቱ በፊት ሲሆን ሁለተኛውም ከሞተ በኋላ ጎኑን በጦር በተወጋ ጊዜ የፈሰሰውን ትኩስ ደም ያመለክታል:: አንድ እጅ ውኃ መሆኑ ደግሞ አንድ ጊዜ ከጐኑ ከደሙ ጋር ውኃ መፍሰሱን ያመለክታል::

የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚዘጋጀው በቤተልሔም ነው:: ከዚህ በኋላ ቄሱና ዲያቆናቱ በመሶበ ወርቅ እና በጽዋ አክብረው፥ በጸሎት በማዕጠንት ወደ ቤተ መቅደስ ያመጡታል:: ይህም በቤተ ልሔም የተወለደ፡ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኅነተ ምእመናን፡- ቅዱስ ሥጋውን ለመቁረስ ክቡር ደሙን ለማፍሰስ ወደ ቀራንዮ መሄዱን ያመለክታል:: በዚህን ጊዜ ቄሱ፡- «ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም:: የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ፥ የዓለምን በደል የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ፤» የሚለውን ኃይለ ቃል ይናገራል:: ይህም የንስሐ መምህር የሆነ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ስብከት ነው:: ዮሐ.1፥29:: ዲያቆኑም ቃጭል ያቃጭላል፥ ደውልም ይመታል:: ይህም የብሥራተ ገብርኤል ምሳሌ ነው፤ አንድም የስብከተ ዮሐንስ ምሳሌ ነው፤ አንድም እመቤታችን በስደቱ ጊዜ ላለቀሰችው ልቅሶ ምሳሌ ነው:: ይኸውም ከትዕማን ደጅ ቆማ በለመነች ጊዜ ክፉ ቃል ተናግረው፥ ልጁዋን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመሬት ጥለው አሳዝነዋታልና ነው::

ቄሱና ዲያቆናቱ ዕለተ ሰንበት ሲሆን ፡- «ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ፥ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ፤ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር፥ ይፈልጠኒኑ እምሕዝቡ:: እውነትን የሚያደርግ ሁሉ ሰንበትንም የሚያከብር ጻድቅ ነው:: ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ መጻተኛ ከሕዝቡ ይለየኝ ይሆንን? አይጠበል::» የሚለውን፥ በዕለተ ቀዳሚት፣ ረቡዕና ዓርብ ሲሆን፡- «መስቀል አብርሀ በከዋክብት አሠ ርገወ ሰማየ፥ እምኵሉሰ ፀሐየ አር አየ፤ መስቀል አበራ፥ ሰማይን በከዋክብት ሸለመ፥ /አስጌጠ/፥ ከሁሉም ይልቅ ፀሐይን አሳየ፤» የሚለውን፥ በዘወትር ሲሆን «እምነ በሐ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርጉት ዐሬፋቲሃ በዕንቈጳዝዮን፤ እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንልሻለን፥ ግድግዳዎቿ በጳዝዮን ዕንቊ ያጌጠች ናት፤» የሚለውን፥ በዓለ ኀምሣ ሲሆን ደግሞ «ሃሌ ሉያ፥ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ በሰንዱናት ለዘተንሥአ እሙታን በመንክር ኪን፤ ሃሌ ሉያ በሚያስደንቅ ምሥጢር ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ኢየሱስን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ ገነዙት፤» የሚለውን እያዜሙ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘልቃሉ::

ይቀጥላል


**አዲስ መጽሐፍ**
**በገበያ ላይ**

"420 ጥያቄና መልሶቻቸው"
አሳታሚና አከፋፋይ፡-

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ስልክ 23-45-29/22-86-01/13-81-30

ትምህርተ ሃይማትና ትምህርተ ክርስትና መጽሐፍን አንብበው መንፈሳዊ እውቀትን ይሸምቱ !!

**ለአዋሳ እና አካባቢው ነዋሪዎች እንኳን ደስ አላችሁ !!**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
አዋሳ ቅርንጫፍ አቡነ ጎርጎርዮስ አጸደ ሕፃናት
ከNursery እስከ Upper KG ለማስተማር ምዝገባ ጀመረ !!
ልጅዎን በሥነ ምግባር ለማነፅ ይላኩ !!
ስልክ (06) 20-48-99 (09)827976
ማኅበረ ቅዱሳን




www.eotcmk.org

እርሱን ለማየት ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ ድምፁን ከፍ አድርጐ እንዲህ አላቸው:- «እኔ ይህን ሥቃይ የታገሥኩትና በልቤም ልቀበለው የተዘጋጀሁት የክብር ባለቤት በሆነ በጌታዬ በፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ተስቤ ነው:: አሁንም እነዚህ አንበሶች እንደ ስንዴ ይፈጩኝ ዘንድ ነፍሴ ወደደች፤ የክብር ባለቤት ወደ ሆነው ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ልትሔድ ነፍሴ ሽታለችና» አላቸው::

አላዊው ንጉሥ የቅዱስ አግናጥዮስን የጽናት ንግግር በሰማ ጊዜ አደነቀ:: በልቡም ፍርሀት አደረበት:: እንዲህም አለ:- «እነዚህ ክርስቲያኖች ትዕግሥታቸው ምን የበዛ? ከኔ ወገን እንዲህ ያለ ጣዖት አምላኪ የሚታገስ ማን አለ» በማለት ተናገረ::

እነዚያ የተለቀቁት አንበሶች ወደ ቅዱሱ በቀረቡ ጊዜ ደንግጠው ቆሙ:: አንዱ፤ አንበሳ እጁን ዘርግቶ ያዘው፤ ቅዱሱም ደስ ብሎት ነፍሱን በፈጣሪው ክርስቶስ እጅ ሰጠ፤ ልመናውን ተቀብሎ ፈጽሞለታልና:: ነገር ግን የተራቡ አንበሳች እንደ ማንኛውም ሰው የቅዱሱን ሥጋ ሊበላ ይዳስሱት ዘንድ አልተቻላቸውም፤ እስከ ምጽአት ተጠብቆ ይኖር ዘንድ ከከተማው ውጪ ቀበሩት::

## ቅዱስ አግናጥዮስ ስለ ምስጢረ ሥላሴ የተናገረው አንቀጽ

ስለ አንድነት ሦስትነት ሲያብራራ በህልውና፣ በባሕርይ፣ በመለኮት አንድ የሆነ እግዚአብሔር ሦስትነቱ በስም በአካል በግብር የሚሠለስ የሚቀደስ የዘለዓለም አምላክን እንደ ሚከተለው ይገልጸዋል:-

«ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ ሹመትና መዓርግ መስጠት የሚቻለው በመልክ በገጽ ፍጹም በሚሆን በሦስት አካል በጌትነቱ ዙፋን ተቀምጦ ሁሉን የሚገዛ ነው» በማለት ፍጥረቱን ሿሚ ሽሳሚ የሆነው አምላክ በአንድነት በሦስትነት ፈጥሮ የሚገዛ መሆኑን ያመለክተናል:: በዚህም ትምህርቱ ነቢዩ ኢሳይያስን ይመስለዋል:: እንዲህ እንዳለ:- «እግዚአብሔርን በረጅም ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት..... እንዲሁም ለአንዱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች....» ኢሳ 6፥1-3 በማለት እንደገለጸው:: /ሃይ. አበ.11÷1/::

ይህም ሦስትነት አንድ ሥልጣን እንዳለው ቅዱስ አግናጥዮስ በትምህርቱ እንደ ሚከተለው ይገልጠዋል::

«አንዲት አገዛዝ፣ አንዲት ፈቃድ፣አንዲት ኃይል፣ አንዲት መንግሥት፣ አንዲት ስግደት፣ አንዲት ምስጋና፣አንዲት ክብር፣ አንድ ጽንዕ ቅድስት ለሥላሴ ይገባል፤ አንዲት ምክር፣ አንዲት ሥልጣን፣ አንድ ክብር፣ አንድ ጽንዕ፣ አንድ አኗኗር፣አንድ ፈቃድ ለሥሉስ ቅዱስ ነው:: ይህም ትምህርቱ «እስራኤል ሆይ÷ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው::» እንዳለ ዘዳ.፮፥፬:: ከብሉይ ኪዳን የተስተካከለ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ:- «አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት» /ኤፌ. 4፥5/ እንዳለ::

ይህ አባት በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ያለውን የህልውና ትምህርት «አብርሃም በሚያደርገው አገልግሎት በአንድነት በሦስትነት ሲያነጋግር እንዲስተዋል ሁሉ እርሱም « በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው እንደ ሆነ እናምናለን፤ ይህች ሦስትነት የተካከለች ናት» በማለት ያስረዳናል::

በዚሁ ትምህርቱ ቅዱስ አግናጥዮስ የአካል፣ የስም፣ የግብር ሦስትነት እንዳይፋለስ፤ ዐላዋቂዎች አይሁድ መናፍቃን «እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው» የሚሉትን ትምህርታቸውን ያፈርስባቸዋል:: ሦስትነት በአንድነት፤ አንድነት በሦስትነት ጸንቶ እንደ ሚኖር ሳይረዱ፣ አንድነት ሦስትነቱን ሲገልጽ:- «አብም አብ ነው እንጂ ወልድን መንፈስ ቅዱስን አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ አብን ወልድን አይደለም::» በማለት የአካል፣ የስም ተፋልሶ በቅድስት ሥላሴ ዘንድ እንደሌለ በትምህርቱ አብራርቷል::

በተጨማሪም የአካል፣ የግብር ውላጤ እንደ ሌላቸውም መናፍቃን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ሳይጠረዱና ሳይገባቸው «የአካላት ፍልሰት አለ» ለሚሉ የማያዳግም የትምህርቱን ኃይለ ቃል እንዲህ በማለት ገልጾታል:: «አብ÷ ወልድን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን አይለወጥም፤ ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን፣ መንፈስ ቅዱስም÷ አብን ወልድን ወደ መሆን አይለወጥም::» ከዚህ ኃይለ ቃልም የምንረዳው ይህ ቅዱስ ሊያብራራ የፈለገው አብ በተለየ ስሙ በተለየ አካሉ በተለየ ግብሩ ቅድመ ዓለም የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር፣ ስሙ፣ ግብሩ፣ አካሉ ወደ ወልድነትና መንፈስ ቅዱስነት የማይለወጥና ፍልሰት የሌለበት መሆኑን እንዲሁም ወልድና መንፈስ ቅዱስ በስም በግብራቸው ያለ ተለውጦ ጸንተው እንደሚኖሩ ያስረዳናል::

ነገር ግን ከላይ እንደ ገለጽነው ሦስትነታቸውን በጠቀሰ ቁጥር አንድነታቸውን ሳይገልጽ አያልፍም::

«እኚህ ሦስቱ አካላት በጌትነት በክብር ፍጹማን ናቸው፤ በአንድ መለኮት አንድነትም አንድ ናቸው» እያለ በተጨማሪም:- «ይኸውም ሦስትነት ከእርሱ የሚገኝ አንድ ብርሃን ነው፤ በዓለሙ ሁሉ ምሉዕ ነው፤ ከምድርም በታች ላሉት ያበራል:: በሰማይም በምድርም ምሉዕ ነው» በነቢዩ ኢሳይያስ:- «በሲኦልም ያሉ ጌትነቴን አዩ» ኢሳ. 66፥1-3 ተብሎ እንደ ተጻፈ በማለት የእግዚአብሔር አንድነትን በሦስትነት ያለ አንድ ብርሃን ነው፤ ብርሃኑም በሁሉም ምሉዕ መሆኑን በመግለጽ እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ እንደ ሆነ በብርሃን ምሳሌ ያስረዳናል::

## 2. ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ የተናገረው አንቀጽ

ይህ አባት በሃይማኖተ አበው ምዕራፍ 11ና 12 ላይ በገለጠው ትምህርቱ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ባደረ ጊዜ፤ ይህም ቃል ከሥጋ ተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሆነው ወልድ እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ እንዳልሆኑ እንዲህ ይገልጠዋል:- «ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል በእመቤታችን ማኅፀን አደረ፤ ስለ መለኮት ተዋሕዶ በዚህ የምንናገርም በወልድ ያለውን ነው:: ስለ አብ ስለ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ፍጹም አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ለመሆን በድንግል ማኅፀን አደሩ አንልም:: ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ብቻ ከእርሷ ተወለደ እንላለን እንጂ» እያለ ያብራራዋል::

በ ት ም ህ ር ቱ ም እ ነ ልዮናውያንን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ የሚሉትን ትምህርታቸውን ያፈርስባቸዋል:: ዕድል ፈንታቸውን ከከሐድያን አይሁድ መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልጽባቸዋል:- «ወልድ ዋሕድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከፍሉት፤ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሲሆን በኋላ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ የሚያደርጉት፤ ሰው ስትሆን ራስህን እግዚአብሔርን ታደርጋለህና ስለ መሳደብህ ነው እንጂ ስለ በጎ ሥራህ ልንጣላህ የምንወድ አይደለም» ብለው በዐመፃቸው ከሚናገሩ፣ አምላክን ከሰቀሉ ከአይሁድ ጋር ይቈጠራሉ:: እንዲሁም:- «በወልደ እግዚአብሔር ድካም ሕጸጽ አለበት» «የሚሉ ሁለት ባሕርይ፣ ሁለት አካል የሚያደርጉትም ዕድል ፈንታቸው ከከሀድያን



www.eotcmk.org

ከመናፍቃን ጋር የተካከለ ነው» በ ማለት ከርትዕት እምነት የተለዩ መሆናቸውን ይገልፅባቸዋል::

ቅዱስ አግናጥዮስ በዘመኑ የነበሩ÷ የእግዚአብሔር ጠላቶች ተብለው የሚጠሩ መናፍቃንን በጥቅል ስማቸው «ታአማኅሊስ»ን ትምህርታቸውን ይነቅፍባቸዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ እንደ መሆኑ እርሱ ባወቀው ከድንግል ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ የተዋሐደውን እነርሱ ለይተው ተዋሕዶው ነፍስ የሌለው እንደ ሆነ፣ መለኮትም ስለ ነፍስ ፈንታ እንደ ሆነው ይናገራሉና:: እርሱም ወንጌልን ጠቅሶ የወልደ እግዚአብሔር ተዋሕዶ ቃል ከሥጋ፣ ከነፍስ ጋር እንደ ሆነ እንደ ሚከተለው ሐሳባቸውን ይገስባቸዋል:- « በውኑ መለኮት ከሥጋ ፈጽሞ ተለየን? ሥጋስ ለዘለዓለም ፈርሶ በስብሶ ቀረን? ነፍስ አልነሳም የሚል እንዲህም የሚክድ ሰው ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ አዘነች ያለውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ሰምቶ እንዲህ ይፈር፤ አቤቱ ይህን መናገሩ በማን ላይ ነው? በኛስ አይደለም፤ በሚጠፉት ወገኖች ላይ ነው እንጂ» በማለት በማስረጃ ገልጾታል::

ይህ አባት ጌታችን በምድር ላይ በተዋሕዶ መገለጹን፤ ከኃጢአት በቀር ለሰው ልጅ የሚገባውን እንዳከናወነ እንዲህ ይላል:- «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ተወለደ፤ በእውነት አደገ፤ በእውነት በላ ጠጣ፤ በእውነት ተሰቀለ፤ በእውነት ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ::» ካለ በኋላ:- «ይህን በፈቃዱ ያደረገ እርሱ ለሌለው ሰጪ አድራጊ ነው:: በመስቀል የተሰቀለ፤ ኃጢአትንም ይቅር የሚል እርሱ ነው:: በመቃብር ያደረ፣ ሙታንንም የሚያነሣ እርሱ ነው:: ከመቃብር አፍአ ነው፤ ከመቃብርም ሰበኑን /መግነዙን/ ትቶ ተነሣ፤ እርሱ ሐዋርያት ወደ አሉበት በዝግ ደጅ ገብቶ ሰላምን ሰጣቸው» ይለናል::

«መለኮት በባሕርዩ ታመመ» ለሚሉትም፤ «መለኮት በባሕርዩ ታመመ÷ ሞተ» የምትል አንተ የኛን ነገር ሰምተህ እፈር፤ እኛ ግን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን ሰው እንደ መሆኑ በሥጋ እንደ ታመመ፤ በመለኮት እንዳልታመመ እናምናለን:: በሥጋ ሞተ፤ በመለኮት አልሞተም:: እግዚአብሔር ቃል ስለ እኛ እንደ ታመመ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ቤዛ ሆኖ እንደ ሞተ ብትሰማ እኛ መለኮትን ከትስብእት ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ አድርገን ለእግዚአብሔርነቱ በሚገባ በዚህ አንድ ስም ክርስቶስ በሚል እንድ ንጠራው እወቅ» እያለ ሐሳባቸውን ያፈርስባቸዋል::

ይህ አባት ለዚህም ትምህርተ የሰውን ልጅ በምሳሌነት አቅርቦ ለትምህርቱ ማብራሪያ ይሰጣል:: የሰው ልጅ ከሁለት ባሕርያት: - ከባሕርየ ሥጋና ከባሕርየ ነፍስ ተሠርቶ አንድ ባሕርይ አንድ ስም ተሰጥቶት ይኖራል:: አንድ ተብሎ ይጠራል:: ይህም የሰው ልጅ ነፍስ እንኳ መለኮት ሳትሆን በባሕርይዋ አትሞትም:: ስለዚህ ብንችል ለነፍሳችን ክብርን ልንሰጥ፤ ሁሉን አሳልፈን ለእርሷ ልንከፍል እንወዳለን:: ይኸውም ነፍሳችን ሕያዊት በመሆኗ ነው::

ከላይ እንደ ጠቀስነው ስለ ነፍሳችን እንዲህ ከሆነ በማለት ይህ ቅዱስ ለክርስቶስ መለኮታዊነት የምን ሰጠውን ታላቅነትና ክብርን እንደ ሚከተለው ይገልጡልናል::

«በጌታችን ላለ ላንዱ ለሥላሴ ባሕርይ፣ ክብር ለተሰጠው እንደምን አትወድ? መለኮት ሞተ ካልክ ሦስቱ ሞቱ እንዲሰኝብህ፣ የጌታችን ሥጋ በመቃብር ውስጥ እንደ ሙታን በድን እንዳ ደረግኸው፤ ከመለኮቱም እንደ ለየኸው አታውቅምን? የሥላሴ ባሕርይ አንድ ነውና፤ ይኸውም አንድ መለኮት ነው::

እንዲህ ካላሰብህ÷ እንዲህ ካላመንህ ወይም መለኮት በባሕርይው ይታመማል የምትል ከሆነ እንግዲህ ሞትን ድል የነሳው ሲኦልን የማረከው ወዴት አለ? ከየት የመጣው የትኛው ነው ልትል ይሆን? እንደ አንተ ሐሳብ ከሆነማ ኃይል እንደሌለው አንድ ተራ ሰው አላደረግኸውምን? ጽንዕ አጥተው ከማይንቀሳቀሱ ሙታን ጋር አልቆጠርከውምን?» በማለት በመጠይቅ መለኮት በሥጋ ተዋሕዶ ያለውን አነዋወር በዝርዝር ያገናዝበናል::

*የቅዱሳን አምላክ የቅዱስ አግናጥዮስን በረከት ያሳድርብን:: አሜን::*


# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

ባሉት ማከፋፈያዎች የሚከተሉትን መንፈሳዊ አገልግሎቶች ያገኛሉ:-

☞ ሐመር መጽሔት
☞ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
☞ ቅዱሳት መጻሕፍት
☞ በቴፕ፣ በቪዲዮ፣ በሲዲና በቪሲዲ የተዘጋጁ የመዝሙርና የስብከት ካሴቶች
☞ የካህናት አልባሳት፣ የመዘምራን ዩኒፎርም እና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት
☞ የተለያዩ ቅዱሳት ስዕሎች፣ ፖስተሮች፣ ፖስት ካርዶች እና የሥጦታ ዕቃዎችን በጅምላም ሆነ በችርቻሮ ያገኛሉ:: ይጎብኙን !!

ቅርንጫፎቻችን:-

| | |
|---|---|
| አዲስ አበባ 22 86 01 /ቅ/ማርያም ቅርንጫፍ/ | ሆሳዕና ቅርንጫፍ /06/ 55 17 28 |
| 56 67 88 /ንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ/ | ደሴ ቅርንጫፍ /03/ 11 75 45 |
| 13 81 30 /ቅ/ራጉኤል ቅርንጫፍ/ | ወልድያ ቅርንጫፍ /03/ 31 22 57 |
| 56 34 45 /ቅ/ጊዮርጊስ ቅርንጫፍ/ | ጅማ ቅርንጫፍ /07/ 11 86 34 |
| መቀሌ ቅርንጫፍ /04/ 40 97 61 | ናዝሬት ቅርንጫፍ /02/ 12 33 77 |
| ጎንደር ቅርንጫፍ /08/ 20 44 44 | አሰላ ቅርንጫፍ /02/ 31 58 08 |
| ባሕር ዳር ቅርንጫፍ /08/ 11 62 40 | ድሬደዋ ቅርንጫፍ /05/ 12 04 93 |
| ደ/ማርቆስ ቅርንጫፍ /08/ 71 39 61 | አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ /06/ 81 15 97 |
| ፍቼ ቅርንጫፍ 35 11 99 | አዋሳ ቅርንጫፍ /06/ 21 02 87 |
| አሶሳ ቅርንጫፍ /07/ 75 12 22 | ሻሸመኔ ቅርንጫፍ /06/ 10 47 95 |
| ነቀምት ቅርጫፍ /07/ 61 43 22 | |

የቃሉን ወተት አሁኑኑ ይመገቡ!!




www.eotcmk.org

# ሱባዔ ፥ ምንነቱ? ሥርዓቱ?

*ይነስም ይብዛ ብዙዎቻችን ምእመናን ውስጣችንን የምንመረምርበት፣ እግዚአብሔርንም ቸርነቱን የምንጠይቅበት የሱባዔ ጊዜ እንይዛለን:: ጊዜውም ይሁን ትጋቱ ጠፍቶ ይህንን መልካም ተግባር ለማድረግ የማንችል ብንኖርም ስለ ሱባዔ የምናስበው ብዙዎች ነን:: በመሆኑም አባቶች ብዙ ስላተረፉበት ሱባዔ ዬት መጣና ጥቅሙ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ልናውቃቸው በሚገቡ ተያያዥ ነጥቦች ዙሪያ ሰፋ ያለ ትምህርት ብትሰጡን መልካም ነው::*

*ፍቅርተ ሥላሴ /አ/አ/*

*በዚህ ርዕስ ዙሪያ ዝግጅቶችን እንድናቀርብ በየጊዜው በርካታ አንባብያን በደብዳቤ ጠይቃችሁናል:: በዚህም መሠረት ወቅቱን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በዚህ እትም ሰፋ ያለ ዝግጅት እናቀርባለን:: መልሱን አቀናብሮ ያቀረበልን መ/ር ኃ/ማርያም ላቀው ነው::*

## ሥርዓተ ሱባዔ

ሱባዔ ምንድን ነው? ሱባዔ በሰዋስዋዋ ትርጉሙ ሰባት ማለት ነው:: ሱባዔ በመንፈሳዊ አተረጓጎም አንድ ሰው ከዚህ ቀን እስከዚህ ቀን በጸሎት ከፈጣሪዬ እገናኛለሁ ብሎ የሚያቅደው መንፈሳዊ ዕቅድ ነው:: ሰባት ቁጥር በእስራኤላውያን ዘንድ በሥራም በቃልም የሚገለጥ ፍጹም ቁጥር ነው:: ለምሳሌ:- ፈጣሬ ዓለማት እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ሥነ ፍጥረትን ከመፍጠር ማረፉ፣ ለጸሎት የሚተጉ ምእመናን በቀን ለሰባት ጊዜ ማመስገናቸው የሰባት ቁጥርን ፍጹምነት ያመለክታል:: ዘፍ. 2፥2፤ መዝ118፥164:: ከዚህ አንጻር አንድ ሰው ለሰባት ቀናት ቢጾም «አንድ ሱባኤ ጾመ» ይባላል:: ለዐሥራ አራት ቀን ቢጾም «ሁለት ሱባዔ ጾመ» እያለ እየጨመረ ይሄዳል::

## መቼ ተጀመረ?

ሱባዔ የተጀመረው ከውድቀት በኋላ በመጀመሪያው ሰው በአዳም ነው:: ቅዱሳን መላእክት አዳምን ጸሎት መጸለይን እንዳስተማሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይናገራሉ:: «መላእክት ለአዳም ጊዜያትን አስተምረውት ነበር::» ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ:: አዳም ጥፋቱን አምኖ ከባሕር ውስጥ ሱባዔ በመግባቱና በመጸለዩ እግዚአብሔር በማይታበል ቃሉ «ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኀለሁ» ሲል ቃል ኪዳን ገብቶለታል /መጽሐፈ ቀሌምጦንስ አንቀጽ አራት/::

## ሱባዔ ስምን?

የሰው ልጅ ኃጢአት በሚስማማው የሥጋ ሰውነቱ ዘወትር ፈጣሪውን ይበድላል:: በፈጸመው በደል ኅሊናው ይወቅሰዋል:: ይጸጸታል:: በመጀመሪያ ደፍሮ በሠራው ኃጢአት በኋላ ይደጠነግጣል:: ይህ በማንኛውም ሰብአዊ ፍጥረት ኅሊና ውስጥ የሚፈራረቅ ክስተት ነው:: በዚህ ጊዜ የፈጣሪውን ይቅርታ ለማግኘት ያስባል፤ ይተክዛል:: «በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛል፥ ነገር ግን በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝ ሌላ ሕግ አያለሁ:: እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ:: ሮሜ.7፥22-25::

ሰው በደፋርነቱ የኃያሉን አምላክ ትእዛዝ ተላልፎ ትካዘ ዓለም ሲያስጨንቀው ሸክሙን የሚያቃልልበትና የሚያስወግድበት መንፈሳዊ ጥበብ ከቸሩ ፈጣሪ ተሰጥቶታል:: ይኸውም በጥቂት ድካመ ሥጋ ያልተወሰነ ጸጋ እግዚአብሔር የሚያገኝበት ሥርዓት ሱባዔ ነው:: ከጥንት እስከ ዛሬ አንድ ሰው በትካዜ ዓለም መንፈሱ ሲታወክ የነፍስና የሥጋ ጸጥታውን ለመመለስና ለማስከበር መጾምና መጸለይ ግድ ይሆንበታል:: በዚህ ጊዜ አመክሮ /ሱባዔ/ ይገባል::

## እግዚአብሔርን ስመማፀን

ሰው ሱባዔ ከሚገባባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ እግዚአብሔርን ለመማፀን ነው:: ማንኛውም ሰው ሱባዔ ሲገባ በቁርጥ ወደ ፈጣሪው የሚያቀርበው ተማኅፅኖ ሊኖረው ይገባል:: ምንም የምንጠይቀው /የምንማፀነው/ ነገር ሳይኖር ሱባዔ ብንገባ የምናገኘው መልስ አይኖርም:: ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታና ዝግጅት ሱባዔ የሚገቡ ሰዎች ከሱባዔ በኋላ ምን እንደ ተመለሰላቸው የሚያውቁት ነገር ስለ ማይኖር ሱባዔ በመግባታቸው የሚያገኙት ነገር የለም::

ስለዚህ ሱባዔ ከመግባታችን በፊት:- «ሱባዔ የምገባው ለምንድን ነው?» በማለት ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል:: ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን በግል ሕይወቱ ዙሪያ ስለ ሀገሩ ሰላም፣ ስለ ጓደኛው ጤና ወዘተ ጉዳዮች ላይ ፈጣሪውን ይማፀናል:: በዚህ ጊዜ በግል ሕይወቱም ሆነ በሀገሩ ጉዳይ ለገባው ሱባዔ ወዲያውኑ መልስ ሊያገኝ ይችላል፤ እንዲሁም መልሱ ሊዘገይ ይችላል:: በዚህ ጊዜ ከተሐራሚው ትዕግሥት /መታገሥ/ ይጠበቅበታል፤ «ለምን ላቀረብኩት ጥያቄ ቶሎ መልስ አልተሰጠኝ?» በማለት ማማረርና እግዚአብሔርን መፈታተን ተገቢ አይደለም:: እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበትና ለሚማፅ ነውም መልስ የሚሰጥበት የራሱ ጊዜ አለው:: ለምሳሌ በጓደኛው ውድቀት ምክንያት ሱባዔ ገብቶ በአንድ ሳምንት ውስጥ መልስ ያገኘ የአንድ ገዳም አገልጋይ ታሪክ መመልከት ተገቢ ነው::

«አኃው ለተልእኮ በወጡበት አንዱን ድቀት አግኝቶት አድሯል:: በነጋው «ወንድሜ እኔ ድቀት አግኝቶኛልና እንግዲህ ወዲህ ተመልሼ ከዚያ ገዳም አልሔድም፤ ዓለሙን መስዬ እኖራለሁ» አለው:: «እኔም እንጂ አግኝቶኛል፤ ይልቁንስ ሔደን ኃጢአታችንን ለመምህረ ንስሐችን ነግረን፤ ቀኖናችንን ተቀብለን እንደ ቀደመው ኾነን እንኖራለን» ብሎ አጽናንቶ ይዞት ሔደ:: ሔደው ለመምህረ ንስሐቸው ነግረው ቀኖናቸውን ተቀብለው ፩ /አንድ/ ሱባዔ፣ ቀኖና እንዳደረሱ «ሰረይኩ ለከ በእንተ ዘኢገብረ እኁከል፤ ኃጢአት ስላላደረገው ወንድምህ ይቅር ብዬሃለሁ» የሚል ድምፅ አሰምቶታል:: /ዜና አበው/::

ከላይ ታሪካቸው የሰፈረው የገዳም አገልጋዮች ለአገልግሎት በተላኩበት አገር አንዱ ድቀት አግኝቶት በዝሙት ሲወድቅ ጓደኛው እንደ እርሱ ድቀት እንዳገኘው አድርጐ ጓደኛውን በማጽናናት ወደ ገዳም በመመለስ አንድነት ኾነው ሱባዔ ይገባሉ:: አንድ ሱባዔ /ሰባት ቀን/ እንደ ጨረሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ «ኃጢአት ሳይሠራ ለአንተ ብሎ ሱባዔ ስለገባው ወንድምህ ስል ይቅር ብዬሃለሁ» የሚል ፈጣን መልስ አገኝቷል:: ስለዚህ ሱባዔ በግል ሕይወትም ሆነ በጓደኞችን ሕይወት ዙሪያ ስንገባ ፈጣን ወይም የዘገየ መልስ ሊሰጠን ስለሚችል በትዕግሥት መጠባበቅ ይኖርብናል::

## የቅዱሳንን በረከት ስመሳተፍ

ቅዱሳን አባቶችና ቅዱሳት እናቶች የተጋደሉትን ተጋድሎ በማዘከር ቃል ኪዳን በተሰጣቸው ገዳማትና አድባራት የሚገባ ሱባዔ የቅዱሳኑን በረከት ተካፋይ ያደርጋል:: ቅዱሳን በሚጋደሉበት ቦታ «ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ» /ኢሳ.56፥6/ በማለት እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለ ገባላ



www.eotcmk.org

ቸው ሱባዔ በመግባት በረከታቸውን መሳተፍ ይቻላል:: በጾመ ነቢያት የነቢያትን በረከት ለመሳተፍ፣ በጾመ ሐዋርያት የሐዋርያትን በረከት ለመሳተፍ፣ በጾመ ፍልሰታ የእመቤታችንን በረከት ለመሳተፍ ሱባዔ መግባት የነበረና ወደ ፊትም የሚኖር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው:: ዛሬ ይህን ሥርዓት በመከተል የተለያዩ ቅዱሳንና በረከት ለመቀበል /ለመሳተፍ/ የቅዱሳን ዐፅም ካረፈበት ገዳም በጾም፣ በጸሎት፣ በጉልበትም ገዳማትን በማገልገል የቅዱሳንን በረከት ደጅ የሚጠኑ ምእመናንና መናንያን በየገዳማቱ እጅግ በርካታ ናቸው:: ይኸውም በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በምዕራፍ 2፥9 እንደ ተመለከተው ነቢዩ ኤልሳዕ መምህሩን ኤልያስን በማገልገል የኤልያስ በረከት በእጥፉ በኤልሳዕ ላይ አድሮበታል:: ይህን አብነት በማድረግ በየገዳማቱ በትሕርምት የሚኖሩ መናንያንን ያገለገሉበትን ገዳም አባት በረከት በእጥፍ እየተቀበሉ ለሌሎችም የሚያቀብሉ አባቶች በየገዳማቱ አሉ:: ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ በስመ ገዳማዊ የምእመናንን ገንዘብ የሚዘርፉና የእውነተኛ መነኮሳትንና መናንያንን የተቀደሰ ሕይወት የሚያጉድፉ መኖራቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል::

## የተሰወረ ምሥጢር እንዲገለጥልን

በዘመነ ብሉይ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ነገሥታት ራእይ በማሳየት ምሥጢሩን ይሰውርባቸው ነበር:: ለምሳሌ የግብፁን ፈርዖን፣ የባቢሎኑን ናቡከደነፆርንና ብልጣሶርን መጥቀስ ይቻላል:: ዘፍ.41፥14-36:: ዳን.4፥9፤ ዳን.5፥4:: እነዚህ ነገሥታት በግል ሕይወታቸውም ሆነ በመላው ዓለም ወደ ፊት ሊፈጸም የሚችል ራእይ ቢያዩም ቅሉ ራእዩን በትክክል ተረድተው «እንዲህ ይሆናል» የማለት ብቃት አልነበራቸውም:: ስለዚህ በዘመናቸው ይኖሩ የነበሩትን ነቢያት ሱባዔ ገብተው የሕልማቸውን ትርጉም እንዲነግሩአቸው ይማፀኑ ነበር:: ነቢያትም ሱባዔ በመግባት ነገሥታቱ ያዩትን የምሥጢረ ሥጋዌ ነገርና የመንግሥታቸውን አወዳደቅ ገልጸው ይናገሩ ነበር:: ዳን.5፥28::

እንዲሁም ቅዱሳን በየራሳቸው ያዩት ራእይ ምሥጢር ሲከደንባቸው የራእዩ ምሥጢርና ትርጉም እንዲገለጥላቸው ሱባዔ ይገባሉ:: እግዚአብሔርም በንጽሕና ሆነው የገቡትን ሱባዔ ተመልክቶ ምሥጢር ይገልጥላቸዋል:: ለምሳሌ ነቢዩ ዕዝራ የመጻሕፍትን ምሥጢር እንዲገልጥለት ሱባዔ ቢገባ የጠፉትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዳግም መልሶ ለመጻፍ ችሏል:: መዝ.8፥1::

በዘመነ ሐዲስ በሰፊው የሚወሳው ቅዱሳን ሐዋርያት ከነሐሴ 1-14 የገቡት ሱባዔ ነው:: ይህ ሱባዔ ተሰውሮ የነበረውን የቅድስት ድንግል ማርያምን ትንሣኤ ተረድተው በረከቷን ለመሳተፍ አብቅቷቸዋል::

«እመቤታችን ያረፈችው ጥር 21 ቀን 1950 ዓመተ ምሕረት ነው:: ሐዋርያት ሊቀብሯት ወደ ጌቴሰማኔ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ በታተቸው:: በዚህ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት የእመቤታችንን ሥጋዋን ወስደው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኑረውታል::» /ተአምረ ማርያም፣ ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን/:: በዚህ ጊዜ እነርሱ ተደናግጠው ስለ ተበታተኑ የእመቤታችን የዕረፍቷ ያስጨንቃቸው ነበር::

«ቅዱስ ዮሐንስ በተመስጦ እየሄደ ሥጋዋን ያጥን ነበር:: ለሐዋርያት ይህን ይነግራቸዋል:: ለዮሐንስ ተገልጣ ለእኛ ሳትገለጥ ብለው በነሐሴ ሱባዔ ገቡ:: ሁለተኛው ሱባዔ ሲፈጸም በ14ኛው ቀን መልአክ ሥጋዋን አምጥቶ ሰጥቶአቸዋል፤ ቀብረዋታል:: በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ ዐርጋለች:: /ተአምረ ማርያም፣ ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን/::

እንግዲህ ለቅዱሳን ሐዋርያት የእመቤታችን የዕረፍትና የዕርገት ምሥጢር የተገለጠላቸው በሱባዔ ነው:: ይህን መሠረት በማድረግ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን የዕርገቷን በረከት ለማግኘት ትጾማለች:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን የሱባዔ ወቅት ሕፃናትም ሳይቀሩ ይሳተፉታል::

## ሱባዔ ነቢያት

እግዚአብሔር ለአዳም የገባውን ቃል ኪዳን መሠረት በማድረግ ቀደምት ነቢያት በተነሡበት ዘመን ቅደም ተከተል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንና ዳግም መምጣት ትንቢት ተናግረዋል:: ሱባዔም ቆጥረዋል:: ኢሳ. 7፥14:: መዝ.49፥3:: ዘካ.13፥6፤ ዘካ.14፥1:: የአንዱ ነቢይ ትንቢታዊ ንግግርና ሱባኤ በአነጋገርና በአቆጣጠር ከሌላኛው ነቢይ ጋር ይለያያል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ትንቢቱን ሲያናግር ምሳሌውን ሲያስመስል ጉዳናው ለየቅል በመሆኑ ነው:: «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጉዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ::» እንዲል:: ዕብ.1፥1:: የአቆጣጠር ስልታቸውና የሱባኤ መንገዳቸው ቢለያይም ዓላማና ግባቸው ግን አንድ ነው::

## ሱባዔ አዳም

አዳም ትንቢት በመናገርና ሱባዔ በመቁጠር የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል:: ምክንያቱም በገነት ሰባት ዓመት ከአንድ ወር ከዐሥራ ሰባት ቀን በተድላና በደስታ ከኖረ በኋላ ሕግ በማፍረሱና የፈጣሪውን ቃል በመጣሱ ያለምንም ትካዜና ጉስቁልና ከሚኖርበት ዔደን ገነት ተባሯል:: ዘፍ.3፥24:: እርሱም ፈጣሪው እንዲታረቀው፣ በዐይነ ምሕረት እንዲጐበኘው፣ ቅዝቃዜው ሰውነት ከሚቆራርጥ ባሕር ውስጥ በመቆም ለሠላሳ አምስት ቀን /አምስት ሱባዔ/ ሱባዔ ገብቷል:: በባሕርዩ የሰውን ልጅ እንግልት የማይወድ ቸሩ ፈጣሪ የአዳምን ፈጽሞ መጸጸት ተመልክቶ «በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅከ ውስተ መርህብከ ወእቤዝወከ በመስቀልየ ወበሞትየ÷ በአምስት ቀን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ» ብሎ ተስፋውን ሰጠው:: አዳም የተሰጠውን ተስፋ ይዞ በዓለመ ሥጋ ለዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ከኖረ በኋላ መከራና ችግር ከበዛበት ዓለም በሞት ተለይቷል::

በወንጌል ተከሶ በወኅኒ የተፈረደበት ሰው ከእስር የሚፈታበትን ዕለት በማውጣት በማውረድ ወራቱንና ዓመታቱን እንደሚቆጥር፣ አዳምም ቢለይም በሲኦል የነፍስ ቅጣት ካለበት ሥፍራ ይኖር ስለነበር የተሰጠውን ተስፋ በማሰብ ሱባዔውን እየቆጠረ÷ የተናገረውን የማያስቀር የማያደርገውን የማይናገር ጌታ÷ «እነሆ አድንኀለሁ» ብሎ የገባልኝ ዘመን ተፈጸመ፤ ሰዓቱ አሁን ነው፤ እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ቸሩ አምላክ ሰው ኾኖ÷ ሥጋ ለብሶ÷ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ:- «ተንሥኡ ለጸሎት÷ ለጸሎት ተነሡ፤ ሰላም ለኩልክሙ፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን» በማለት አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ነጻ አውጥቶታል:: አዳምን በመከተል ልጆቹም አበው ቅዱሳን ነቢያት ሱባዔ በመግባት የተስፋውን ዘመን በመቁጠር በመልካም ግብር ተከትለውታል:: በዚህም መሠረት በርካታ ነቢያት በተለያየ ስልት ሱባኤ ቆጥረዋል፤ እኛም ሱባዔ ከቆጠሩ ነቢያት የተወሰኑትን በዚህ ጽሑፍ እንደ ሚከተለው እናቀርባለን::

## ሱባዔ ሔኖክ

ጻድቁ ሔኖክ፣ የያሬድ ልጅ ሲሆን፣ በትውልድ ከአዳም ሰባተኛ ነው:: እርሱም በሕይወቱ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ቤት ንብረቱን በመተው በሱባዔና በትሕርምት እግዚአብሔርን አገልግሏል:: ፍጹም አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሰው በመሆኑ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን መልካም ግብሩ ተመስክሮለታል:: «ሔኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ::» ዘፍ.5፥22:: ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር የሱባዔውን ዋጋ ቅዱስ መንፈሱን በረድኤት ስለ አሳደረበት ትንቢት ተናግሯል፤ ሱባዔ ቆጥሯል:: በሰማይ ተሰውሮ ሳለ ስለ





www.eotcmk.org

ቅዱሳን መላእክት፣ ስለ መሲሕ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ፀሐይና ጨረቃ አመላለስ /ዑደት/ የሚተርክ በስሙ የተሰየመውን መጽሐፍ ጽፏል:: ዘፍ. 5፥21-24:: ይሁዳ ቁ.14:: ሔኖክ 1፥9::

ሱባዔ ሔኖክ የሚባለው ነቢዩ ሔኖክ በመስፈርት የቆጠረው ሱባዔ ነው:: መስፈርቱ /ማባዣ ቁጥሩ/ 35 ሲሆን 35×19 ሲበዛ በውጤቱ 685 ዓመት ይሆናል:: 685×12 ስናባዛው 7980 ይሆናል:: ይኸውም ሐሳብ የሚያስረዳው ስለ ክርስቶስ ምጽአት ነው::

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አሁን የደረስንበት ዘመን 7497 ይሆናል:: ይህን ለማረጋገጥ በ5500 ዓመት ላይ 1997 ዓመትን መደመር ነው:: በዚህን ጊዜ ከላይ ያስቀመጥነውን 7497 ዓመት ይሰጠናል:: በነቢዩ ሔኖክ አቆጣጠር መሠረት ምጽአተ ክርስቶስ በ7980 ይሆናል:: ከላይ ሔኖክ የቀመረውን ቁጥር ይዘን ከ7980 ዓመት ላይ አሁን ያለንበትን ዘመን /1997/ ስንቀንስ 483 ዓመት እናገኛለን:: ስለዚህ በሔኖክ ሱባዔ መሠረት ምጽአተ ክርስቶስ ሊሆን 483 ዓመት ይቀራል::

## ሱባዔ ዳዊት

ነቢዩ ዳዊት ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ ንጉሥ ነበር:: ዘመነ መንግሥቱ 1011-971 ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ነበር ይታመናል:: ነቢዩ ዳዊት ልበ አምላክ እንደ መሆኑ ትንቢት ተናግሯል:: ሱባዔ ቆጥሯል:: ይኸውም ቀመረ ዳዊት በመባል ይታወቃል:: «እስመ ዐሠርቱ ምእት ዓመት በቅድሜከ፤ ከመ ዕለት እንተ ትማልም ኃለፈት፤ ሺ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትላንት ቀን»:: /መዝ.89፥4/ የሚለውን መምህራን ሲቆጥሩት 1140 ዓመት ይሆናል:: ይኸውም በጌታ ዘንድ 1140 ዓመት እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ነቢዩ ዳዊት ተናግሯል:: ይህም ለዳዊት ሱባዔ መቁጠሪያ /መሥፈሪያ/ ሆኖ አገልግሏል፤ 1140×7= 7980 ዓመት ይሆናል:: ይህም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በ7980 ዓመት ክርስቶስ ዳግም እንደ ሚመጣ የሚያመለክት ነው::

## ሱባዔ ዳንኤል

ነቢዩ ዳንኤል ምድቡ ከዐበይት ነቢያት ነው:: እስራኤል ወደ ባቢሎን ሲማረኩ ተማርኮ ወደ ባቢሎን ወርዷል:: እርሱም ስለ ክርስቶስ መምጣት ትንቢት ተናግሯል፤ ሱባዔም ቆጥሯል:: «ሰብአ ሰንበታተ አድሞሙ ለሕዝብከ፤ ሰባ ሰንበት ወገኖችህን ቅጠራቸው::» ይኸውም ክርስቶስ ከ490 ዓመት በኋላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ትንቢት ነው:: እንዲሁም «እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ትትሐነፅ መቅደስ ወእምዝ ትትመዘበር፤ እስከ ንጉሥ ክርስቶስ ንጉሥ ድረስ መቅደስ ትታነፃለች፥ በኋላም ትፈርሳለች» ሲል ተናግሯል::

የአቆጣጠር ስልቱም በዓመት ሲሆን ይኸውም ሰባቱን ዓመት አንድ እያሉ መቁጠር ነው:: ይኸውም ሱባዔ ሰንበት ይባላል:: ዳንኤል ሱባዔ ከቆጠረበትና ትንቢት ከተናገረበት ጀምሮ ክርስቶስ እስከ ሚወለድ 490 ይሆናል:: መስፈርቱ /ማባዣው/ ሰባት ስለሆነ 7X70 ስናባዛው 490 እናገኛለን:: ይኸውም ነቢዩ ሱባዔ ከቆጠረና ትንቢት ከተናገረ ከ490 ዓመት በኋላ የክርስቶስን መወለድ ያመለክታል::

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትናቸው ቅዱሳን ነቢያት አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ሱባዔ ገብተው በትሕርምት በመኖራቸው ድንቅ የሆነውን የክርስቶስን ልደትና ዳግም ምጽአት ለመተንበይ ችለዋል:: ሱባዔ መግባት የራቀን ለማቅረብ፥ የረቀቀን ለማጉላት ብቃትን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስገኝ መንፈሳዊ ጥበብ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው::

## የሱባዔ ዓይነቶች

## የግል ሱባዔ /ዝግ ሱባዔ/

የግል ሱባዔ አንድ ሰው ብቻውን ሆኖ በቤትና በአመቺ ቦታ የሚይዘው ማንም ሰው ሳያየው በግሉ የጸሎት በአቱን ዘግቶ በሰቂለ ኅሊና ሆኖ ፈጣሪው ብቻ እንዲያየው፥ እንዲሰማው በኅቡዕ የሚፈጽመው ሱባዔ ነው:: ማቴ.6፥5-13:: በዚህ ዓይነት መልክ አንድ ሰው ሱባዔ ሲገባ ዘጋ ይባላል:: ዝግ ሱባዔ የያዘ ሰው የሚያስፈልገውን ነገር ይዞ ወደ በአቱ ከተከተተ በኋላ ሱባዔው እስኪፈጸም ድረስ ከሰው አይገናኝም:: መዝ. 101፥6-7::

## የማኅበር ሱባዔ

የማኅበር ሱባዔ የሚባለው ካህናት፣ ምእመናን ወንዶችና ሴቶች፣ ሽማግሌዎችና ወጣቶች በአንድ ሆነው በቤተ ክርስቲያንና አመቺ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ ተሰብስበው የሚገቡት ሱባዔ ነው:: በብሉይ ኪዳን የነበሩ ምእመናን ወደ እግዚአብሔር በመሄድ ይጸልዩ ነበር:: 1ኛ ሳሙ.1፥9፤ መዝ.121፥1፤ ሉቃ.18፥10-14::

በሐዲስ ኪዳንም የሐዋርያት ተከታዮች የኾኑ መነኮሳት፣ ካህናትና ምእመናን በገዳማት፣ በአድባራት፣ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፣ የጽዋ ማኅበርተኞች ስለ ማኅበራቸው ጥንካሬና ከማኅበርተኞቹ መካከል አንዱ ችግር ሲገጥመው የማኅበር ሱባዔ ይያዛል::

## የዐዋጅ ሱባዔ

የዐዋጅ ሱባዔ በአገር ላይ ድንገተኛ አደጋ፣ አባር ቸነፈርና ጦርነት ሲነሣ እንዲሁም ለማኅበረ ምእመናን አስጊ የሆነ መቅሰፍት ሲከሰት፣ እግዚአብሔር መዓቱን በምሕረት ቁጣውን በትዕግሥት እንዲመልስ የሚያዝ የሱባዔ ዓይነት ነው:: ለዚህ ዓይነቱ ሱባዔ የነነዌ ሰዎችና በፋርስ በስደት ይኖሩ የነበሩ እስራኤላውያን ተጠቃሾች ናቸው:: የነነዌ ሰዎች የዮናስን ስብከት ሰምተው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ለሦስት ቀን ከመብል ከመጠጥ ተከልክለው በመጾም በመጸለይ እግዚአብሔር መዓቱን በምሕረት፥ ቁጣውን በትዕግሥት እንዲመልስ አድርገዋል:: ሌላው በፋርስ በስደት ይኖሩ የነበሩ አይሁድ በአስቴር ትእዛዝ የያዙት ሱባዔ ተጠቃሽ ነው:: በዚያን ዘመን አርጤክስስ አይሁድ በያሉበት እንዲገደሉ በማዘዙ ከዚህ የጅምላ ጭፍጨፋ ለመዳን አይሁድ በዐዋጅ ሱባዔ ገብተዋል:: አስቴር ገብታ ንጉሡን ስታናግረው ሌላው ሕዝብ በውጭ ዐዋጅ ዐውጀው ሱባዔ ገብተው ፈጣሪያቸውን ተማፅነዋል:: አስቴር 4፥16 - 28::

በአገራችንም ይህን የመሰለ የዐዋጅ ሱባዔ በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ተደርጓል:: ፋሽስት ጣልያን አገራችንን በመውረር ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዥ ለማድረግ ድንበሯን አልፎ በመጣበት ወቅት ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ:- «ጉልበት ያለህ በጉልበትህ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ ርዳኝ» በማለት የዐዋጅ ሱባዔ መያዛቸው ይነገራል:: በዚህም መሠረት በየገዳማቱ ምሕላ ተይዟል፤ ንጉሡም ታቦተ ጊዮርጊስን ይዘው ዓለምን እጅግ ያስደነቀ፥ ጥቁሮችን ለነጻነታቸው እንዲነሣሡ የሚያስችል ፋና ወጊ የሆነ ድል አግኝተው አገራችንን ለቅኝ ግዛት ያሰበውን ፋሽስት ጣልያንን ማሸነፋቸው በከፍተኛ ስሜት የምናስታውሰው ነው::

## ቅድመ ዝግጅት

ሱባዔ መግባት የሚፈልግ ምእመን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል:: ያለምንም ዝግጅት ሱባዔ መግባት ለፈተና ያጋልጣል::



www.eotcmk.org

ስለዚህ ቅድመ ሱባዔ /ሱባዔ ከመግባት አስቀድሞ/፣ ጊዜ ሱባዔ /በሱባዔ ጊዜና ድኅረ ሱባዔ /ከሱባዔ በኋላ/ ዝግጅት አስፈላጊ ነው።

## ቅድመ ሱባዔ /ሱባዔ ከመግባት አስቀድሞ/

በመጀመሪያ ሱባዔ የምንገባበትን ምክንያት ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። አንድ ሰው ሱባዔ የሚገባበትን ዓላማ ለይቶ ካስቀመጠ ከሱባዔ በኋላ የሚጠበቀውን ነገር ማግኘት አለማግኘቱን ይረዳል። ይህ ሳይሆን ሱባዔ ቢገባ ከሱባዔው በኋላ የጠየቀው ነገር ስለሌለ ትርጉም ያጣል። ስለዚህ ሱባዔ ከመግባታችን በፊት ለምን ሱባዔ ለመግባት እንዳሰብን ለይተን ማወቅ ይኖርብናል።

ሱባዔ ለመግባት የወሰንበትን ምክንያት ከለየን በኋላ ምክንያታችንን ይዘን የንስሐ አባታችንን ማማከር ያስፈልጋል። ምክንያቱም በምክረ ካህን መጓዝ መጀመር ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። ከዚህ ባሻገር በአባትነታቸውና በሕይወት ልምዳቸው ምን ማድረግ እንደሚገባን ምክር ለማግኘት እገዛ ያደርግልናል። ቅድመ ሱባዔ ከንስሐ አባት ጋር መመካከር ተገቢ ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ሰው በሱባዔ ወቅት የተለያዩ ፈተናዎች ቢያጋጥሙት የተሰጠውን ምክር በመጠቀም ፈተናውን ለመቋቋም ይችላል። እንዲሁም የንስሐ አባቱ በሱባዔ ወቅት በጸሎት እንዲያስቡት መማከሩ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው።

ሱባዔ ለመግባት ስናስብ ለምን ያህል ቀናት መቆየት እንዳለብን መወሰን ያስፈልጋል። ሱባዔ ከዚህ እስከዚህ እቆያለሁ ብለን ዕቅድ የምንይዝበት ነው። እንደ አቅማችንና እንደ ችሎታችን ከዚህ ቀን እስከዚህ ብለን በመወሰን ሱባዔ መግባት ተገቢ ይሆናል። ለምሳሌ፡- ምንም ዓይነት ልምድ ሳይኖረው አንድ ሰው «በዋሻ እዘጋለሁ» ቢል ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል። ምክንያቱም በሱባዔ ወቅት ፈተና ስለሚበዛ የሚመጣበትን ፈተና መቋቋም ባለመቻል ሱባዔው ሊቋረጥ ይችላል። ስለዚህ ቅድመ ሱባዔ ዐቅምንና ችሎታን አገናዝቦ መወሰን ተገቢ ነው።

ሌላው ቅድመ ሱባዔ ለሱባዔ ተስማሚ የሆነ ወቅትና ቦታ መምረጥ ተገቢ ነው። በቤተ ክርስቲያን በአብዛኛው ሱባዔ የሚገባው አጽዋማትን ተከትሎ ነው። ስለዚህ ሱባዔ የምንገባበት ወቅት የጾም ወቅት መሆን አለመሆኑን መለየት ያስፈልጋል። በአጽዋማት ወቅት የሚያዝ ሱባዔ ለተሐራሚ ጠቀሜታው እጅግ የጐላ ነው። ምክንያቱም በአጽዋማት ወቅት ብዙ አባቶች ሱባዔ ስለሚይዙ ከአባቶች ጸሎት ጋር ልመናችንና ጸሎታችን ሊያርግ ይችላል። ስለዚህ ወቅትን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ «ከወርኃ አጽዋማት ውጭ ሱባዔ አይያዝም» የሚል አቋም ለመያዝ አይደለም። አንድ ሰው ፈተና ከአጋጠመው በማንኛውም ጊዜ ሱባዔ ሊገባ እንደሚችል እዚህ ላይ ለመጠቆም እንወዳለን። ከዚህም ባሻገር ሱባዔ የምንይዝበትን ቦታ መምረጥ አለብን። ለሱባዔ የምንመርጣቸው ቦታዎች ለፈተና የሚያጋልጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይኸውም ሱባዔ ከተገባ በኋላ ኀሊናችን እንዳይበተን እገዛ ያደርጉልናል። ጫጫታና ግርግር የሚበዛበት ቦታ በሰቂለ ኅሊና ለመጸለይ አያመችም። ስለዚህ ሱባዔ የምንይዝባቸው ቦታዎች ከከተማ ራቅ ያሉ ገዳማትና አድባራት ተመራጭ ናቸው።

## ጊዜ ሱባዔ /በሱባዔ ጊዜ/

በጸሎት ሰዓት ዓምድና ግድግዳ ሳይደገፉ፥ መቋሚያ ሳይዙ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ በመቆም መጸለይ ይኖርብናል። እንዲሁም ፊትን ወደ ምሥራቅ መልሶ መቆም ወዲያና ወዲህ፥ ወደ ግራ ወደ ቀኝ አለመዟዟር በሰፊሐ እድ በሰቂለ ኅሊና ኆኖ መጸለይ ይገባል። መዝ.5፥3፤ መዝ.133፥2፤ ዮሐ.11፥41።

በሱባዔ ወቅት በቅደም ተከተል መጸለይ አለብን። መጀመሪያ «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል፥ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንዱ አምላክ መላ ሰውነቴን በትእምርተ መስቀል አማትባለሁ» እያለ ሰጊድን ከሚያነሣው ሲደርስ መስገድ መስቀልን ከሚያነሣ ላይ ስንደርስ ማማተብ ይገባል።

በማስከተል አቡነ ዘበሰማያት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያምና ሌሎች በመዝገበ ጸሎት የተካተቱትን መጸለይ፤ ቀጥሎ አቡነ ዘበሰማያት፣ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያምን፣ ጸሎተ ሃይማኖትን ከጸለይን በኋላ አቡነ ዘበሰማያት መድገም፤ ከዚያ 41 ጊዜ ኪርያላይሶን ይባላል። ሌላው በሱባዔ ጊዜ ከተሐራሚ የሚጠበቀው ነገር ኃጢአቱን እያሰበ ማዘን ማልቀስ ነው። ሲያለቅስም ለእያንዳንዱ በደል እንባ ማፍሰስ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ሱባዔ የገባ ሰው ሱባዔውን ሳይጨርስ ወይም ሱባዔውን አቋርጦ ከማንም ሰው ጋር ፈጽሞ መገናኘት የለበትም።

## ድኅረ ሱባዔ /ከሱባዔ በኋላ/

ለቀረበ ተማኅፅኖ እግዚአብሔር የሚያደርግልንን ነገር መጠበቅ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ላቀረብንለት ምልጃና ጸሎት እንደ ልባችን መሻት እንደ እርሱ ቸርነት እርሱ በወደደ ጊዜ ያደርግልናል። ሱባዔ የገባ ሰው ሁሉ ራእይ ላያይ ይችላል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መልስ አሰጣጥ ለማንም ግልጽ አይደለም። ከሱባዔ በኋላ መጀመሪያ የምናገኘው የኅሊና ሰላምን ነው። ይህ ትልቅ የአምላክ ስጦታ ነው። ከዚህ ባሻገር ሱባዔ ገብተን ያሰብነውን ካላገኘን ዳግመኛ ተዘጋጅተን እስከ መጨረሻው ሰዓት መማፀን፥ መጽናት ይኖርብናል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


የአብነት እና የዜማ መሣሪያዎች ትምህርት ይማሩ

የሚሰጠት የትምህርት ዓይነቶች፡-
1ኛ/ የግእዝ ቋንቋ 2ኛ/ ንባባ /ቆጠራ/ 3ኛ/ ዜማ
4ኛ/ ቅኔ 5ኛ/ በገና 6ኛ/ መሰንቆ
7ኛ/ ዋሽንት 8ኛ/ ቅዳሴ ተሰጥኦ

ትምህርቱ የሚሰጥበት አድራሻ፡-
ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ወረድ ብሎ አዲስ አበባ ጤና ቢሮ አጠገብ አቡነ ጎርጎርዮስ የትምህርት ማዕከል

ስልክ 51 06 59/ 09- 65 95 84
የመረጡትን ይማሩ ዘንድ አሁኑኑ ይመዝገቡ!!
ማኅበረ ቅዱሳን





www.eotcmk.org

# «አባ ኖዋል»

ትዕግስት ታፈረ

ታኅሣሥ 29/ 1997 ዓ.ም
እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ምድርን ኀበኘ፡፡ ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡበት ቤት በሰዎች ተሞልቷል፡፡ ካህናት ባለ ልደቱን ያወድሳሉ፡፡ ምእመናን ይቀበላሉ፡፡ ጧፍ ያላበራ በጣት ቢቆጠር ነው፡፡ ካህናትና ዲያቆናት ዐይን በሚስብ ካባ÷ ምእመኑ እንደ ወተት በጠሩ አልባሳት ደምቀዋል፡፡ በተለይ በግቢው ዙሪያ ዓመታትን ካስቆጠሩት የጥድ ዛፎች ስር የተኮለኮሉት ነጭ ለባሾች ከጧፉ ከሚወጣው ብርሃን ጋር ሲታዩ ግቢውን ከትልልቅ ዛፍ በተሠሩ /የገና ዛፎች/ ያሸበረቀ አስመስለውታል፡፡

«ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ

እም ማርያም ቅድስት ድንግል

ተሣሀለነ እግዚኦ... » እያሉ ካህናት ከልደቱ ጀምረው ስለ ሥነ ስቅለቱና ትንሣኤው እያነሡ ምስጋናቸውን ይደረድራሉ፡፡

በተጠራበት መርሐ ግብር እንደማይቀር በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ያስመሰከረው ክርስቶስ የራሱን ልደት በደመቀ ሁኔታ እያ ከበሩ÷ ስሙን ሲያወድሱ÷ ለክብሩ ሲዘምሩና በክብር ሲጠሩት በመካ ከላቸው ለመገኘት አፍታ አልቆ የም፡፡ ከእነርሱም ጋር ደስ አለው፡፡ መላእክት ከምእመናኑ ጋር ከ1997 ዓመት በፊት በግርግም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ እንዳ ደረጉት አመሰገኑ፡፡

ይኼ ቀን በመላው ዓለም ተከብሮ እንደሚውል ሲያውቅ በእርሱ ዘንድ የማይቻል የለምና ዓለም እንዴት ልደቱን እንደ ሚያከብርለት ለመጐብኘት ሄደ፡፡ እዚህም አለ፡፡ በስሙ በየቤታቸው «ድል» ያለ ድግስ ያዘጋጁ የአውሮፓውያን፣ የእስያ፣ የአሜሪካና የእስራኤል ሕዝቦችም ወገባቸውን ታጥቀው ዕለቱን የደመቀ ለማድረግ ደክመዋል፡፡ ፊልም ቤቶች የአዳዲስ ፊልም ማስተዋወቂያዎችን ይለቃሉ፤ ሙዚቀኞች በዓሉን ምክንያት በማድረግ ስሌት ማውጣታቸውን ይጽፋሉ፡፡ ተዋናዮች የሲኒማውንና የቴአትሩን ገበያ ለማጥለቀለቅ ይታትራሉ፡፡ የሰፊው ሕዝብ ልማድ ይኼው ነው፡፡

ከሁሉም ግን የክርስቶስን «ግርምት» እጥፍ ያደረገው በትውልድ ሀገሩ በአንድ ከበርቴ ምእመን ቤት በተገኘ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ታላቅ ሰው ቤት ውስጥ ሁሉ ነገር ሙሉ ነው፡፡ ከእንግዳ መቀ በያው ክፍል መሃል ላይ ትልቅ ክሬም ኬክ ጉብ ብሎ እነ ከረሜላና ቼኮላት አጅበውታል፡፡ ባለ ልደቱን ግን የጠራው የለም፡፡ እንዲሁ ገብቶ ጥግ ይዞ ቆሟል፡፡ ፊት ለፊቱ ትልቅ የጥድ ዛፍ በግርማ ሞገስ ተተክሏል፡፡ ከስር ዙሪያውን ዘር የተዘራባቸው ስህኖች ከበውታል፡፡ ክርስቶስ ማንም ባይነግረውም ከሁለት ሳምንት በፊት የተተከለ አዝዕርት እንደ ሆኑ አላጣውም፡፡ እስራኤላውያን ጌታ ሲወለድ ሁሉ ነገር መለምለሙን የሚያመለክቱበት ምሳሌያቸው ነው፡፡

ዙሪያውን እየቃኘ ጥጉን አለቀቀም፡፡ በቤቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ዐይናቸውን እንኳን አላዋሱትም፡፡ በምትኩ ሙሉ ትኩረት የተሰጠው የቤቱ ጥቁር እንግዳ አለ፡፡ በቀይ ልብስ ተሸልሞ፣ ረጅም ነጭ ጽሕሙን አንዥርግጎ በክብር ተቀምጧል፡፡ «አባ ኖዋል» ይሉታል እስራኤላውያን፤ ሌሎቹ ደግሞ « አባ ገና»፡፡ ክርስቶስ ለመንግስቱ ቀናኢ ነውና ቀና፡፡

ከአሁን አሁን ቀልባቸው ለኔ ይገዛል ብሎ በትዕግሥት ብዙ ጠበቀ፡፡ የእርሱ መኖር ቁባቸው አልነበረም፡፡ ኬኩም ተቆረሰ፡፡ ሻምፓኙ ተከፈተ፡፡ ብርጭቆ ከ«አባ ኖዋል» ጋር ለጤናችን ተብሎ ተጋጨ፡፡ የጤንነት ባለቤቱ ግን ለፍርፋሪ አልታጨም፡፡ ቸርነታቸው ወደ «አባ ኖዋል» ጐረፈ፡፡ ቀጥሎም በሚያብረቀርቅ ወረቀት የተጠቀለለ ስጦታ ልጆቻቸው ከአባ ኖዋል እጅ እንዲወስዱ አስረከቡ፡፡

ከሌላ ክፍል የሕፃናት ድምፅ ይሰማል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እነርሱን ናፈቀ፡፡ የወደደውን እንደሚሰጡት አልተጠራጠረም፡፡ ሕፃናት እንደ ርግብ የዋሆች ናቸው፡፡ ይባላል፡፡ ወላጆቻቸው «የአባ ኖዋልን» መምጣት ጠርተው አበሠሯቸው፡፡ በደስታ እየፈነጠዙ እየቦረቁ ክፍሉን ሞሉት፡፡ ክርስቶስ ሕፃናቱን ሲያይ ባለበት መርጋት አላስቻለውም፡፡ እንደ ምስኪን ጥጉን ይዞ ከቆመበት ተላወሰ፡፡ ልጆቹ ባልጠበቁት ትዕይንት ተገርመው ዐይናቸውን ተከሉበት፡፡ እጆቹን ዘረጋላቸው፡፡ ፈገግታው በገጹ ላይ ሞላ «ሕፃናት ወደኔ ይምጡ» ብሎ ለእስራኤል ሕዝብ በራሱ አንደበት እንደ ሰበከ እያስታወሰ «ኑ ወደ እኔ» እያለ እጆቹን እንደ ዘረጋ ቀረባቸው፡፡ የሁሉም ልጆች ዐይን እጆቹን ፈተሹ፡፡ በብርቅርቅ መጠቅለያ የተጠቀለለ ስጦታ አልያዘም፡፡ ወዲያው ዐይኖቻቸውን ከክርስቶስ ወደ «አባ ኖዋል» ሲመልሱ ግን የፈለጉትን አላጡም፡፡ ክርስቶስ በቀረባቸው ቁጥር እያፈገፈጉ ሸሹ፡፡ ተከተላቸው፡፡ ሊቀርቡት አልወደዱም፡፡ ሁሉም በ«አባ ኖዋል» ስር ተኮልኩለው አንጋጠጡ፡፡ ለእያንዳንዳቸው የተዘጋጀው ስጦታ ተበረከተላቸው፡፡ በርግጥ እርሱም በሕፃንነቱ ሰብአ ሰገል ስጦታ አበርክተውለታል፡፡ ይኼ ግን ከዚያ ተለየበት፡፡

በመዋዕለ ሥጋዌው እያለ፡ - «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ መንግሥቴን አትወርሱም» ብሎ በባሕሪው ንጹሕ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረላቸው ልጆቹ ከእርሱ ፍቅር በአብረቅራቂ ወረቀት የተጠቀለለው ስጦታ ላቀባቸው፡፡ እጅግ እያዘነ ለስጦታ ያቀረበውን ራሱን ሳይቀበሉት ካልተጠራበት ልደቱ ወጣ፡፡

በተጠራበት የልደቱ ክብረ በዓል ተመልሶ ታደመ፡፡ ድሮውንም ነበር፤ ስሙ ይጠራል፡፡ ይከበራል፡፡ ይወደሳል፡፡ ክቡር ስጦታውን ምእመናን አክብረው ተቀብለዋል፡፡ እንደ ገና ፍሥሐ ሆነ፡፡ ቀይ ለባሹን ሰው ግን አልረሳውም፡፡ በአብረቅራቂ ወረቀት በተጠቀለለ አላቂ ስጦታ አእምሮአቸውን በርዞበታል፡፡ የበለጠ ስጋት ላይ የጣለው ደግሞ ይኼው ቀይ ለባሽ ከጥቂት ዓመት ወዲህ በዚህች አዳጊ ሀገር ውስጥም መታየቱ ነው፡፡ እዚህ ስሙ « አባ ገና» ነው፡፡ ግብሩ በየመንገዱ ቆሞ ንግድ ቤቶች ያዘጋጁትን የማስታወቂያ ወረቀት መበተን ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ አልተረጋጋም፡፡ ስጦታውን ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በአክብሮት የተቀበሉት የዚህች ሀገር ምእመናን ኮራጆች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ የሠለጠነው ዓለም ባሕል፣ እምነትና ሥርዓት ኀሊናና ልባቸውን ሲሰርቃቸው ታዝቧል፡፡ ለ30 ዓመት ውድ ስጦታውን እንዲቀበሉ ላንቃው ከጉሮሮው እስኪጣጋ ነግሯቸዋል፡፡ የሰማው ቢገኝ እንኳን ያዳመጠው ብዙ አይደለም፡፡

እናም ይኼን ቀይ ለባሽ እዚህ ማየት አላስደሰተውም፡፡ ምናልባት ነገ እነዚህን አማኞችም በብርቅርቅ ስጦታው አባብሎ የተቀበሉትን ዘላለማዊ ስጦታ ያስጥላቸው ይሆናል፡፡ «ራሱን ለሰጠ አምላክ የሚገባውን ንጹሕ ልቡና «አባ ገና» እንዳ ይነግሥበትም ፈራ... እጅግ ፈራ .....


ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# <ዑደት> ቅዱሳት መካናት በትግራይ አድያማት

*«በመንፈስም ጌታ ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፤ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት በጫካ ተቀመጠ፤ ሰይጣንም ይፈትነው ነበር፤ ከአራዊት ጋርም ተቀምጦ ነበር።» /ማር. 1፥13/።*



*የዘገባ ቡድኑ ስለ ጉብኝቱ ዕቅድ ከንዑስ ማዕከሉ ጸሐፊ ጋር ውይይት ሲያደርግ*

ከካቲት 28 ቀን፥ የዐቢይ ጾም መግቢያ፥ ጀምሮ በሦስት የትግራይ አህጉረ ስብከት በሚገኙ ገዳማት፣ አድባራትና ታሪካዊ ቦታዎች ለማከናወን የታሰበው የጉዞ ዘገባ በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይቶ የመጋቢት ወር በባተ ኻያ አንደኛው ቀን ላይ እንገኛለን። እንደ ማኅበራችን አገልግሎት መዋቅር የወዲህና የወዲያው መሰናዶ /ቅድመ ዝግጅት/ ከተጠናቀቀ በኋላ በዚህ ቀን ወደ መንገድ ለመግባት ቁርጥ አሳባችን ኾነ። ዑራኤል መልአክ የዶሮውን ክንፍ በሚያማታበት ከሌሊቱ 11:00 ብዙም ሳይዘገይ የሥራ መሣሪያዎቻችንንና የግል ዕቃዎቻችንን ሸክፈን አውቶብስ ተራ ደረስን። ቆርጠን ባደርነው ትኬት መሠረት «መቐለ አንደኛ» በሚለው ካቻማሊ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ገብተን፥ በደረስንበት ተቀመጥን፥ የጉዞውን መጀመር መጠባበቅ ያዝን። «እግር አድራሽ እንጂ ተጓዡ ልብ /ሐሳብ/ ነው» እንደ ሚባለው ጋራ ቁልቁለቱ ሳያሰናክለው ከአውቶቡሱ ቀድሞ ትግራይ በገባው ሐሳባችን ምናባዊ ጭውውት ጀመርን።

ለጉዞው ከተዘጋጀነው ሦስት የቡድኑ አባላት መካከል ለትግራይ በተለይም ደግሞ ለመቐለ ከተማ እንግዳ የኾነ የለም። እኔና ዲያቆን መርሻ ከመቐለ ባናልፍም የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ ባለሞያችን የትናየት እንዳያፍሩ ግን በአዲግራት - ደብረ ዳሞ ገዳምን፣ በአክሱም - ርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮንን፣ በውቅሮ - የአብርሃ ወአጽብሓ ውቅር ቤተ ክርስቲያንን፣ በሽሬ እንዳሥላሴ ደግሞ የቆየፃ አቡነ ሳሙኤል ገዳምን የማየት ዕድል ገጥሞታል። የአሁኑ ጉዟችን ከቀድሞው የሚለየው ጊዜ ወስደን፣ ከከተማ ወጥተን፣ ወደ ገጠር ገብተን፣ ቆላውን ወርደን፣ ደጋውን ወጥተን በዚያው ውለን እያደርን በቁጥር በርከት ያሉ ጥንታውያን ገዳማትን፣ አድባራትንና ታሪካዊ ቦታዎችን በስፋት የምንቃኝበት በመኾኑ ነው።

የገዳማቱና አድባራቱ አተካከል ቅድመ ታሪክና የታሪክ ጊዜያት፣ የሕንጻ አብያተ ክርስቲያናቱ ዐቅድና የአስተዳዳራቸው ሥሪት አጥጋቢ ጥናትና ትንታኔን ይጠይቃሉ። ቅዱሳት መካናቱና ታሪካዊ ቦታዎቹ በገጻቸው፣ በከርሳቸውና በዙሪያቸው አካብተው ለትውልድ ያቆዩአቸው መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶች በጥልቀት መታየት፥ በቅርበት መደመጥና መዳሰስ ያስፈልጋቸዎል። በዘመን ርቀት፣ በመረጃዎች መውደም፣ መጥፋት ወይም ተቆፍረው ያለመውጣት የተነሣ በቃለ አፍ እየተነገሩ በእምነት በሚቀበሉትና በምርምር በሚገለጹት መካከል ያለውን ክፍተት ለማቀራረብ፣ ሕዝብ ማንነቱንና ታሪካዊ ቅርሶቹን አንብቦ ለመረዳት፣ ለመከባከብና ለመጠበቅ ብቃት ይኖረው ዘንድ እንዲህ ያሉት ጋዜጣዊ የዘገባ ዕቅዶች እንደ ማሟያ፣ እንደ ማነጻጸሪያም ያገለግላሉ የሚል እምነት አለኝ። ከምድር በላይና በታች በሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችዋ፣ በጥንታዊ የሃይማኖትና የመንግሥት ማዕከልነቷ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት መሠረትና ከፍተኛ ትርጉም ያላት ትግራይ ደግሞ ለዚህ ተግባር ዓይነተኛ መነሻና ምን ጊዜም የማይቀንስ መስሕብነት ያላት ናት።

አሳባችን ከተግባራችን እየቀደመ እንዲህ ቢያወጣና ቢያወርድም ገብተን የተቀመጠንበት አውቶቡስ ሞተሩን እያሞቀ በሚያወጣው ጭስ ከሚያፍነን በቀር ለመንቀሳቀስ አልፈቀደም። የተጓዡ ጭንቀትና ጥድፊት ቁብ የሰጠው አይመስልም። ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ሊሆን «ፍርቅ ሰዓት» /30 ደቂቃ/ ቀርቶታል። ትዕግሥታቸው የተሟጠጠና ቀድም ብለው ትኬት ያልቆረጡ ተጓዦች ሁለት ቀናት ለሚወስደው ጉዞ አስተማማኝ አውቶቡስ ላይ «መሰቀል» እንዳለባቸው ወስነዋል። መናኸሪያውን ለቀው ለመውጣት ጥቂት ተጓዦችን ብቻ በመጠባበቅ ላይ በሚገኙት መቐለ ሁለተኛና ሦስተኛ አውቶቡሶች ተሳፍረው ከዐይናችን ተሰወሩ። ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ኾነ። ወንበር ይዞ ተደላድሎ የተቀመጠው ተሳፋሪ ሁሉ ለአውቶቡሱ ሠራተኞች አቤቱታውን አቀረበ። ሁነኛው ምላሽ ዘግይቶ ተሰጠ። አውቶቡሱ «ለግዳጅ» እንደ ሚፈለግ ተነግሮን ቀድመን ትኬት የቆረጥነው ተጓዦች ገንዘባችን ተመለሰልን። ከዚህ በኋላ ያለው አማራጭ ጉዞውን በይደር ማቆየት አልያም በተገኘው አውቶቡስ መሳፈር ነበር። በእኛ በኩል «አሳባችንን የቆረጥን» በመኾኑ ጉዟችንን ማሳደር አልፈለግንም፤ *«ዉፈር ወቅደም!!»* እንዲል።

በአውቶቡሱ የኋላ ኪስና የውስጥ አካላት የተሸጎጡትን፣ በፖርቶ መጋላው ላይ የታሰሩትን ጭነቶች አውርዶ ተተኪ መኪና ለማግኘት የነበረው መራወጥ አስቂኝም አሳዛኝም ትዕይንት ነበረው። የዘርና የቋንቋ ልዩነት ሳይገድበው በአጭር ጊዜ ተላምዶ ወግ ይዞ የነበረው ተጓዥ «ለግዳጅ» በተወሰደበት አውቶቡስ ሳቢያ ትርምሱ ወጣ። በተጓዥ መካከል በቆይታ የተገኘው





www.eotcmk.org


ወዳጅነት ግን ለቅጽበት በተፈጠረው ትርምስ አልተሰረዘም:: ለዚህም ዲያቆን መርሻና የትናየት ተቀያሪ አውቶቡስና ማለፊያ መቀመጫ ይዘው ሊቆዩኝ ሲሯሯጡ አንጻራዊ ብዛትና ክብደት የነበረውን የሥራ መሣሪያችንን በመጠበቅና በምትኩ ወዳገኘነው አውቶቡስ በማዘዋወር የተራዱንን ሁለት ትግራዋይ ወጣቶች በምሳሌነት ልጠቅሳቸው እወዳለሁ፤ ስማቸውን ጠርቼ ለማመስገን ባለመቻሌ ደግሞ አዝናለሁ::

«ከመቅረት መዘግየት ይሻላል» /Better late than never/ እን ዲሉ በቅያሪው ባገኘነው አውቶቡስ የመጨረሻ ወንበር ላይ ለሰባት ተቀመጠን:: ከጠዋቱ 2:30 ገደማ ከአዲስ አበባ አውቶቡስ መናኸሪያ ተንቀሳቀስን - የአባ ዳኘው ፈረስ «ወዳቀናበቱ» የትግራይ ማእከል መቐለ:: ተጨናንቀን ብንቀመጥም አላዘንም:: ሰውነቱ የዛለ በትና እንቅልፍ የሚያናውዘው ቢኖርም ራሱን መሸከም ያቃተው አንገቱን በጓደኛው ትከሻ ላይ ዘንበል አድርጎ ለማረፍ አይከለከልም:: ነቅቶ በዕውኑ ተቀምጦ የሚሄደውንም ኾነ ተኝቶ በእንቅልፍ ዕረፍት ያለውን የሚያ ውከው አንድ ነገር ብቻ ነበር:: በአገራችን መንገዶች ሁኔታ በአገር አቋራጭ አውቶቡሶች የኋላ ወንበር ተቀምጣችሁ የሄዳችሁ ሁሉ የምታውቁት ነው- «የከፍታ ዝላይ»:: በዚያውም ላይ የተሸከርካሪው እርጅና ሲታከልበት የተጓዡ ስጋት ያይላል:: በተለይም አውቶቡሱ በሚንገጫገጭበት ወቅት እንቅልፍ ያሸነፋቸው ተጓዦች ከተደገፉት የብረት ቋሚና የመቀመጫ ወንበር ጋር ሲላተሙ ማየት ያሳቅቃል - እንደ ዛፍ ላይ እንቅልፍ::

በተለዋጭ እንዲሁም ሙሉ እድሳትና ጥገና በሚጠይቁት አስፋልት መንገዶች ላይማ ችግሩ የባሰ ነበር:: ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንና ለለጋሽ መንግሥታት ምስጋና ይድረሳቸውና ከአዲስ አበባ እስከ መቐለ ካለው 778 ኪ.ሜ መንገድ ውስጥ ቀላል የማይባለው ርቀት በአዲስ መልክ የተሠራ በመኾኑ የአጠውቶቡሳችንን ድካም አግዞልናል:: ያም ኾኖ ሐይቅ ከተማ ደርሰን ለማደር የቻልነው ከምሽቱ አንድ ሰዓት በኋላ ነበር፤ በየመሀሉ አውቶቡሳችን ቢያንስ ለዐሥርና ዐሥራ አምስት ደቂቃ በተደጋጋሚ እየቆመ መጠገን ነበረበትና:: በተለይም በአርማኒያ ከተማ መውጫ ላይ ከግማሽ ሰዓት ያላነሰ ለመጠበቅ ተገደናል::

በበነጋው ካረፍንበት ሐይቅ ከተማ ከማለዳው 11:00 ተነሥተን ቆቦ ላይ ቁርስ ከተበላ በኋላ እስክ ረፋድ ድረስ በመልካም ሁኔታ ለመሄድ ቻልን:: የራያ ኦዘቦ ወረዳ ከተማ ከሆነችው መኾኒ ለመድረስ ሁለት ኪ.ሚ ያህል እንደ ቀረን የሚንከባለል ብረት ድምፅ ተሰማ:: የአውቶቡሱ - መኾኑ ነው:: ለመጨረሻ ጊዜ በሚመስል መልኩ አውቶቡሳችን ቆመ:: ረዳት ሠራተኞቹና ሹፌሩ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ከአንድ ሰዓት በላይ ቢጥሩም ሳይሳካላቸው ቀረ:: ከነአካቴው ሹፌሩ የተጓደለ ዕቃ ለመግዛት ብሎ በአልፎ ኺያጅ ሎንቺና ወደ መኾኒ ከተማ አቀና:: የአጠውቶቡሱ ውስጥ ወበቅ ከውጩ የፀሐይ ቃጠሎ ያልተሻለ ነው:: እኛም እንደ ሾፌሩ የራሳችንን አማራጭ ወሰድን:: ጓዛ ችንን ጠቅልለን በሌላ አውቶቡስ በመሳፈር መኾኒ ከተማ ገብተን ከሁነኛ ቦታ ዐርፈን ጠበቅነው:: ከሰዓታት ቆይታ በኋላ አፍንጫውን ወደ እኛ ቀስሮ የጥርጊያ መንገዱን አቧራ አንሥቶ ወደ ጎን እየተወ ካለንበት ደረሰ::

በመጠናቸው የተለያዩ ሁለት አውቶብሶችን አፈራርቀን፥ ጉዞ በጀመርን በሁለተኛው ቀን፥ መጋቢት 22 ቀን 1997 ዓ.ም፥ 778 ኪ.ሜ ርቀት አካለን መቐለ ከተማ ገባን:: ንጉሠ ጽዮን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም በአህያዮቱና በአህያዮቱ ግልገል በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ ከቤተ ፋጌ ወደ ኢየሩሳሌም የገባ በት፥ ቤተ መቅደሱን የዞረበት ጥንተ ዕለትም መጋቢት 22 ቀን ነበር:: /መጽሐፈ ሥንክሳር፡ መጋቢት 22 ቀን 1993 ዓ.




ም፥ ገጽ 88:: ለእኔ የተከሰተልኝ አስገራሚ መመሳሰል ነው:: የቀኑና የጉዟችን ሁኔታ መግጠም ብቻ ሳይሆን በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንዑስ ማዕከል ጽ/ቤትና አባላት የተደረገልን አቀባበልም እንዲሁ ምኞት የተሞላበት፥ ድካምን የሚያስረሳ፥ መንፈስን የሚያበረታ ነበር፤ በርግጥም እንግዳ ተቀባይ ከኾነው ሕዝብ የተገኙ፥ በመካከሉም የሚኖሩ በመኾኑ እኛን በቤታቸው ለመቀበል የነበራቸው መቀዳደም ብዙ ላያስገርም ይችላል:: «......ብዙ ሕዝብም ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎችም ከዕንጨቶች ጫፍ ጫፉን እየቆረጡ በመንገድ ያነ ጥፉ ነበር::» እንዳለ:: ማቴ.21፡8-9::

በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንዑስ ማዕከል ጽ/ቤት ጋር በመኾን ከዛሬ ጀምሮ መቐለ ከተማ ውስጥ ለምንቆይባቸው ጥቂት ቀናት የመስተንግዶ ቅድሚያውን የወሰዱት በመቐለ ዩኒቨርስቲ እንዳ ኢየሱስ ካምፓስ መምህራን የኾኑት መምህር ደረጀ አሸብርና ባለቤታቸው ወ/ሮ ትዕግሥት አይታ፤ ዲያቆን ኃይሉ ተረፈ እና ዲያቆን ታደሰ አያሌው ናቸው:: ከሞቀ መስ ተንግዶአቸው ባሻገር ጉዟችንን ለማ ሳካት የሚረዱ አጠቃላይ አሳቦችን በመስጠት፥ ለሥራችን አግባብነት ከነበራቸው አካላት ጋር የነበረንን ግንኙነት በማቀላጠፍ በእጅጉ ስለ ተባበሩን በአንባብያን ስም ልናመሰግናቸው እንወዳለን::

ይቅርታውና ቸርነቱ ለዘላለሙ በእኛ ላይ ይኑርና እንደ መጽሐፍ ሥንክሳር አገላለጽ ቀጣዩ መጋቢት 23 ቀን የአይሁድ ማኅበር በጌታችን ላይ ሊመክሩ በቀያፋ ቤት የተሰበሰቡበት



www.eotcmk.org

ነው። ሦስታችን የልዑካን ቡድኑ አባላት ግን በመቐለ ንዑስ ማዕከል ጽ/ቤት ከንዑስ ማዕከሉ ሰብሳቢ ዲያቆን ዳንኤል ገብረ መድኅን፥ ከንዑስ ማዕከሉ ጸሐፊ ዲያቆን የማነ ኃይሉ ጋር ረፋድና ምሽት ላይ የተሰበሰብነው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ለሦስት አህጉረ ስብከት /ምሥራቃዊ፣ ምዕራባዊና ማዕከላዊ ትግራይ አህጉረ ስብከት / በተጻፈልን ደብዳቤ መሠረት ለመዘገብ በመነሻነት የያዝናቸውን የጉዞ ቦታዎች /ገዳማት፣አድባራት፣ ታሪካዊ ቦታዎች/ ዝርዝር ለይተን ቅደም ተከተል በማውጣት የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት በተጨማሪም በዘገባችን ወቅት በየሥፍራው በሚገኙ የንዑስ ማዕከሉ ወረዳ ማዕከላት ተቀብለው የሚተባበሩንን አባላት ማግኘት ይኖርብናል። በትግራይ ያለ ጽሑፍ ፈቃድ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ለማከናወን አዳጋች መኾኑን በቆይታችን አረጋግጠናል። የፎቶና የቪድዮ ካሜራ ባለሞያው የትናየት ሥራውን ከዚህ ስብሰባ ጀምሯል።

ዲያቆን የማነ የቦታዎችን ዝርዝር ከነ አንጻራዊ ብልጫቸው /ልዩ ገጽታቸው/ ያብራራል፤ የመንገድና የመጓጓዣ ሁኔታዎችን የሚወስዱትን ጊዜ መረጃ ያቀርባል። እኛ ያለንን አጠቃላይ አቅም እያገናዘብን እናጤናለን። በዚህ መልክ ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን ውይይቱ ቀጠለ። እንዳለን ጊዜ ፣ የሰው ኃይልና የበጀት አቅም መጠን በዘገባችን የምንሸ ፍናቸው ቦታዎች ዝርዝርና የአካሄድ ቅደም ተከተል ተወሰነ።

ዲያቆን የማነ በየሀገረ ስብከቱና ወረዳ ማዕከላቱ አስፈላጊ የኾኑ ሰዎችን ለማግኘት ስልኩን ደጋግሞ ይመታል። መለስ በሎ ከእኛ ጋር ሐሳብ ይለዋወጣል። እኛን ለደ ወሉላቸው ሰዎች ያስተዋውቃል። በግል ማስታወሻው ሐሳቦችን ያስፍራል። ንግግሩን ሲቋጭ «ጨለ»፤ «የቐንየለይ» ይላል። በአማርኛ «እሺ፤ ያቆይልኝ፤ ያሰንብትልኝ» ማለት ነው። እኛም እንዲሁ ዲያቆን የማነ ሃይሉንና የንዑስ ማዕከሉን ሰብሳቢ ዲያቆን ዳንኤል ገብረ መድኅንን ከነቤተሰቡ ልናመሰግናቸው እንወዳለን። በእነርሱ የላቀ ትብብር የተዘጋጀውን የጉዞ ዕቅድ ቅኝታችንን ከትግራይ ክልል ማዕከል መቐለ ከተማ ልንጀምር ነው። በነገራችን ላይ የትግርኛ ቋንቋን ለመናገር እንጂ ሰምቼ ለመረዳት እንደ ማይቸግረኝ ዲያቆን መርሻና የትናየት መዝግ በውልኛል - «ሠናይ ምክትታል ምስምድላዋትና፤» መልካም ቆይታ ከዝግጅታችን ጋር።

* * *

በሰሜናዊ የአገራችን ክፍል የሚገኘው የትግራይ ክልል በምሥራቅ የአፋር ስምጥ ሸለቆ፣ በደቡብ ምዕራብ ደግሞ የሰሜን ከፍተኛ ተራሮች መካከል ያለ ነው። ይህም ትግራይ ከ600 እስከ 3000 ሜትር ከባሕር ጠለል በላይ ያላቸው ልዩ ልዩ መልክአ ምድራዊ ገጽታዎች እንዲኖሩት አስችሎታል። የቆዳ ስፋቱ 53,638 ስዌ ዬር ኪ.ሜ ገደማ ነው። ከ 3.6 ሚልዮን የክልሉ ነዋሪ /ኩናማ፣ኢሮብ፣ ትግራይ/ መካከል 95.5 በመቶው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ነው። 83 በመቶው የሕዝቡ ኑሮ በግብርና ላይ የተመሠረተ ነው።

እንደ ትግራይ ቱሪዝም ቢሮ መረጃ በክልሉ ከ120 በላይ ከአለት ተፈልፍለው የተሠሩ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ዘመናትን በተሻገረ የሕንጻ ጥበብና አሠራራቸው ክልሉን ቁጥር አንድ የታሪካዊና የመንፈሳዊ ቅርሶች መስሕብነት አጎ ናጽፈውታል። አብያተ መንግሥት፣ ሐውልቶች፣ መቃብሮች፣ ጥርብ የደንጊያ ቅርሶች፣ መጻሕፍት ወዘተ ትግራይን ገሃደ ትዕይንት «The open air museum» አሰኝ ተውታል። እኒህን በአካል ተገኝቶ ማየትም ለዘመናት የኋሊት መልሶ የኢትዮጵያችንን ልዩና ዕድሜ ጠገብ ሥልጣኔ ቃላት ከሚገልጹት በላይ በጥልቀት ለመረዳት ያስችላል። የተወደዳችሁ አንባብያን ሆይ፥ የኢትዮጲያ ሥልጣኔ መነሻ፣ የሃይማኖትና ቅርስ ማዕከል ወደ ኾነችው ትግራይ እንኳን በደኅና መጣችሁ፤ *ናብ መስለምታ ሥልጣነ ኢትዮጵያን ማእኸል ሓድግታትን፣ ሃይማኖትን ዝኾነት ትግራይ እንኳዕ ደሓን መፃእኹም።*

ከዚህ በመቀጠል የቅኝታችን መጀመሪያ ወደ ኾነው በመቐለ ከተማ ወደሚገኘው የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንወስዳችኋለን። ይህ ኮሌጅ በረከታቸው ይደርብንና የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ «ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኵሉን አድያማተ ትግራይ» /የአክሱምና የትግራይ አውራጃዎች ሁሉ ሊቀ ጳጳስ/ /1887 - 1983 ዓ.ም/ ትምህርት ቤትን የመሥራት፣ የማስፋፋትና ትምህርትን ለሁሉ የማዳረስ ጠንካራ ዓላማና ጽኑ ፍላጎት የተገለጸበት ነው። ስለ ብፁዓዊው ጳጳስ ዜና ሕይወትና ሥራዎች ተናግረው የማይሰለቹት የኮሌጁ አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሐላፊ ሊቀ ትጉሃን ሳእከ ታረቀና የኮሌጁ ሐዲስ ኪዳን መምህር ሊቀ ሊቃ ውንት ያሬድ ካሣ ያጫወቱ ትን እናወጋችኋለን።

*ይቆየን።*

*የክልል ትግራይ አህጉረ ስብከት አጠቃላይ መረጃዎች*

| ተ.ቁ | ዝርዝር | መለኪያ ቁጥር | መጠን | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቀሳውስት | ቁጥር | 40,693 | |
| 2 | ዲያቆናት | | 36,505 | |
| 3 | መዘምራን | | 394 | |
| 4 | የአብነት መምህራን | | 1775 | |
| 5 | ልዩ ልዩ | | 5037 | የሀገረ ስብአት ሠራተኛ |
| 6 | በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ ምእመናን | | 2,176,260 | |
| 7 | በሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገቡ ምእመናን | | 140530 | |
| 8 | በቅጽ 20 ያልተመዘገቡ ምእመናን | | 660571 | በማረሚያ ቤቶች፣በሕክምናቤቶች፣በሠራዊት ቤት ያሉ ምእመናን |
| | የምእመናን ጠቅላላ ብዛት | | 2,977,361 | |
| 9 | ገዳማት | | 220 | |
| 10 | አድባራት | | 493 | |
| 11 | ገጠር አብያተ ክርስቲያናት | | 2242 | |
| | የአብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ብዛት | | 2955 | |
| 12 | ሰበካ ጉባኤ የተቋቋመባቸው | | 2976 | |
| 13 | ሰበካ ጉባኤ ያልተቋቋመባቸው | | 180 | |
| 14 | ሰንበት ት/ቤት የተቋቋመባቸው | | 336 | |
| 15 | ሰንበት ት/ቤት ያልተቋቋመባቸው | | 2819 | |
| 16 | የካህናት ቤተሰብ ብዛት | | 318500 | |

ምንጭ፡- የ1986 ዓ.ም የትግራይ ሀገረ ስብከት መረጃ



www.eotcmk.org

# አቡነ ፊልጶስ



«መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ፤ ልዑል እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮ ድንቅ ሥራውን ይሠራል» ብሎ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 67፥35 እንደ ተናገረው ቀድሞ በዘመነ ብሉይ በሙሴና በአሮን አድሮ ደጋጎቹን /እስራኤልን/ ከግብጽ አወጣ:: ክፉዎችን ግብጻውያን የቅዱሳን የሙሴንና አሮንን ቃል ያቃለሉ እነዚህን መናፍቃን አሰጠማቸው፤ ዛሬም በጻድቁ አባታችን አቡነ ፊልጶስ ላይ አድሮ ድንቅ ሥራ ሠርቷል:: አቡነ ፊልጶስ አገራቸው ኢትዮጵያ ሲሆን የተወለዱት በሰላሌ ልዩ ስሙ ሙገር ይባላል:: ቋዓት አካባቢ የሚገኝ አገር ነው:: አባታቸው አብርሃም እናታቸው ሣራ ይባላሉ:: አባታቸውና እናታቸው በሕግ በሥርዐት ተጋብተው ይኖሩ ነበር:: እነርሱ እግዚአብሔርን እንጂ ጣዖትን አያመልኩም ነበር፤ የሀገሩ ሕዝብ ግን ድንጋይንና እንጨትን፣ ባሕርንና ተራራን፥ ጨሌን፣ ቃልቻንና ጠንቋይን እያመለኩ ይኖሩ ነበር::

ጻድቁ አቡነ ፊል ጶስ ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በአካባቢው ባለው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው ሲማሩ መንፈሳዊ መምህራቸው፡- «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» ብሎ ሲያስተምር ሰምተው በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ማለት ትርጓሜው ምንድን ነው ብለው ጠየቁ፤ እርሱም አንድነቱን ሦስትነቱንና በሰባቱ ዕለታት የተፈጠሩ 22ቱን ሥነ ፍጥረታት ጭምር በሚገባ እያስረዳ አስተማራቸው፤ ሌሎች ሕፃናት ያልጠየቁትን ምስጢር በጠየቃቸው ያ መምህር በጣም አድንቆ ስለ ቃልቻ ምንነት በሚገባ አስተማራቸው፤ በትምህርተ መስቀል እያማተቡ እየጸለዩ አጋንንትን ማውጣት እንደሚቻል በቃልቻ ላይ ጋኔን እያደረ እንደሚያስት ዐወቁ፤ ተረዱ፣ ከዚህ በኋላ አባታቸው አብርሃም ዲቁና ይቀበሉ ዘንድ ወደ ጳጳሱ አባ ዮሐንስ ዘንድ ወሰዳቸው:: ከዚያ ዲቁና ተቀብለው /ተሹመው/ ሲመለሱ ማድረግ ጀመሩ::

ካደረጉት አንዱ ይህ ነው:: ከእለታት በአንድ ቀን ቃልቻ በዓል በሚያደርግበት ተአምራት ዕለት ለአባታቸውና ለእናታቸው ሳይናገሩ ተደብቀው ከሰዎች ጋር ቃልቻ ቤት ሄዱ:: ተቀምጠው ሲመለከቱ ያ ጋኔን ያደረበት ቃልቻ ከነዝክትልትሉ ከነዙፋኑ ገባና ተቀምጦ በትምህት የጋለውን ብረት የሚልስ መስሎ ይዘይን ጀመር:: ቁጭ ብድግ እያለ እየተከባለለ ያጓራ ጀመር፤ ጻድቁ አቡነ ፊልጶስም ሠይጣን በሰው እያደረ ሕዝቡን የሚያስትበትን ዘዴ አይተው መንፈሳዊ ፍቅር መንፈሳዊ ቅናት ያዛቸው፤ እንደ አዮስያስ /2ኛ ነገ.23፥1 ተመልከት/ አቡነ ፊልጶስ ከተቀመጡበት ብድግ ብለው «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» በማለት ስመ ሥላሴን ጠርተው «ይትነሣእ»ን መዝ.67፥1-4 እየደገሙ አማተቡበት:: ቃልቻውም ለጊዜው በምትሃት ከእሳት ውስጥ ይጠብቀው የነበረው ዛር የተባለው ሠይጣን ቃልቻውን ከእሳት ውስጥ ጥሎ እንደ ጢስ ብን ብሎ ጠፋ::

ያ ቃልቻ የነበረው ሰውዬ እዚያው እሳት ውስጥ ተቃጥሎ እርር ኩምትር ብሎ ሞተ:: ለዚያ ቃልቻ ሊሰግዱና ሊያመልኩ የመጡ ሰዎች በድንጋጤ ፈዘው ቀሩ:: ከነዚያም 24 ሰዎች በጻድቁ አቡነ ፊሊጶስ ድንቅ ተኣምራት ንስሐ ገብተው ቄደር ተጠምቀው የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀብለው በሃይማኖት ፍጹማን ሆነዋል፤ የቃልቻው ልጅ በአጋንንት ቁራኛነት ተይዞ ሲያጓራ አቡነ ፊልጶስ የእመቤታችንን «ሰላም ለኪ» ጸልየው ውኃው ላይ እፍ ብለው ቢረጩበት ያ የጠንቋዩ ልጅ ተፈውሷል:: ጋኔኑም በውሻ ተመስሎ እየጮኸ ወጥቶ ሄዷል::

ልዑል እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ አድሮ የሚሠራው ሥራ እጅግ ድንቅ ነው:: ያን የዳነውን ልጅ አብነት አድርገው ብዙዎቹ በሽተኞች ወደ እርሳቸው እየመጡ ተፈውሰዋል:: ከዚህ በኋላ አባታቸው ሚስት ያገቡ ዘንድ ጠየቋቸው:: እርሳቸውም «አላገባም» ብለው በዚህ ምክንያት ወደ ጌታ አመልክተው መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ወደ ደብረ ሊባኖስ እንዲሄዱ በሕልም ነገራቸው:: በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል



www.eotcmk.org

መሪነት መንነው ደብረ ሊባኖስ በ15 ዓመታቸው ገብተው ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥርዓተ ምንኩስናን ተምረው በእኒሁ በመንፈሳዊ አባታቸው እጅ መነኮሱ፤ ታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዐረፉ በኋላ ነሐሴ 25 ቀን ኤልሳዕ በአባታችን እግር ተተክተው ዕጨጌ ሆነው ተሹመው ሳለ ጥቅምት 24 ቀን ዐረፉ:: ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሞተውን ዲያቆን አሥነስተው «ፊልጶስ በእኔ እግር ይሾም፤ በእርሱ ዘመን በእርሱ ትምህርት ስሜ በዓለም ይታወቃል:: እርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትጸናለች» ብለው ላኩ፤ የተነሣውም ዲያቆን ይህን ተናግሮ ተመልሶ ዐርፎአል::

ጻድቁ አቡነ ፊልጶስ በደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ ሁነው በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ሥርዓተ ገዳምን በሚገባ አስተካክለው ሠርተው ሲያስተዳድሩ ኢትዮጵያን ከ12 ተካፍለው እርሳቸውና ከእርሳቸው ጋር የነበሩ 11ዱ ንቡራነ እድ አባቶች ሀገራችን ኢትዮጵያን በትምህርታቸው ቀድሰዋታል፤ ሃይማኖትን አጽንተዋል፤ ሕዝቡን በሚገባ አስተምረዋል፤ በአቡነ ፊልጶስ ጊዜ የዐፄ ይኩኖ አምላክ ልጅ ንጉሥ ዓምደ ጽዮን በደብረ ብርሃን ከተማ ነግሦ ሳለ ጠንቋዮች ተሰብስበው ወደ ንጉሥ ዓምደ ጽዮን የእንጀራ እናቱን አግብቶ እቴጌነት አድርሶላት ይዧት ሲኖር የኢትዮጵያ መምህራን ቢያስተምሩትና ቢመክሩት አልቀበልም ቢላቸው «የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነና እግዚአብሔርም ቃል በቃል የሚያናግረው ጻድቁ /ሰማዕቱ/ አቡነ ፊሊጶስ በደብረ ሊባኖስ ገዳም እንዳለ ዝናውን ስለ ሰማን እርሱ መጥቶ ቢመክረውና ቢያስተምረው ይሰማል» ብለው ወደ እርሳቸው መልእክተኛ ላኩ:: ጻድቁ አቡነ ፊልጶስም ሰምተው በጣም አዘኑ፤ ሳይፈሩ በቆራጥነት መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ የተቀበለውን መከራ ሊቀበሉ በገዳሙ ከአሉ አባቶች ተሰናብተው በእርሳቸው ፋንታ ሌላ ዕጨጌ ተክተው ሰማዕትነት ሊቀበሉ ከሠላሳ ስምንቱ መንፈሳውያን ልጆቻቸው ወይም ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር ንጉሥ አምደ ጽዮን ካለበት ደብረ ብርሃን ከተማ ሄዱ::

ንጉሥ ዓምደ ጽዮንን አስጠርተው ለብቻው ቢመክሩት ቢያስተምሩት የማይሰማቸው ሆነ:: ከዚህ በኋላ «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል» የሚለውን በረቂቅ ስንሰለት አስረው አውግዘው ለዩት:: የማቴ.16፥19:: ንጉሥ ዓምደ ጽዮንም ተቆጥቶ በአፋቸውና በአፍንጫቸው ደም እስኪወጣ አስደበደባቸው:: እርሳቸውም የክርስቶስን ሕማማተ መስቀል እያሰቡ በደስታ መከራውን ይቀበሉ ጀመር፤ ንጉሡ ተቆጥቶ በብረት አለንጋ ቆዳቸው አልቆ ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው እስኪታይ ድረስ አስገረፋቸው:: ከግርፋት የተነሣ በአንገታቸውና በጀርባቸው ላይ ያለው ቆዳ ተልጦ ወደ ታች ተንጠለጠለ፤ የሥጋቸውንና የቆዳቸውን ቅራፊ ደቀ መዛሙርቶቻቸው እና የደብረ ብርሃን ከተማ ሕዝብ ለበረከት እየወሰዱ ድውያንን ፈውሰውበታል፤ ሙታንን አሥነስተውበታል:: መሬት ላይ የፈሰሰው ደማቸው እሳት ሆኖ 300 ወታደሮችን አቃጥሎ አባኖቸዋል:: እንደ ነቢዩ ኤልያስ /2ኛ ነገሥት 19፥15/ እነዚያን ተጠራጣሪዎች ወታደሮች በእሳት እንዳቃጠላቸው ጻድቁ አቡነ ፊሊጶስም ደማቸውን በእግዚአብሔር ኃይል እሳት አድርገው 300 ወታደሮችን አላስቀርብ አሉ:: ወታደሮቹም ወደ ንጉሥ ዓምደ ጽዮን ሄደው: - «ከአካላቸው የሚወጣ ደም እሳት ሆኖ እየነደደ አላስቀርብ አለን» ብለው ነገሩት፤ እርሱም «300 እንሥራ ወስዳችሁ ውኃ ቀድታችሁ እሳቱን በውኃ አጥፍታችሁ ቶሎ ግደሉልኝ» ብሎ አዘዛቸው፤ እነሱም ውኃውን ቀድተው ወስደው ቢያፈሱበት «ወተለአለ ነበልባሉ» እንዳለ የእሳቱ ነበልባል ከቀድሞው ይልቅ ከፍ ከፍ አለ፤ ጋዝና ደረቅ እንጨት እንደ ተጨመረበት ሆኖ ነበልባሉ ወደ አየር እስከ ደመና ድረስ ወጣ፤ ወታደሮቹም ሸሹ፤ ንጉሡም ከቤተ መንግሥቱ ወጥቶ ሸሸ:: የእሳቱ ነበልባል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሊገባ ነውና ጻድቁ አቡነ ፊልጶስ ወደ እግዚአብሔር ጸልየው እሳቱን እንዲጠፋ አደረጉ፤ እሳቱ ከጠፋ በኋላ ያ ልቡ እንደ ፈርዖን ልብ የደነደነው ንጉሥ ዓምደ ጽዮን ከነሠራዊቱ ከሸሸበት ተመልሶ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አቡነ ፊልጶስንና እርሳቸውን ተከትለው የመጡትን ደጋጎች መነኮሳትን አስጠርቶ ልብሳቸውን አስወልቆ ራቁታቸውን ከእርሱና ከሠራዊቱ ከሕዝቡም ፊት እንዲቆሙ አደረጋቸው::

የሀፍረተ ሥጋቸውን ፀጉር ሠራዊቱ እየነጨ በሕዝቡ ፊት እያዞሩ:- «አንተ መነኩሴ ከአንተ ጋር አብረው ካሉ መነኮሳት ጋር አብረህ እፈር» ይሏቸው ነበር:: ጻድቁ አቡነ ፊልጶስም «እኛ የያዝነውን እናንተም ይዛችኋል፤ ምን ያሳፍረናል፤ እናንተ እንጂ በመድኃኔዓለም ክርስቶስና በመላእክቱ ፊት ከመልካም ሥራ ራቁታችሁን ሆናችሁ በቆማችሁ ጊዜ እፈሩ እንጂ» ብለው መለሱላቸው:: ራቁታቸውን አንድ ቀን ሙሉ ገበያና ከተማውን እያዞሩአቸው ውለው ማታ ራቁታቸውን ሳሉ አንበሳን የማይፈሩ ኃይለኞች ውሾችን ለቀቁባቸው፤ የጻድቁ አቡነ ፊልጶስ እጅ ታስሮ ነበርና ሥር ወድቀው ይሰግዱላቸው ጀመር፤ ለዳንኤል አንበሶች እንደ ሰገዱ:: ዳን.6፥16-23፤ ተረፈ ዳንኤል ተመልከት/:: እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ አድሮ የሚሠራው ሥራ ድንቅ ነው፤ ከዚህ በኋላ አባታችንን በጋለ ብረት ከግንባራቸው እስከ ሆዳቸው ከተቧቸው፤ ከእርሳቸው ጋር የነበሩ ቅዱሳን መነኮሳትና መነኮሳዪያት አንለይም ብለው እንደ እርሳቸው ተከትበው ወደ ትግራይ በረሃ ተሰደው ሲሄዱ ከአሳደዷቸው ወታደሮች አንዱ አንድ ዐይና ነበርና እድናለሁ ብሎ አምኖ ከቁስላቸው የሚፈሰውን ደምና መግል ቢቀባ ዐይኑ በራለት፤ እርሱን አይተው ብዙዎቹ ከተለያዩ በሽታዎች ድነዋል፤ ከአጋንንት ቁራኛነትና ሽባነት፤ ከእውርነትና ከዲዳነት፣ ከተለያየ ጭንቀትና ችግር ድነዋል፤ ዛሬም ብዙዎቹ ስማቸውን እየጠሩ፣ ዝክራቸውን እየዘከሩ፣ በዓላቸውን እያከበሩ፣ ጠበላቸውን እየተጠመቁ፣ እምነታቸውን እየተቀቡ አምነው ከተለያዩ በሽታ የሚድኑ ምእመናን ብዙዎች ናቸው፤ «አስበ ጻድቅ ለበረከት ውእቱ፤ የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» ብሎ ጠቢቡ ሰሎሞን እንደ ተናገረው /ምሳ.10፥7/:: ዛሬም ብዙዎቹ ምእመናንን የበረከት ዝክራቸውን ዘክረው በዓላቸውን አክብረው ቤትና ንብረታቸውን እንዲሁም ሕይወታቸውን ልጆቻቸውን በአባታችን በአቡነ ፊልጶስ አማላጅነት በበረከት በጤና በሰላም በፍቅር በደስታ ተጠብቀው የሚኖሩ ምእመናን ብዙዎች ናቸው::



www.eotcmk.org

ንጉሥ ዓምደ ጽዮን ከሞተ በኋላ ልጁ ሠይፈ አርእድ ነግሦ ሳለ በዘመነ ዮሐንስ የልደት በዐል ዐማኑአል ማክሰኞ ሆኖ በዓለ እግዚእ ረቡዕ፣ ዐማኑኤል ኀሙስ ሆኖ በዓለ እግዚእ አርብ በሆነ ጊዜ በጠዋት ቀድሰህ እንብላ ብሎ ንጉሡ ዓምደ ጽዮን አባታችን አቡነ ፊልጶስን ጠየቃቸው፤ እርሳቸውም «አይሆንም» አሉት:: በዚህ ምክንያት ከ17 ልጆቻቸው ጋር ደራ ወደ ተባለ በረሃ ተሰደዱ:: በዚያ የሚበሉት አጥተው ለሦስት ወር ሣር እንደ ሳም እየበሉ ቆይተዋል:: ከዕለታት አንድ ቀን ያልተጠመቀ ሰው ጦር ቢወረውርባቸው ከእርሳቸው ጋር የተሰደደች አንዲት መበለት ጻድቁ አቡነ ፊልጶስ ከሚሞቱ እኔ ልሙት ብላ ሄዳ ከፊታቸው ብትቆም፤ የተወረወረው ጦር ልቧን ቢወጋት ሞተች:: በእርሳቸው ምክንያት ሰማዕትነት ተቀብላለች::

አባታችን አቡነ ፊልጶስ ጦር የወረወረባቸውን ሰውዬ ቢረግሙት ከሁለት ተሰንጥቆ ሞተ፤ «በጻድቅ ላይ ሸንገላን የሚናገሩ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ /መዝ.30፥18/:: እንዲል:: ከደራ በረሃ ተመልሰው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ዝዋይ ደሴት ተሰደው በደሴት ውስጥ እግራቸውን ታስረው ሳሉ በሽተኞችን ፈውሰዋል፤ በዚያ አካባቢ የሚኖር አንድ እስላም ልጁ ታሞበት በየጠንቋዩ ቤትና ባለመድኃኒተኞች ቤት ቢወስደው የማይድን ሆነ፤ በልጁ ያደረ ሰይጣን «ከጻድቁ አቡነ ፊልጶስ በቀር የሚያስወጣኝ የለም» ቢል አባቱ ሰምቶ እርሳቸውን ጠየቀ:: እርሳቸውም «ታምናለህን?» አሉት፤ አዎን፥ አላቸው:: የእጃቸውን እጣቢ ቢሰጡት ልጁ ያን ተጠምቆ ዳነ:: አባቱ ሳያምን ቀረ፤ በዚህ ጊዜ ያ ሰይጣን ሰባት ጓደኞቹን ይዞ እንደገና በልጁና በቤተሰቦቹ ላይ አደረ፤ እንደ አውሬ ይነካከሱ ጀመር:: ያ እስላም ለአባታችን ሄዶ ነገራቸው:: «ለምን አላመንክም?» አሉት:: «አምናለሁ» አላቸው፤ የእጃቸውንና የእግራቸውን እጣቢ ቢሰጡት ወስዶ ቢረጫቸው ድነውለታል፤ እርሱም በአባታችን በአቡነ ፊልጶስ ትምህርት ከነ ቤተሰቦቹ አምኖ ተጠምቆ ክርስቲያን ሆኗል፤ እኚህ አባት ከልዑል እግዚአብሔር ብዙ ቃል ኪዳንና በረከት ተቀብለዋል:: ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ፤ ከመርጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ» ብሎ ክቡር ዳዊት ልዑል እግዚአብሔር ከቅዱሳን ጋር ቃል ኪዳን መግባቱን እንደ ተናገረ:: መዝ.88፥3:: እኚህ አባት 74 ዓመት ከ10 ወር በሆናቸው ጊዜ ሐምሌ 28 ቀን ከዚሁ ከመከረኛው ዓለም ዐርፈዋል:: በዕረፍታቸውም ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ዘንድ የቅዱሳን ሞት የከበረ ነውና ቅዱሳን መላእክት እመቤታችንን፣ ነቢያት ሐዋርያትን፥ ጻድቃን ሰማዕታትን አስከትሎ መጥቶ ብዙ ቃል ኪዳን ሰጣቸው:: ነፍሳቸውንም በእልልታ በዝማሬ መላእክት ወደ ገነት አስገቧት፤ «ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር፤ የጻድቅ ሰው ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው፤» እንዳለ:: መዝ 115፥6:: ጌታ ለአባታችን ለአቡነ ፊልጶስ እንዲህ አላቸው:-

ስለ እኔ ተሰደሃልና፥ ብዙ መከራን ተቀብለሃልና ቤተ ክርስቲያንህን የሠራ ያሠራ፣ ዝክርህን ያዘከረ፣ ለቤተ ክርስቲያንህ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ፣ መገበሪያ ስንዴ የሰጠውን፥ ለተጠማ፥ በስምህ ቀዝቃዛ ውኃ ያጠጣውን፥ ለተራበው ያበላውን፥ ለታረዘ ያለበሰውን፥ ያንተን መከራና ያንተን ስደት የሚናገር የገድልህን መጽሐፍ የጻፈውን ያጻፈውን ሰው ከቅዱሳን፥ ከሐዋርያትና ጻድቃን ሰማዕታት ጋር ስሙን በመንግሥተ ሰማያት በቀለመ ወርቅ እጽፈዋለሁ፤ ሥጋህ ከተቀበረበት ቦታ ይቅርታዬ ቸርነቴ በረከቴ በዚያ ይሆናል፤ እህልን የሚጎዳ በረዶና ብርድ፥ አንበጣና የተለያየ ትል አይኖርም፤ ወዳጄ ፊልጶስ ሆይ፥ እነሆ ለአንተ ሰባት አክሊል አዘጋጅ ቼልሃለሁ:: አንዱ ስለ ድንግልናህ፥ ስለ ቅድስናህ፥ አንዱ ስለ እኔ ብለህ መከራን ታግሠህ ሰማዕትነት ስለ ተቀበልህ፤ አንዱ ጣዖት ያመልኩ የነበሩትን ሕዝብ አስተምረህ በሃይማኖት ስለ አጸናኽልኝ፤ አንዱ ስለ እኔ ስትል ስለ ደረሰብህ ስደትና ሣር እስከ መብላት ስለ ደረሰብህ ችግርና መከራ፤ አንዱ ከልጅነትህ የተነሣ ሳትፈራ አማትበህ ያን ቃልቻ ስለ አጠፋህ፤ አንዱ በንጽሕና በቅድስና ቅዱስ ሥጋዬን ክቡር ደሜን ስለምታቀርብ ስለ ክህነትና፣ አንዱ ስለ ፍጹም ምንኩስናህ እንደ እንጦስና እንደ መቃርስ ፍጹም ኹነህ ስለ ተገኘህ ወዳጄ ፊልጶስ ሆይ፥ ይህን ቃል ኪዳንህን ሰምተው አምነው በስምህ መልካም ነገር ያደረጉ ሁሉ ከአንተ ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይኖራሉ፤ ብዬ በራሴ ስም በእውነት ምዬልሃለሁ» ብሎ ቃል ኪዳን ገባላቸው:: የጻድቁ አቡነ ፊልጶስ ገድል ብዙ ነው:: ከብዙ በጥቂቱ ከምሉዕ በክፍሉ ምእመናን አንብበውና ተረድተው ከአባታችን በረከት እንዲቀበሉ ወይም እንዲያገኙ ይህን ጽፈናል::

*.... አነሣስቶ ላስጀመረን አስጀምሮን ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይግባው:: አሜን::*

## የሰይጣን ቀረርቶና ፉከራ

### ዱሮ እና ዘንድሮ

እከሰዋለሁ ስል አምላኩን አስክጄ፣
ሰው ንስሐ ገባ ከጽድቅ ተወዳጄ::
ወይ ገሃነመ እሳት ወይ ሲዖል ሀገሬ፣
ብቻችን ልንቀር ነው እሪ በሉ ዛሬ::
ዘራፍ!!!... ዘራፍ!!! ...
ሲዖል የሞላች ሳላስመስላት፣
ጠላት ንስሐ ጦም አሳደራት::

በዘር በቋንቋ ሳይከፈሉ፣
መግቢያ ቀዳደው ሲጠፉኝ ውሉ፣
እንኳንስ አምላክ ሕይወት የሰጠኝ፣
ስመ ቅዱሳን አንቀጠቀጠኝ::
በጾም በጸሎት ባይያዝ እግሬ፣
እጥለው ነበር አነባብሬ::
ዘራፍ! የዚያለት የድብልቅልቁ፣
ወንድ ሴት ሳይሉ ትንሽ ትልቁ፣
አገኛቸው የል በዘር ሲወድቁ::

ሃይማኖት ተረሳ በቦታ ታሠረ
ጭንቀታችሁ ሁሉ የዘር ሆኖ ቀረ::
በሃይማኖት ቢያሥሩኝ እኒያ አባቶቻችሁ፣
የሚያቃጥል ፍቅሬን አሳድሬባችሁ፣
በዘር ተወልጄ እኔ አባት ሆንኳችሁ::
ዘራፍ!!! ... ዘራፍ!!! ...
ያደክበቱ ወንዙ ሲጠራ፣
እንዲያተኩስህ እያንጠራራ
የለኮስኩልህ በደምህ እሳት፣
ላታወራ ነው የዚያን ዘር ክፋት!?
ላትመኝ ኖሯል የነዚያን ጥፋት!?
በል ጨምርበት ግፍ ከሚሉቱ፣
ይህን ከመጥቀም ያን ከመጉዳቱ፣
ሰፍቶ እንዲቆይህ የሲዖል ቤቱ::
ሲዖል ርስቱን ማን ይተዋታል!?
በዘር ተሰቦ ይገባባታል::
የዘሩን ነገር ብነካካለት፣
እየዘለለ ተከመረባት::

/ማርዬ ይግዛው፣ 1997/





www.eotcmk.org

# የባሕረ ሐሳብ <Soft Ware>

ወጣት ኃይለ ኢየሱስ እንግዳው ይባላል:: በመቐለ ዩኒቨርስቲ እንዳ ኢየሱስ ካምፓስ የሦስተኛ ዓመት የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ዲፓርትመንት ተማሪ ነው:: የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለ በባሕር ዳር ደብረ ጽዮን ሰላም አድርጊው ማርያም ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤት ደረጃ የላቀ የመንፈሳዊ አገልግሎት ተሳትፎ የነበረው ተማሪ ኃይለ ኢየሱስ በ1995 ዓ.ም ወደ ተቋሙ ከገባ በኋላ በግቢ ጉባኤው የተጠናከረ አገልግሎቱን ቀጥሏል:: በዚህም ብቻ ሳይወሰን በአካዳሚያዊ ትምህርቱ ባካበተው ዕውቀት በቤተ ክርስቲያናችን «የቁጥር ትምህርት» የሚባለውን ባሕረ ሐሳብን በቀላሉ ለመማር የሚያስችል «ሶፍት ዌር» ለመሥራት ችሏል:: የወጣቱ ጅምር ጥረት ለሌሎች አርአያ ይሆናል በሚል በዚህና በተጓዳኝ ጉዳዮች ዙሪያ አነጋግረነዋል:: እንደ ሚከተለው አቅርበነዋል:: መልካም ንባብ::



ዝግጅት ክፍል:- *ቤተ ክርስቲያን ከወጣት ምሁራን በቀዳሚነት የምትፈልገው ሞያዊ ድጋፋቸውን እንደ ኾነ ይታመናል:: ካለህበት ግቢ ጉባኤ በመነሣት በአሁኑ ወቅት ወጣቶች በዘመናዊ ትምህርት ያገኙትን ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በማዋል ረገድ ያላቸውን እንቅስቃሴ እንዴት ትገመግመዋለህ?*

ኃይለ ኢየሱስ:- እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት /ዲፓርትመንት/ የተለያየ ዕውቀትና ሞያ የምትቀስምበት ነው:: የየራሱ የትውር ዕውቀትና ተግባራዊ አፈጻጸም ያለው ነው:: ከዚህ አኳያ ባለሁበት ዩኒቨርስቲ የሚሰጡት አካዳሚያዊ ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያናችንን በልጆቿ በኩል በየዘርፉ ያሉ ጥበቦችና ባለሞያዎች ማዕከል የሚያደርጋት ነው:: እኒህ ወጣት ባለሞያዎችም ከተማሩት ትምህርት አንጻር ብዙ ጠቃሚ <application> መሥራት ይችላሉ ማለት ነው::

ዝግጅት ክፍል:- *አንተ ይህን «የአቡሻኸር /ባሕረ ሐሳብ/ ሶፍት ዌር» ለመወጠንና ለማኅልበት ያበቃህ መንሥኤ ምንድን ነው?*

ኃይለ ኢየሱስ:- ማኅበራችን ለግቢ ጉባኤያት ባዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት «ነገረ ቅዱሳን» በምንማርበት ወቅት ስለ ግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅዱሳን ስናጠና ታሪካቸው እንዴት በሲዲ ተጠናቅሮ እንደ ቀረበ ተመለከትን:: በዚያም መንፈሳዊነቱን በመሠረቱ ያለቀቀ÷ የገጻማቱን አተካከልና አደረጃጀት ዘመናዊነት አጤንን:: ከዚህ አኳያ እኔም ለቤተ ክርስቲያኔ አንድ ነገር መሥራት አለብኝ ብዬ አመንኩ:: ወደ ተቋም ከመግባቴ በፊት የባሕረ ሐሳብን ትምህርት በድምጫም ቢሆን ለመማር የሞከርኩበት አጋጣሚ ነበር:: የእኛ የዘመን አቆጣጠር ሲታይ ብዙ ምእመናን አጽዋማት መቼ እንደሚገቡና እንደሚወጡ እንዲሁም በዓላት መቼ እንደ ሚውሉ ለማወቅ ይቸገራሉ:: በእኔ ሥራ ላይ እኛ በምንጠቀምበት የዘመን አቆጣጠር (Julian Calendar) ማንም ሰው ሊያውቀው በሚችለው መንገድ ተቀምሯል:: ይህም ወደ አውሮፓውያኑ የጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ለመለወጥ በሚያስችል መንገድ ተቀምጧል:: በመሆኑም የከበደ መስሎ የሚታየውን የስሌት ችግር ይፈታል ብዬ አምናለሁ::

ዝግጅት ክፍል:- *በጥንታዊውና ትውፊታዊው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ላይ ከዘመኑ ትውልድ አቀባበል አንጻር መስተካከል ያለበት ችግር አለ ብለህ ታምናለህ?*

ኃይለ ኢየሱስ:- በእኔ ሥራ ውስጥ ትኩረት የሰጠሁት በዓላትና አጽዋማት የሚውሉባቸውን፣ የሚገቡባቸውንና የሚወጡባቸውን ዕለታትና ቀናት ማንም ሰው በቀላሉ ማስላት እንዲችል ማድረግን ነው:: የባሕረ ሐሳብን የተወሰነ ክፍል ነው የሸፈነው:: ይህንን በነባሩ ሥርዓተ ትምህርትም ማስተማር ይቻላል:: ይሁንና የእኔ ሥራ ከትምህርቱ ስፋት አኳያ ክብደቱን ለማቅለል የተሻለ አማራጭ ይሰጣል:: ሁሉም ሰው ለመማር ይችላል ማለት ነው::

ዝግጅት ክፍል:- *ስለ ሥራው ይዘት ዘርዘር አድርገህ ብታስረዳን?*

ኃይለ ኢየሱስ:- እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያናችን ብሎም አገራችን የምትጠቀምበት የዘመን አቆጣጠር - አቡሻኸር /ባሕረ ሐሳብ/ ይባላል:: ቀመሩ የቅዱስ ድሜጥሮስ ነው:: የፋሲካ በዓል እሑድ መዋሉ ቀርቶ እየተዛባ ሲያስቸግር በብዙ ሱባኤ ተገልጾለት ያወጣቸው ቀመሮች አሉ:: እኔ ስሌቱን በሶፍት ዌር ለማቀናበር የጀመርኩት በያዝነው ዓመት ኅዳር ወር ላይ ነበር:: ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት ትኩረቴም የበዓላት መዋያ ቀናት፣ የአጽዋማት መግቢያና መውጫ ቀናት ላይ ነበር:: በዚህ መሠረት እስከ ነነዌ ድረስ ያለውን ለመሥራት ችያለሁ:: በሥራው ሂደት በትምህርቱ ላይ የምንጠቀማቸውን ቃላት:- ለምሳሌ ይኸን ያህል ቀን ይገደፋል፤ ይህን ያህል ይቀራል፤ የሚለውን ወደ ስሌቱ (calculation) ለማምጣት አስቸግሮኝ ነበር፤ አንድ ቀን ያህል ዋልኩበትና ተሳካልኝ:: ከዚያ በኋላ ነው ሌሎችን ወደ ማስተካከል ሥራ የገባሁት:: በባሕር ሐሳብ ላይ የምንነሣው ከዓመተ ምሕረቱ ነው፤ ዓመተ ምሕረቱን ወስደን ከዓመተ ፍዳ /ኵነኔ/ ጋር በመደመር ዓመተ ዓለምን እናገኛለን:: ከዚያ በኋላ ዓመተ ዓለሙን እያካፈልን፣ የሚደመሩትንና የሚቀነሱትን ቁጥሮች እየደመርንና እየቀነስን ነው አጠቃላይ ስሌቱን የምንሠራው:: በ«ፕሮግራሚንግ» ውስጥ «ቫሪያብልስ» አሉ:: «ቫሪያብል» በኮምፒዩተር «ቋንቋ» መሠረት ለእያንዳንዱ ሐሳብ ውክልና የምትሰጥበት ሥርዓት ነው:: «ለቫሪያብሉ» ቁጥር አለ:: ለምሳሌ:- <Year> የሚል «ቫሪያብል» ቢኖርህ በዚያ ውስጥ አስፈላጊው መረጃዎች ሁሉ እንዲያዙ (Stored) ይደረጋል፤ «ዓመተ ዓለም፣ መጠነ ራብዒት፣ መደብ...» የሚባሉት ነገሮች ማለት



www.eotcmk.org

ነው:: እነዚህ «ቫሪያብሎች» ወደ «ኮድ» ይለወጣሉ:: ኮዶች ሲለወጡ ግን አብዛኛውን ጊዜ ማካፈል ላይ ቀሪው ስለሚወሰድ ቀሪው በሚያሳየው መጠን የሚጨመር፣ የሚቀነስ ነገር ይኖራል:: ያን ጊዜ ነው በመጠኑ አስቸጋሪ የሚኾነው::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *ሶፍት ዌሩን የመሥራት ሂደት ተጠናቋል ለማለት ይቻላል? ወይስ ቀሪ ተግባራት አሉ? ተጠናቆ ከኾነስ ለገበያ በሰፊው አቅርቦ ለአገልግሎት ማዋል ይቻላል?*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- እኔ ባሰብኩት መንገድ አሁን መሥራት የሚችለውን ያህል መሥራት ይቻላል:: ለአገልግሎት መዋልም ይችላል:: ይሁንና ለገበያ ሥርጭት ከመዋሉ በፊት መደረግ ያለባቸው ነገሮች አሉ:: እንዴት ነው መሠራጨት ያለበት፤ ከሚለው ጀምሮ የባለሞያዎች ተጨማሪ ግምገማዎች ያስፈልጉታል:: እኔ ይህን ያልኩት «ባሕረ ሓሳብ ቨርዥን -1» ነው:: በቨርዥን ማስተካከል ይቻላል:: «ባሕረ ሓሳብ ቨርዥን - 2» ላይ አዳዲስ ገጽታዎችና ባሕርያት /features/ ጨምሮ ዳግም ማውጣት ይቻላል::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *በሥራው ሂደት ያጋጠሙህ ጉልህ ችግሮች ምን ምን ናቸው? በተለይ ተማሪ እንደ መሆንህ መጠን...*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- ኮምፒዩተር እንደ ልብ የማግኘት፣ ዶክመንቶቹ ከfloppy በላይ ስለሚሆኑ <drive> ከሰው የመለመን ሁኔታ የመሳሰሉት ችግሮች ነበሩ:: በዲፓርትመንታችን ላብራቶሪ አለ፤ ከዚያ ኮምፒዩተር አገኛለሁ:: በተጨማሪም «ሶታ» የሚባል የዲፓርትመንት ክለብ ስላለ በዚያ አንዳንድ ነገሮችን ማግኘት ተችሏል:: ይህ ክለብ በግቢ ውስጥ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል:: በግል ኮምፒዩተር ካላቸውም ልጆች የተጠቀምኩበት ነበር::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *በዝግጅትህ የፊት ገጽ ላይ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ፎቶ ግራፍ አለ፤ ዝግጅቱን ለእርሳቸው መታሰቢያነት የሰጠኸው ነውን? ወይስ...*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- አዎ! እርሳቸው በዘመናዊው የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ብዙ ሥራ ሠርተዋል:: የዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛን ከፍተው በርካታ ሰባክያነ ወንጌልን እንዲወጡበት አድርገዋል:: ወጣቶችን ሰብስበው በማስተማር በልባቸው ላይ ፍቅረ ቤተ ክርስቲያንን በማተም አርአያነት ያለው ሥራ ሠርተዋል:: በመሆኑም ይህን ተግባራቸውን በዚህ ላይ ማስታወስ ቢቻል መልካም ነው ብዬ ነው:: ታሪካቸውንም በተወሰነ መልኩ ለማካተት ሞክሬአለሁ:: በመሆኑም የሥራው ውጤት መታሰቢያነት ለእርሳቸው ነው::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *አንዳንድ ሰዎች ይህ ዓይነቱ ዝግጅት ትውልዱ በነባሩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የአበውን ትምህርትና ፍልስፍና እንዳያጠና ያደርገዋል ይላሉ? እዚህ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- ቴክኖሎጂውን ብቻ እንከተል ከተባለ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሊያስወጣን የሚችል ነገር ይኖር ይሆናል:: ጥንቃቄ ያሻዋል:: ከቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ሥርዓት ሳይወጡ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ለመኾን የአባቶች ምዘናና አስተያየት፣ ምክርና ተግሣጽ አስፈላጊ ነው:: ይህ ከሆነ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን መገደብና በወቅቱ ማስተካከል ይቻላል:: የእኔን ሥራ በተለይ ስመለከት ደግሞ የአጽዋማትና የበዓላት መውጫና መግቢያን እንዲሁም መዋያ ቀናትን ለማግኘት በነባሩ ሥርዓተ ትምህርት የነበሩትን የስሌት ደረጃዎች ወደ «Code» የመለወጥ ሥራ ብቻ ነው የሠራሁት እንጂ አዲስ ቀመር አልፈጠርኩም:: በመሆኑም ሰው በቀላሉ እንዲያውቀው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤ በውጤቱም ሰዎችን ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በመጥራቱ ረገድ አስተዋፅዖ ይኖረዋል::

ደግሞም ሰው ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጊዜ ያጠረው መስሎ ስለሚታይ ባለው ጊዜ በሚያመቸው ሁኔታ ለመማር ያስችለዋል:: ተረጋግቶ ጊዜ ባገኘበት ሁኔታ ደግሞ በነባሩ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ሊማር ይችላል፤ ይገባዋልም:: አሁን እዚህ በግቢ ጉባኤያችን በሥርዓተ ትምህርታችን በተወሰነ መልኩ እንማራለን:: እኔ የሠራሁት «ሶፍት ዌር» ጅምር ነው:: ለወደፊቱ ሌሎች ባሕርያትና ገጽታዎች /features/ ጨምሮ በሰፊው መሥራት ይቻላል:: <u>ለምሳሌ</u>: - ሰውዬው የሚፈልገውን ዓመተ ምሕረት እያስገባ፣ እያካፈለ «interactive» በኾነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ «applications» እንዲኖሩት ማስቻልን የመሰሉ ነገሮች ማለት ነው::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *በአገራችን በአጠቃላይና በቤተ ክርስቲያናችን በተለይ ለፈጠራ ውጤቶችና ግኝቶች የባለቤትነት መብት ጥበቃ ማድረግ ላይ ግዙፍ ችግሮችና ክፍተቶች አሉ፤ ይህ ሁኔታ እንደ አንተ ዓይነት ግኝት ላላቸው ባለሞያዎች ምን ተጽዕኖ ያሳድራል ትላለህ?*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- መቼም በሰፊው ካየነው የሚሠራው ሥራ ብዙ ወጪ የወጣበትና የተለፋበት ነው:: የፈጠራ ውጤት ጥበቃ ያስፈልገዋል:: እንደ እኔ ካለው የሥራ ውጤት አኳያ ጥቅሙ መንፈሳዊ እንደ መሆኑ መጠን በሚገኘው ገቢ ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት፣ ተጨማሪ ሥራዎችንም ለመሥራት ይጠቅማል ከሚለው ማዕዘን ብቻ እንጂ ያን ያህል ተጽዕኖ ያሳድራል ብዬ አላስብም:: በርግጥ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክተው በስምዋ በሚወጡ ነገሮች ላይ ቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባታል:: የእርስዋ በኾነው ነገር የግል አስተሳሰባቸውንና ኑፋቄያቸውን አሥርገውና አስመስለው የሚያስገቡ አይጠፉምና ቁጥጥር ማድረግ ይገባታል::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *ቅድም ይህን ጅምር ሥራ ሌሎች ገጽታዎችንና ባሕርያትን /features/ እየጨመሩ በቨርዥን ማስተካከል ይቻላል ብለሃል፤ ይህንንና ተጨማሪ ሌሎች ሥራዎችን ለመሥራት ታስባለህ?*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- ለወደፊቱ በርካታ ሊሠሩ የሚችሉ ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ ወደ ኮምፒዩተር አሠራር ያልተለወጡና ሊለወጡ የሚችሉ ጽሑፎች አሉ:: በብራና የእጅ ጽሕፈት ያሉ ወደ «ድጅታል» ሊለወጡ የሚችሉ ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ብዙ ሰው ሊማርባቸው ይችላል:: የባሕረ ሓሳቡን ሶፍት ዌር የጊዜ መቁጠሪያ ካላንደር መደበኛ በኾነ መልኩ ለማዘጋጀት እንዲያስችል አድርጌ ለማውጣት ዕቅድ አለኝ::

<u>ዝግጅት ክፍል</u>:- *የማኅበራችን መሠረቶች በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት ያሉ ተማሪዎች ናቸው:: ተምረው ከሚወጡባቸው በርካታ የሞያ ዘርፎች አንጻር መፈጸም ስለሚገባቸው ነገር የምታስተላልፍላቸው መልእክት ካለህ...*

<u>ኃይለ ኢየሱስ</u>:- እንደ ክርስቲያንነታችን በተሰጠን ጊዜ የማያልፍ መልካም ሥራ እንሥራበት:: ለቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ሥራ ብሠራ ገንቢ ለውጥ አመጣለሁ ብለን እንስብ፤ በየሞያችን ልንሠራ የምንችለው በርካታ ነገር አለና:: ማኅበራችን በዚህ ረገድ የተደራጀ ድጋፍ መስጠቱን አጠናክሮ መቀጠል አለበት:: እኔ ይህን ሶፍት ዌር በምሠራበት ወቅት የመቐለ ዩኒቨርስቲ እንዳየሱስ ካምፓስ ግቢ ጉባኤ /ሰንበት ት/ቤት/ ተከታታይ ድጋፍና ማበረታቻ አድርጎልኛል:: በቅድሚያ አስልቼ ለማግኘት የቻልኩት ጾመ ነነዌን ነበር:: ታዲያ በዚያ ወቅት ሥራውን በመጀመሬ ብቻ የልደትን በዓል አስመልክቶ በዋዜማው ምሽት በተደረገው የግቢ ጉባኤው መርሐ ግብር ላይ የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቶኛል:: ሠርቼ የደረስኩበትን ነገር በየጊዜው በማሳውቅበት ወቅትም መጨመርና ማስተካከል ያለብኝን ነገር (Property) ይጠቁሙኝ ነበር:: ይኸው ማበረታቻና እገዛ ለሌሎችም ቢደረግ መልካም ነው እላለሁ::



www.eotcmk.org

# መሐላ

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

በሰዎች የሐሳብ ልውውጥ ሒደት ውስጥ አንዳንዶች የነገራቸውን እውነተኛነት ለማስረዳት ሌሎች ደግሞ እንዲሁ እንደ ልማድ ሆኖባቸው እየደጋገሙ ሲምሉ ይሰማሉ:: እነዚህም ከሁሉም በላይ ክቡርና ገናና ከሆነው ከእግዚአብሔር ስም አንሥቶ ከዚያ በመለስም የእመቤታችንን፣ የመላእክትን፣የሰማዕታትንና የሌሎችን ቅዱሳን ስም ሁሉ ማሉልኝ ሳይባሉ በነገራቸው መሐል እንደ አዝማች መሐላን ይጨምራሉ:: አንዳንድ በጣም መሐላ የለመደባቸው ደግሞ ሓሳባቸውን ከሚገልጡበት ቃልና ሐረግ ይልቅ የሚደረድሩት መሓላ ሳይበዛ አይቀርም:: ለመሆኑ እንዲምሉ የሚያስገድድና የሚጠይቅ በሌለበት ለወሬ ማድመቂያና ለነገር ማሣመሪያ ይህን ያህል መሐላ መደርደርን ምን አመጣው? የማይተማመኑ ባልንጀሮች በየወንዙ ይማማላሉ እንደሚባለው ኅሊናቸው እውነተኛ ያለመሆናቸውን እየመሰከረባቸው ይህንን ለማስተባበልና ለመቋቋም የሚያደርጉት ጥረት ይሆን?

## መሐላ ለምን አስፈለገ?

መሐላ አንድ ሰው የሚናገረውን ነገር የሚሰሙት ሰማዕያን የነገሩን ተአማኒነት የሚጠራጠሩት ሲሆን ወይም በሙሉ እምነት ለመቀበል የሚቸገሩ ሲሆን በነገሩ ዙሪያ ያላቸውን ጥርጣሬ ለመቀነስና ብሎም ለማኅመን ለአጽንዖተ ነገር የሚደረግ ነው:: የሚምለው ሰው መሐላውን የሚምለው ከእርሱ በሚበልጥ ነገር ነው:: «ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ:: ዕብ.6÷14:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት መሐላውን የሚፈጽመው ሰው ከእርሱ በላይ በሆነ÷ በሚፈራውና በሚያከብረው ስም ሲናገር የመጨረሻውንና ሊናገረው የሚገባውን ወይም የሚችለውን እውነት ይናገራልና ነው:: ከእርሱ በታች በሆነ÷ ሐሰት ብናገር ጉዳት ያደርስብኛል ወይም ያውቅብኛል በማይለው ስም ቢምል ግን መሐላው መሐላ አይሆንም፤ ለሰማዒው ማስተማመኛ ሆኖ አያገለግልም:: ስለሆነም ማንም ሰው ሲምል ከእርሱ በላይ በሆነ÷ ከማንም በላይ በሚወደውና በሚያፈቅረው እንዲሁም ሐሰትን ብናገር ያውቅብኛል ይፈርድብኛልም በሚለውና በሚፈራው ነገር ይምላል::

## መሐላ በብሉይ ኪዳን

ሰዎች እንደየእምነታቸውና ባሕላቸው በሚያምኑበት ነገር የመማል ልምድ ነበራቸው:: ጣዖት የሚያመልኩ ጣዖታውያን በአማልክቶቻቸው ይምሉ ነበር:: ለምሳሌ፡- ንግሥቲቱ ኤልዛቤል ነቢዩ ኤልያስ ነቢያተ ሐሰትንና ካህናተ ጣዖትን እንዳጠፋቸው አክአብ በነገራት ጊዜ «ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት÷ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ÷ ይህንም ይጨምሩብኝ» ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኞችን ላከች:: 1ነገ.19÷1–2:: እስራኤላውያን በግብፅ ሲኖሩ በጣዖታት ስም መማልን ያዩና ይሰሙ ነበር:: ስለሆነም እነርሱን ከአሕዛብ ለይቶ በብዙ ተኣምር ነጻ አውጥቶ ለእርሱ የተለዩ ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ በጠራቸው ጊዜ ይህ በጣዖታት ስም የመማል ልምድ እንዳይገዛቸው መሐላ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው እንዲምሉ አዘዛቸው፤ «በስሜም በሐሰት አትማሉ» በማለት ቅዱስ ስሙን እውነቱን ሲናገሩ ብቻ እንዲመሰክሩበት ተናገረ:: ዘሌ.19÷12::

በዚህ ላይ በመሐላ ሰበብ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እንዳይጠሩ ከዐሥሩ ትእዛዛት ውስጥ አንዱ በሆነው፡ -«የእግዚአብሔርን የአምላካህን ስም በከንቱ አትጥራ» በሚለው ሕግ አዘዛቸው:: የዚህንም ትእዛዝ ማለትም ስሙን በከንቱ መጥራት ለምን እንደ ሌለባቸው ከነምክንያቱ ነገራቸው፤ እንዲህ ሲል፡- «እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና» ዘጸ.20÷7:: የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት የሚሆነው በኃጢአት እየኖሩ÷ ሐሰት እየተናገሩ እንዲሁም በዘፈቀደ አለቦታውና አለጊዜው ክቡር የሆነውን ቅዱስ ስሙን በማይገባው ነገር ሁሉ መጥራት ከንቱ ጥሪ ነው:: «የአምላካችሁን ስም በከንቱ አታርክሱ» የተባለው ለእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው:: ዘሌ.19÷12::

በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሰጠው ሕግ ማለትም በእውነት ነገር የእግዚአብሔርን ስም ጠርተው እንዲምሉ እግዚአብሔር መፍቀዱ ለጊዜው ሕጉ ከሚሠራላቸው ሰዎች ደካማነት አንጻር የተደረገ ነው:: ምክንያቱም ገና ሰውና እግዚአብሔር ባልታረቀበት÷ ኃጢአትና ዲያብሎስ በሠለጠነበት÷ ምግባር ትሩፋት ቀርቶ የእግዚአብሔር ስም ራሱ ለሕዝቡ ገና እየተገለጠ በነበረበት በድንግዝግዝ ዘመን በኋላ ዘመን የሚታዘዘውን ፍጹሙን ሕግ ቢታዘዙ ኖሮ ሕጉን ከመጠበቅና እነርሱም በዚህ ከመጠቀም ይልቅ ስለሚከብዳቸው እነርሱም ሕጉን አይጠብቁትም÷ ነበር÷ ያልጠበቁት ሕግም ደግሞ ያስፈርድባቸው ነበር:: ከአሕዛብ ሕይወት እንደ ለመዱትና በዙሪያቸው ካሉትም እንደሚያዩት እውነቱን መናገራቸውን መግለጽ ሲፈልጉ በእግዚአብሔር ስም መማል ባይፈቀድላቸው ኖሮ የግድ በጣዖታት ስም ወደ መማል ይሳቡ ነበር:: ስለሆነም እግዚአብሔር ሕግ የሚሠራው ሕጉ በሚሠራለት አቅምና ችሎታ ስለሆነ በብሉይ ኪዳን ዘመን እውነት በሆነ ነገር ላይ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ መማል የተፈቀደ ነበር:: ይህም የአሕዛብ አማልክትን ስም ወደ መጥራት፣ የእነዚህን ስም ከመጥራትም እነርሱን ወደ መፍራትና ማምለክ እንዳይሄዱ ለመጠበቅ ነው::

## መሐላ በሐዲስ ኪዳን

የወንጌልን መሠረታዊ ምንነት ከጥንቱ ሕግ አንጻር በገለጠበትና «የተራራው ስብከት» ተብሎ በሚታወቀው ትምህርት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሐላን በተመለከተ እንዲህ ብሏል:: «ደግሞ ለቀደሙት: - በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ፤ እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ከቶ አትማሉ::» ማቴ.5÷33::

እንዲሁም በእግዚአብሔር አለመማል ብቻ ሳይሆን በሌላ በምንም ነገርም ቢሆን መማል እንደማይገባ ሲያስረዳ፡- «በሰማይም አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና» አለ:: ማቴ. 5÷34–35:: ይህንን የተናገረው የተናገረው አይሁድ በእነዚህ ነገሮች የመማል ልማድ ስለ ነበራቸው ነው:: ጸሐፍትንና ፈሪሳውያንን በተለይ ልማደ አይሁድን በአጠቃላይ በገሠጸበት ትምህርቱ እንዲህ በማለት እንደገሠጻቸው፡- «እናንተ ግን በቤተ መቅደስ የሚምል ምንም የለበትም ማንም በቤተ መቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል የምትሉ ዕውሮች መሪዎች ወዮላችሁ:: ማናቸው ይበልጣል? ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ መቅደስ? ደግሞም፡- ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መብዐ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ትላላችሁ...::» ማቴ.23÷16÷22::

እነዚህን ነገሮች ማለትም ሰማይን÷ምድርን÷ኢየሩሳሌምን ያከበራቸውና «በእነዚህ አትማሉ» ያለው ከራሳቸው ተፈጥሮ (ባሕርይ) ሳይሆን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ካለው ግንኙነት የተነሣ ነው:: ሰማይ «ውብና ድንቅ ስለሆነ» አላለም÷ ነገር ግን «የእግዚአብሔር ዙፋን ስለሆነ» አለ÷ ምድርንም «ጠቃሚና የሀብት ምንጭ ስለሆነ» አላለም÷ «የእግሩ መረገጫ» ስለሆነ እንጂ:: ምድራዊቷ ኢየሩሳሌምም የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም አምሳል ናትና:: በእነዚህ ነገሮች መማል ቢፈቀድ እነርሱን ማለትም ሰማይንና



www.eotcmk.org

ምድርን ወደ መፍራትና ማክበር ሊወስድ ይችል ነበር፥ ሰው የሚምለው ከእርሱ በሚበልጠው ነገር ነውና::

ከዚህም ሁሉ ጋር ሰው ከእርሱ በላይ ባሉ ነገሮች ብቻ ሳይሆን በራሱም እንዳይምል ታዟል:: «በራስህም አትማል አንዲቱን ፀጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና» ብሏል፤ ማቴ.5፥.36:: ሰው የእግዚአብሔር እንጂ የራሱ አይደለምና:: ስለሆነም የራሱ ባልሆነ ነገር ሊያዝበትና ሊምልበት አይችልም:: በአጠቃላይ ክርስቲያን በምንም ነገር ሊምል አልተፈቀደለትም:: በእግዚአብሔር፥ በቅዱሳን ስም፣ በሰማይ፥ በምድር፥ በራሱ... በምንም ነገር ሊምል አይገባውም፤ እውነቱን መናገር ብቻ ነው፥ በቃ እውነቱን እውነት፥ ሐሰቱን ሐሰት ማለት ብቻ ነው የሚገባው፤ ጌታችን:- «ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህ የወጣ ከክፉው ነው::» ብሏል:: ማቴ.5፥37::

እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንድ ዐቢይ ነገር አለ:: መሐላ ከክፉው ነበር ወይ? ከክፉው ከሆነስ እንዴት በሕግ (በብሉይ ኪዳን) ተፈቀደ? የሚለው ነው:: የተሠሩት ሕግጋት የሕጉን ተከታዮች ድካም ያገናዘቡ ስለመሆናቸው ከላይ ለማየት ተሞክሯል:: እዚህ ላይ ይህን በመጠኑ ሰፋ አድርጐ ማየት ያስፈልጋል:: ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን የተፈቀዱ በሐዲስ ኪዳን ግን የተከለከሉ እንዲያውም እንደ መሐላ ያሉት «ከክፉው ነው» እስከ መባል የደረሱ አሉና::

ለምሳሌ:- ከጋብቻ በኋላ ፍቺ ከጥንቱ በእግዚብሔር ዘንድ ያልተፈቀደ ብቻ ሳይሆን የተጠላም ነው:: ሆኖም ግን መፈታት የተከለከለ ስለሆነ ሌላ ለማግባት የፈለገው ወገን ሕይወት እስከ ማጥፋት ድረስ እየሄደ ስላስቸገረ ለዚህ ድካማቸው ሙሴ እንደ ልቡናቸው ደንዳናናት መጠን የአስተያየት ሕግ ሠራላቸው:: ይኸውም መፍታት የሚፈልግ የፍቺዋን ምክንያት ጽፎ በመስጠት እንዲፋቱ አዘዘ:: ይህ ግን ስለ እነርሱ ደካማነት የተደረገ እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ሆኖ አልነበረም:: ስለሆነም በሐዲስ ኪዳን ጌታችን ፈሪሳውያንም ወደእርሱ ቀረቡና ሊፈትኑት:- ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት:: እርሱ ግን መልስ እንዲህ አለ:: ፈጣሪ በጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለምን አዘዘ? አሉት:: እርሱም ሙሴስ ስለልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም:: እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ... ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል:: የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል» አለ:: ማቴ.5፥31–32:: በኦሪቱ ተፈቅዶ የነበረ መፋታት አሁን (በሐዲስ ኪዳን) ግን እንደ ዝሙት ተቆጠረ፥ «አመንዝራነት ነው» ተባለ:: መሐላም እንዲሁ ነው:: በኦሪት ለጊዜው ወደ ፍጹምነት ዘመን መዳረሻ እንዲሆናቸው ከአቅማቸው አንጻር ሊሸከሙት የሚችሉትን ያህል ሠራላቸው፤ ያውም ለእውነት ነገር ብቻ የእግዚአብሔርን ስም ጠርተው እንዲምሉ:: በሐዲስ ኪዳን ግን ይህ ሁሉ ተከለከለ:: ሕጉን አስቀድሞ እንዲህ ቀለል አድርጐ ባይሠራውና ከመጀመሪያው ጀምሮ ፍጹሙን ሕግ ሠርቶ ቢሆን ኖሮ በሂደት ባላደጉና ወደ ታላቅነት ባላደረሱ ነበር:: የሕግጋቱ መሠረት አስቀድሞ በሰዎቹ ዐቅም መጠን ባይደረግ ኖሮ ያን ጊዜም ሰሚና ፈጻሚ አያገኝም፥ በኋላም ሲነገር በቀላሉ ተቀባይነት አይኖረውም ነበር:: ስለዚህ በኋላ በራሱ መምህርነት ፍጹም ሆኖ ለሚሠራው ሕገ ወንጌል መንገድ ጠራጊዎች፥ አለማማጆችና አዘጋጆች ይሆኑ ዘንድ ቀለል ተደርገው ተሠሩ፥ አሁን ደግሞ በፍጹሙ ሕግ ተተኩ::

ብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን የሚያደርስ መንገድ ነበር:: አንድ ሕፃን እስኪያድግ ድረስ በሞግዚት ክብካቤ እንደሚያዘው ሁሉ የሰዎችም ሕይወት ወደ ፍጹም ሕግ እስኪደርስ ድረስ ሕግ (ኦሪት) እንደ ሞግዚት አገልግሏል:: ሐዋርያው «ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም» በማለት የገለጸው ይህንኑ ነው:: ገላ.3፥24–25:: የእናት ጡት ወተት ሕፃኑ እስኪያድግና ሌላ ምግብ መመገብ እስኪችል ድረስ ወሳኝና አስፈላጊ ነው፥ በኋላ ግን አስፈላጊነቱ ይቀራል፥ የሰውነት ሥርዓት ሂደትም ለእናት ጡት ወተት ሳይሆን ለሌላ ምግብ ዝግጁ ይሆናል:: በጊዜው ጠቃሚና ወሳኝ የነበረው የእናት ጡት ወተት ጊዜ ሲያልፍ ደግሞ በሌላ ይተካል:: የኋላው የፊቱን አያስነቅፈውም፤ የፊቱም የኋላውን እንዲሁ፥ነገር ግን ሁሉም በተገቢው ጊዜ መልካምና ተገቢ ነው:: እንደዚሁም ሁሉ በዘመነ ብሉይ የሕፃንነት ዘመን መሐላ በገደብም ቢሆን ተፈቅዶ ነበር:: በፍጹም የአእምሮ ጉልምስና በዘመነ ወንጌል ግን ምንም ዓይነት መሐላ አልተፈቀደም:: እውነቱን እውነት፥ ሐሰቱን ደግሞ ሐሰት ከማለት ውጭ መሄድ «ከክፉው» ነው ተብሎ ተነግሮአል::

## *መሐላ ለምን ተከለከለ?*

በዘመነ ኦሪት በሐሰት ለሚምሉ የቅጣት አንቀጽ ነበር:: ይህም መሐላ በሐሰት መናገርንና መመስከርን ያስቀር ዘንድ ነው:: በእምነት ላይ የተመሠረተው ዘመነ ወንጌል (ሐዲስ ኪዳን) ግን የመሐላን አስፈላጊነት አስወግዶታል:: ምክንያቱም የክርስቲያኖች ሕይወት ሁሉ በእውነት ላይ ተመሥርቶአልና ከእምነት በሚገኝ ጽድቅ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች መሐላ አያስፈልጋቸውም:: በክርስቲያኖች ዘንድ ምንጊዜም ቢሆን የሆነው ነው፥ያልሆነው ደግሞ አይደለም:: ስለሆነም ንግግራቸውና ተግባራቸው ሁሉ እውነት ነው::

አንዳንዶች ያለ መሐላ እውነትን መግለጽና ሕግን መጠበቅ ያስቸግራል ይላሉ:: ነገር ግን እንዲያውም በተቃራኒው መሐላ ካልተወገደ በሐሰት መማልንና መዋሸትን ማስወገድ ያስቸግራል:: በሐሰት የማይመሰክርና የማይዋሽ ሰው መሐላ አያስፈልገውም:: የሚምሉና የሚገዝቱ ሰዎች ብዙ ጊዜ መዋሸት የለመዱ ሰዎች ናቸው:: ስለዚህም ነው ጠቢቡ:- «ልጄ ለአፍህ መሐላን አታስተምረው፥በእርሱ ውስጥ ብዙ ክፉ ነገር አለና» ያለው:: ሲራ. 23፥9::

ብዙ መናገር የለመደበት ሰው ነገር ከማብዛት የተነሣ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችንም አብሮ የመናገር ልምዱ እንደሚጨምር ሁሉ ለእውነት ብሎ መማል የለመደ ሰውም ተገቢ ባልሆነውም ጊዜ ሁሉ መማል ይለምድበታል:: ጠቢቡ እንደሚለው:- «የማለኛ ሰው ኃጢአቱ ብዙ ነው» ሲራ. 23፥11:: ስለዚህ ሁል ጊዜም ሆነ አንዳንድ ጊዜ የሚምል ዞሮ ዞሮ ተገቢ አይደለም:: በመማል ምን ጥቅም ይገኛል? ሌላው ወገን እውነትን ብቻ እንደምትናገር የሚያውቅ ከሆነ እንድትምል አይፈልግም ነበር:: ነገር ግን ሐሰትን ልትናገር እንደምትችል የሚያውቅ ከሆነ እንድትምልለት ይፈልጋል:: ስለዚህ መሐላን የሚያመጣው በእውነት አለመጽናት ነው:: ንግግሩ ሕይወቱ ሁሉ እውነት ከሆነ የመሐላ አስፈላጊነት አይኖርም::

በምንም ሁኔታ ሐሰትን መናገር ያልተፈቀደልን እና ቃላችን ራሱ እንደ መሐላ ሆኖ እስኪታመን ድረስ እውነተኛና ተአማኒ መሆን ያለበት ሲሆን መሐላ እንዴት ያስፈልጋል?

ስለዚህም ጌታችን በሐሰት መማልን ብቻ ሳይሆን መሐላን ፈጽሞ ከለከለ:: ይህም:– በቃላችን ሁሉ እውነተኞች ልንሆን ሲገባን ስንምል ብቻ እውነቱን የምንናገር፣ በማንምልበት ጊዜ ግን መዋሸት ያን ያህል ያልተከለከለና የማይገባ እንዳልሆነ እንዳናስብ ነው:: ስለሆነም ጌታችን በመሐላችንና በማንኛውም ተራ ንግግራችን መካከል ልዩነት እንዲኖር አይፈልግም:: በመሐላ ውስጥ ኢተአማኒነት መኖር እንደሌለበት ሁሉ በሌላው ቃላችንም ሐሰት ሊኖር አይገባውም:: ስለዚህ እውነቱን የሚናገር ሰው ነገሩ ሁሉ እንደ መሐላ ነው:: እውነትን መናገር ደግሞ የሰው ሁሉ ግዴታ





www.eotcmk.org

በመሆኑ ሌላ ድጋፍና አስረጅ ለመሆን መሐላ አያስፈልግም። ነገር ግን ሐሰትን ለመናገር የደፈረና ኅሊናውን ያዋረደ ሰው ሲምልም በሐሰት የማይምልበት ምክንያት አይኖርም። ስለዚህ ዋናውና መሠረታዊው ነገር ሐሰትን ከመናገር መራቅ ነው። እንግዲህ እውነትን ብቻ የሚናገር ሰው ነገሩ ሁሉ በመሐላ ከተደገፈ ነገር ይልቅ ይበልጥ ተአማኒ ነው። እውነትንና ሐሰትን እየደባለቀ የሚናገር ግን ቢምልና ቢገዘትም ጥርጣሬን ይቀንስ እንደ ሆነ እንጂ አያጠፋም። ነቢዩ «ወሐሰት ርእሰ አመፃ–ሐሰት የዓመፃ ሁሉ ራስ ነው» ያለውን ታላቁን ኃጢአት ሐሰትን ካልተጸየፈ ያንን ሐሰት እውነት ለማስመሰል ከመማል ወደ ኋላ ይላል ብሎ ማሰብ ራስን ማታለል ነው። ነገር ግን ከመማል የሚታቀብ ከሆነ ከሐሰትና ከማይገባ ነገር ራሱን ያርቃል።

ከዘመነ ኦሪት ማለትም የጽሑፍ ሕግ በሙሴ አማካይነት ከመሰጠቱ በፊት በነበሩት አበው ዘመን መሐላ አልነበረም። በአብርሃም ዘመን ብዙ ቃል ኪዳን ተደረገ፥ መሥዋዕት ተሠዋ፤ ሆኖም ግን መሐላ መማል አልነበረም። ነገር ግን ክፋት እየበዛ፥ ነገሮች እየተደባለቁ፥አምልኮ ጣዖት እየተስፋፋ በአጠቃላይ ሰዎች ለመታመን ብቁ አልሆን እያሉ ሲመጡ ለነገራቸው አሳማኝ ዋስ ወይም ማስረጃ ይሆናቸው ዘንድ እግዚአብሔርን እንደ ምስክር መጥራት ጀመሩ። መሐላ የሚመጣው የሰዎች እውነተኛነት ሊታመን የማይችል ሲሆን ነውና። ስለሆነም በመሐላ ውስጥ የሚምለው ሰው ኢተአማኒ ነው ማለት ነው። ይኸውም እግዚአብሔርን እንደ መያዣ እስኪጠራ ድረስ ሊታመን የማይቻል ሰው ነው ማለት ነው። መሐላ የሚያስምለው ሌላው ወገንም ሰውን ወይም ሌላ ነገርን ሳይሆን እግዚአብሔርን እንደ መያዣ እንዲጠራለት መፈለጉ ተገቢ አይደለም። ዓመድና ትቢያ የሆነ ሰው እግዚአብሔርን እንደ መያዣ መጠየቅ ሌላውንም ሰው (የሚምለውን) እንዲህ እንዲያደርግ ማስገደድ እግዚአብሔርን እንደ መናቅና ማቃለል ነው። ስለዚህም እንዲምል በሚያስገድደው ሰው ላይ ፍዳውና ቅጣቱ የበለጠ ይሆናል። ማንም ሳይጠይቀው የሚምልም እንዲሁ ነው። «አንዳንድ የማይታወቁ ጉዳዮች አሉ ስለዚህ የእነዚህን እውነተኛነት ለማወቅ መሐላ ያስፈልጋል» የሚል ይኖራል። የማይታወቅ ጉዳይ ላይ ይህንኑ በሚገባ በመረዳት በጥንቃቄና በአግባቡ ማድረግ ነው፥ ነገር ግን በግዴለሽነት ካደረግኸው የሚመጣውን እንደ ቅጣት ተቀበለው፥ ትምህርትም ታገኝበታለህ። የክርስቶስን ሕግ ከማፍረስ ኪሳራ ቢያመጣም ይህንኑ መቀበል ይሻላል።

«ካልማልኩኝ በስተቀር ሰዎች አያምኑኝም» የሚሉ ሰዎች አሉ። ነገር ግን እንዲህ ሳትሆን ማለትም ለሰው ሁሉ እንደማትምል አቋምህ ግልጽና ቁርጥ ያለ ቢሆን ኖሮ ሺ ጊዜ ከሚምሉና ከሚገዘቱ ሰዎች ይልቅ ራስህን በማንቀሳቀስ ብቻ እንኳ ትታመን ነበር። ከሚምልና ከማይምል ሰው እስኪ የትኛው ተአማኒ ነው? ማንም ሰው እንድ ትምል የሚያስገድድ ቢሆን «ክርስቶስ ተናግሯል፥ስለዚህም አልምልም» ማለት ይገባል።

ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በየገቢያውና በየቦታው ሁሉ ለትንሹም ለትልቁም ነገር ስመ እግዚአብሔርን እየጠሩ ለሚምሉ ሰዎች ይህን ልማዳቸውን በተመለከተ ካስተማረው ውስጥ የሐዋርያት ሥራን በተረጐመበት ድርሰት ውስጥ የሚከተለውን ብሏል፦ «ለዐሥር ምናን ስትሉ ትምላላችሁ፥ እግዚአብሔር ዕለቱን መብረቅ ከሰማይ አውርዶ ስላላጠፋችሁ፥ ትንሽ አትክልቶችን፥ጥንድ ጫማዎችን፥ ትንሽ ገንዘብና የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን ለማግኘት ስትሉ ብቻ እግዚአብሔርን ምስክር ትጠራላችሁ። ስላልተቀጣን ያልበደልን አይምሰለን፥ ይህ የእርሱ ቸርነት እንጂ የእኛ ጽድቅ አይደለምና። መሐላው በራስህ ላይ፥ በልጅህ ላይ ቢሆን፥ «ራሴን ያጥፋኝ» ወይም «ዐይኔ ይታወር» ማለት ትደፍራለህ? እግዚአብሔር ከአንተ ዐይንና ሕይወት ያነሰ ነገር ነውን? ክርስቶስ በራሳችን እንኳ እንዳንምል ቢያዝን እኛ ግን በሆነ ባልሆነው ስሙን በመጥራት ለእርሱ ክብር አንቆረቆርም። እግዚአብሔር በምን ዓይነት አንደበት ሊጠራ እንደሚገባው የክብሩን መጠን አታውቅምን? ከስም ሁሉ በላይ የከበረውንና ቅዱስ የሆነውን ስሙን፥ አጋንንት ሰምተው የሚንቀጠቀጡለትን እኛ እንዳገኘን እንጠራዋለን። በዚህ መጥፎ ልማድ ቅዱስ ስሙ ተራ እስከ መምሰል ደርሷል። አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመስቀል እንዲምል ቢደረግ መሐላው ከባድና አስፈሪ እንደ ሆነ ያስባል። ለምን እንዲህ ሆነ? ታላቁንና ገናናውን የእግዚአብሔርን ስም እንዲሁ እንዳገኘን መጥራት ስለለመደብን ቤተ መቅደስንና መስቀልን ግን እንደዚህ ስላልተለመደ ነው። የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ ልንፈራና ልንቀጠቀጥ አይገባንምን?...Homillies of St. John Chrysostom on the Acts of the Apostles, Homily x. /ትርጉም- ከጽሑፉ አቅራቢ ገጽ 62/

## *በመሐላ ምክንያት ችግር ውስጥ የገቡ ሰዎች*

1. ሄሮድስ፦ «ከሴቶች ከተወለዱት መካከል የሚበልጠው የለም» ተብሎ የተነገረለትን መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን እስከ መግደል የደረሰው ስለ መሐላው ሲል ነው። የሄሮድያዳ ልጅ በተወለደበት ቀን ባደረገው ግብር ላይ ዘፍና ደስ ስላሰኘችው «የምትወጅውን ሁሉ ለምኚኝ፥ እሰጥሻ ለሁ የመንግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ» ብሎ ማለላት።" እርሷም ይህንን በመሐላ የተደገፈ ተስፋ ይዛ እናቷን "ምን ልለምነው?" ባለቻት ጊዜ የመ ጥምቁን የዮሐንስን ራስ እንድትለምን ነገረቻት። እርሷም እንደ ተላከች ለንጉሡ ነገረች፤ "የመጥምቁ የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ" ብላ ለመነችው። ንጉሡም በነገሩ እጅግ ቢያዝንም በመሐላ ቃል የገባውን ነገር መከልከል አልፈለገም፥ «ስለ መሐላው፥ ከእርሱም ጋር ስለ ተቀመጡት ሊነሳት አልወደደም" ይላል። ማር. 6፥26። ወዲያው ባለወግ ንጉሡ ልኮ የክርስቶስን መንገድ ጠራጊ፥ የታላቁን ነቢይና ሐዋርያ ራስ በወኅኒ አስቆረጠ። ለዚህ ዓይነት ከባድ ወንጀል የተዳረገው በመሐላ በመታሰሩ ነው። በርግጥ ይህን ዓይነት አሰቃቂ ግፍ ከመፈጸም መሐላውን ሺ ጊዜ ቢያፈርስ በተሻለው ነበር። ሆኖም ግን በግብዝነት የራሱን መሐላ ለመጠበቅና ይህን መሐላዬን ባፈርስ ከእኔ ጋር ያሉት ይታዘቡኛል በሚል ከንቱ ሃሳብ ይህንን የመሐላ በደል ፈጽሞአል። *ከጥንቱ* ራሱን በመሐላ ባያስር ኖሮ ወደዚህ ሁሉ ባልደረሰ ነበር።

2. የገባዖን ሀገር ሰዎች በተንኰል ከሩቅ ሀገር የመጡ ለማስመሰል አሮጌ ዓይበትና ያረጀና የተቀደደ የጠጅ አቁማዳ በአህዮቻቸው ላይ ጭነው፥ ያረጀና የተሰፋ ጫማ በእግራቸው አድርገው አሮጌ ልብስ ለብሰው የደረቀና የሻገተ እንጀራ ስንቅ ይዘው ኢያሱ ከሕዝበ እስራኤል ጋር ወደ ሰፈረበት ወደ ጌልጌላ ሄደው ለእርሱና ለእስራኤል ሰዎች «ከሩቅ አገር ወጥተናል አሁንም ከእኛ ጋር ኪዳን አድርጉ» አሏቸው። ይህንን ያደረጉት እስራኤላውያን በአምላካቸው በእግዚአብሔር ኃይል በኃያላን ነገሥታት ላይ ያገኙትን ድል ስለ ሰሙ እነርሱ ከዚህ ይድኑ ዘንድ ነው። ገባዖናውያን የስንቃቸውን መድረቅና መሻገት፥ የልብሳቸውን ማርጀት በማሳየት «ከሩቅ አገር የመጣን ነን» ሲሏቸው ኢያሱና እስራኤላውያን አመኗቸው። "ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ፥ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ የማኅበሩም አለቆች ማሉላቸው።» ኢያሱ.9፥15። ነገር ግን ከማሉላቸውና ቃል ኪዳን ከገቡላቸው ከሦስት ቀን በኋላ በቅርብ ቦታ የሚኖሩ ጐረቤቶቻቸው እንደ ሆኑ ሰሙ።

3. ዐሥራ አንዱ የእስራኤል ነገድ ከብንያም ነገድ ጋር ተዋግተው ከተማቸውን አጥፍተው በተመለሱ ጊዜ "ከእኛ ማንም ሰው ልጁን ለብንያም ልጆች አያጋባ" ብለው ተማምለው ነበር። ነገር ግን ከጦርነቱ የተረፉት ጥቂት የብንያም ነገድ ሰዎች ሚስቶችን ሊያገኙ ባለመቻላቸው እንደገና ራሳቸው ተመ ልሰው ተጨነቁ። "የእስራኤልም ልጆች

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



www.eotcmk.org

# የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

## • መጽሐፈ ክርስትና

*ከዚህ በፊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን የምትፈጽማቸው ምሥጢራት በየትም ቦታ አንድ ዓይነት እንዲሆኑ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት አበው መምህራን ስለ ጻፏቸው የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት ባሕርያት በመጠኑ ዳስሰናል:: ከዚያም ከእነዚሁ መጻሕፍት አንዱ የሆነውንና በ15ኛው መ/ክ/ዘ የደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ በነበሩት አባ ፊልጶስ በተባሉ አባት እንደ ተዘጋጀ የሚነገርለትን መጽሐፈ ቄደርን አስተዋውቀናል:: በዚህኛው እትም ደግሞ መጽሐፈ ክርስትና የተባለውን መጽሐፍ እናስተዋውቃለን::*

አባታችን አዳም የእግዚአብሐ ርን ትእዛዝ ስላፈረሰ በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም /በመቃብር መውረድ ላይ ወደ ገሃነም መውረድ/ ተፈረደበት:: ይህም ኩነኔ በልጆቹ ሁሉ ላይ አለፈ:: ሮሜ.5÷15-25:: ስለዚህ ሰው ሁሉ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት የማይቻል ስለሆነ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ግድ አስፈለገ:: ዮሐ.3÷5::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች በውኃና በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀን ከእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነትን እንድናገኝ ምሥጢረ ጥምቀትን ባርኮ የሰጠን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ ታምናለች፣ ታስተምራለችም:: የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ለንስሐ የሚያበቃ ጥምቀት እያጠመቀ በነበረበት ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መጥቶ በትሕትና በተጠመቀ ጊዜ አብ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ረቦ የባሕርይ አምላክነቱን መሰከረለት:: ማቴ.3÷13-17::

በዚህ ዓይነት ጌታችን ራሱ በመፈጸም አርአያ ከሆነን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ አሕዛብን ሁሉ እያስተማሩ እንዲያጠምቋቸውና የእርሱ ቤተሰቦች እንዲያደርጓቸው አዝዟል:: ማቴ.28÷19:: በጣዕመ ስብከታቸው አማካይነት በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምኖ የተጠመቀ እንደሚድን፣ አምኖ ያልተጠመቀው ደግሞ እንደ ሚፈረድበት ተናግሯል:: ማር.16÷16:: ይህን አምላካዊ ትእዛዝ የተቀበሉት ደቀ መዛሙርተ·ም በሁሉም የዓለም አቅጣጫ ተበትነው አስተምረዋል:: ሐዋ.2÷38፤ 10÷48፤ 22÷16፤ ሮሜ.6÷3፤1ቆሮ.12÷12፤ 1ጴጥ.3÷21::

ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ትእዛዝ ተቀብላ የሐዋርያትን ሥልጣን በያዙ ካህናት ልጆቿ አማካይነት ምእመናንን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቀች ሕዝበ እግዚአብሔርን ታበዛለች፣ መንግሥቱንም ታስፋፋለች:: «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው» እንዲል /ዮሐ.3÷6/ በሥርዓተ ጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ እንዲወለዱ ታደርጋለች:: ለዚህም ቀሳውስት ውኃውን በብርት አድርገው ሥርዓቱን አድርሰው ሲባርኩት ጌታችን ተሰቅሎ ሳለ አንድ ወታደር «በሕይወቱ ነውን? ወይስ ሞተ?» ብሎ ጐኑን በወጋው ጊዜ ከጐኑ የወጣውን ውኃ ይሆናል ብላ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጽኑዕ እምነት ታምናለች::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህን ረቂቅ ምሥጢር የምትፈጽምበት የጸሎትና የሥርዓት መጽሐፍ *መጽሐፈ ክርስትና* ይባላል:: ይህ የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ በ14 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግእዝ እንደ ተተረጎመ ይነገራል:: በዚህ እትም የዚህን መጽሐፍ ይዘት ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን::

*መጽሐፉ* ካህኑ ሥርዓቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ሊከተላቸው የሚገቡትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ያቀርባል:: በዚህም መሠረት ሥርዓተ ጥምቀቱን ሲጀምር ለሥርዓቱ የተመረጡትን የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችና ጸሎተ አኰቴት እየጸለየ ማጥመቂያ ቤቱን በዕጣን ካጠነ በኋላ የተጠማቂዎችን ስም ይመረምራል:: የተጠማቂውን ስመ ክርስትና ቤተ ሰቦቹ ካመጡ የእነርሱን፣ ካላመጡ ደግሞ ራሱ ይሰይማል ማለት ነው:: ለከበረች ጥምቀት ዝግጁዎች ይሆኑ ዘንድ ስለ እነርሱ ይጸልያል:: ይህንን ካለ በኋላም ዲያቆኑ በሥርዓተ ጥምቀቱ ሊሳተፉ በጥምቀት ቤቱ ለተሰበሰቡት «ጸልዩ» ይላል በዜማ:: በዚህ ጊዜ ካህኑ ስለ ሚጠመቁት ሰዎች ያቋረጠውን ጸሎት ይፈጽምና ተጠማቂዎቹ በሚቀቡት የዘይት ቅብዐት ላይ ይጸልያል:: ከዚያም የተጠማቂዎቹን ደረቶቻቸውን፣ ፊታቸውን፣ ትከሻቸውን፣ የእጆቻቸውን መሐል፣ ውጭና ውስጥ እንዲሁም ጀርባቸውን «የእግዚአብሔር ማደሪያ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ስም እቀባዋለሁ» እያለ በዘይቱ ·ይቀባቸዋል::

ከዚያ በመቀጠል ተጠማቂዎቹ «በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ለጣዖት መስገድንም ሁሉ ይክዱ ዘንድ እንለምንሃለን፤ በልባቸው ጉልበት ይሰግዱልሃል፤ እንሰግድልሃለን፣ ሰማያዊት መወለድን ሰጥተሃቸው በመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ልጆች ይሆኑ ዘንድ እንማፀንሃለን ወዘተ.» ሲል የተጠማቂዎቹን ጉልበት እያጠፈ ልዩ ልዩ ጸሎቶችን ይጸልያል:: ዲያቆኑም በመካከል እያገባ «ጸልዩ» እያለ ያውጃል:: ከዚያ በኋላ በተጠማቂዎቹ ላይ እጁን ጭኖ ተጠማቂዎቹ ከአጋንንት ከርኩሰትም ሁሉ ነጻ የወጡ ይሆኑ ዘንድ ጸሎት ካደረገ በኋላ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ መልሶ የተጠማቂዎችን ልብስ ያወልቃል:: የቀኝ እጃቸውን አንሥቶም ወደ ምዕራብ መልሶ የተጠማቂዎችን ልብስ ያወልቃል:: የቀኝ እጃቸውን አንሥቶም ወደ ምዕራብ እንዲመለከቱ ያደርግና አካለ መጠን የደረሱ ከሆኑ ራሳቸው እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በ40ና በ80 ቀናቸው የሚጠመቁ ሕፃናት ከሆኑ ደግሞ በሚዋሱአቸው /ክርስትና በሚያነሡአቸው/ አማካይነት የሚከተለውን እንዲሉ ያደርጋቸዋል::

«ሰይጣንን ክጄሃለሁ፤ የረከሰ ሥራህንም ሁሉ አጋንንትህንም ሁሉ ክፉዎችን ሠራዊትህንም ሁሉ፣ መልእክተኞችህንም ሥርዓትህንም ሁሉ፣ መንጋዎችህንም ሁሉ፣ አሸክላህንም ጸብህንም ሽንገላህንም ሁሉ ክጄሐለሁ»

ቀጥሎም ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ መልሶ እጃቸውን እንደ ቅድሙ እንዲያነሡ አድርጎ የሚከተለውን እንዲሉ ያደርጋቸዋል::

«ወልድ ዋሕድ አምላኬ ክርስቶስ በአንተ አምኛለሁ:: መድኃኒታችን የሚሆን ሕግህንም መላእክትህንም የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ ሥራህንና ሕግህንም ሁሉ





www.eotcmk.org

አምናለሁ::»

ከዚህ በኋላ ጸሎተ ሃይማኖትንና አቡነ ዘበሰማያትን ብሎ በቅደም ተከተል መዝ.50÷1-19፤ መዝ.68÷1-36፤ መዝ.113÷1-18፤ ቲቶ.3÷1-15፤ 1ኛዮሐ.5-12፤ ሐዋ.8÷26-40 ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ካነበበ በኋላ የኪዳን ጸሎት እስከ መጨረሻው ያደርሳል:: ከዚያም ዲያቆኑ መዝ.31÷1-3፤ ወይም መዝ.33÷5-7ና ወይም መዝ. 50÷13-15 ያሉትን ይሰብክና ካህኑ በዮሐ.3÷1-20 ያለውን የወንጌል ክፍል ያነባል:: ከዚህ ቀጥሎ ካህኑ «በእንተ ሰላም»ና «በእንተ ማኅበርነ» የሚባሉትን «ከዱያን እስከ ንዑሰ ክርስቲያን» ያሉ የጸሎተ ቅዳሴ ክፍሎችን ይጸልያል:: ስማቸውን ስለ ሰጡም ሰዎች እጁን ጭኖ ይጸልይላቸዋል::

ከዚህ በኋላ ያለው የጸሎት ክፍል በውኃው ላይ የሚፈጸመው ነው:: ካህኑ የተቀደሰውን ዘይት አንሥቶ ሦስት ጊዜ በመስቀል አምሳል እያደረገ «ቡሩክ እግዚአብሐር አብ አሜን:: ቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አሜን:: ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ አሜን» እያለ ውኃውን ይባርካል:: ከዚያም «ሰማይን የፈጠርህ ሁሉንም ያደረግህ ቅዱስ ወደሚሆን ኃይልህ እንጮኻለን...» ብሎ ከጸለየ በኋላ በውኃው ሦስት ጊዜ እፍ ይልበታል::

ካህኑ ውኃውና ዘይቱ ለአዲስ መወለድና ለዘላለም ሕይወት ይሆኑ ዘንድ ጸልዮ ሲጨርስ ዲያቆኑ በዜማ «ሰዎች ሆይ ቁሙ፤ ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ ፥ አድምጡም» ብሎ ያውጃል:: ምእመናኑም ተነሥተው «ምሕረት ወሰላም ወጥምቀት ቅድስት÷ ምሕረትና ሰላም ቅድስት ጥምቀትም ናት» ይላሉ:: ከዚያም ካህኑ ይጸልያል:: ሕዝቡም «ቅዱስ÷ ቅዱስ ÷ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጹም አሸናፊ የምስጋናህ ቅድስና በሰማይ በምድር የመላ ነው» እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ:: በዚህ ዓይነት ሁሉም የሚገባቸውን ጸሎት ካደረሱ በኋላ ካህኑ ከሜሮኑ በውኃው ላይ ሦስት ጊዜ ይጨምርና በመስቀል አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ይባርከዋል:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሥርዓቱ ይፈጸም ዘንድ ስለ ፈቀደ ካህኑ መዝ.150÷1-6 ባለው የነቢዩ ዳዊት የምስጋና መዝሙር ያመሰግነዋል::

የምስጋና መዝሙሩ እንደ ተጠናቀቀ በመስቀሉ የመጠመቂያውን ውኃ ያማስለዋል:: ቀጥሎም ተጠማቂው ሕፃን ከሆነ ዲያቆኑ፤ ዐዋቂ ከሆነ ግን ራሱ በአራቱ ማዕዘን ወደ ውኃው ይሰግዳል:: ከዚያ ቄሱ ተቀብሎ ስመ ጥምቀቱን እየጠራ ሦስት ጊዜ «እገሌ በአብ ስም÷ በወልድ ስም÷ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ» እያለ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ያጠምቀዋል:: ተጠማቂውም /ሕፃን ከሆነ በአንሺው አማካይነት/ «አሜን» ይላል:: ከዚህም በኋላ ካህኑ በተጠማቂው መንፈስ ቅዱስን ተቀበል ብሎ እፍ ይልበታል:: ከዚያም ካህኑ መስቀሉን ከውኃው አንሥቶ ያጥበዋል:: እጁንም ይታጠባል::

ተጠማቂዎቹ ከተጠመቁ በኋላ ካህኑ ሜሮን ከመቀባቱ ማሕተም ከማተሙ በፊት በተጠመቁት ላይ እጁን ጭኖ በመጸለይ እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: ከዚያም ካህኑ የተጠማቂዎቹን ፊት፣ ዐይኖች፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ ጆሮ፣ የእጆች ውስጥና ውጭ፣ ደረት፣ ልብ፣ ጉልበት፣ ጭን፣ እግሮች፣ ብልቶች፣ የትከሻ መካከልና ፊት በመስቀል ምልክት እያደረገ ለየሰውነት ክፍሉ የሚገባውን ዐዋጅ እየነገረ በሜሮን ይቀባዋል:: ተጠማቂውም በየዐዋጁ «አሜን» ይላል:: ከዚያም ካህኑ በተጠማቂው ላይ እጁን ጭኖ ይጸልያል:: በመጨረሻም «ለእሊህ ለባሮችህ ቅዱስ ሥጋህንና ክቡር ደምህን ይቀበሉ ዘንድ ስጣቸው» ብሎ ትእዛዙን ነግሯቸውና ባርኳቸው «በሰላም ሂዱ» ብሎ ያሰናብታቸዋል:: ተጠማቂዎችም ከጥምቀት ቤቱ ወጥተው ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ይቀበላሉ:: ይህ በአንድ ቀን ተጠምቆ ወዲያው መቁረብ ዛሬ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በስፋት ሲፈጸም የሚታይ ነው:: ወደ ፊት እትም ደግሞ በሌላ የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ እንገናኛለን:: ቸር ይግጠመን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


**አቡነ ጎርጎርዮስ አጸደ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከነርሰሪ እስከ ሦስተኛ ክፍል ምዝገባ ጀመረ !!**

*ባሉን ጥቂት ቦታዎች ቀድመው ይመዝገቡ*

*ስልክ 51-37-42/51-06-59*


# *መሐላ*

*ከገጽ ፴፪ የዞረ*

ስለ ወን ድሞቻቸው ስለ ብንያም ልጆች ተጸጽተው ዛሬ ከእስራኤል አንዱ ነገድ ጠፍቶአል:: እኛ ልጆቻችንን እንዳን ድርላቸው በእግዚአብሔር ምለናልና የተረፉት ሚስቶች እንዲያገኙ ምን እናድርግ? አሉ::" መሳ. 21፥6-7:: ከዚያም ይህን ሁኔታ ለመፍታት ሌሎች በኢያቢስ ዘገለዓድ ያሉ ሰዎችን በሰይፍ ወደ መግደልና ወደ ሌሎች አስቸጋሪ ነገሮች ውስጥ እስከ ለመግባት ደርሰዋል::

4. በሳዖል መሪነት እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ ሳለ ሳዖል "ጠላቶቼን እስክበቀል እስከ ማታ ድረስ መብል የሚበላ ሰው ርጉም ይሁን::" ብሎ ሕዝቡን አማላቸው:: ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ መብል አልቀመሱም ነበር:: ሕዝቡ ወደ ዱር በገባ ጊዜ የሚፈስስ ማር ነበር፥ ሆኖም ግን መሐላውን ስለ ፈሩ ማንም ከዚያ ማር አል ቀመሱም:: ዮናታን ግን አባቱ /ሳዖል/ ሕዝቡን ባማለ ጊዜ አልሰማም ነበርና ከዚያ ማር ወለላ በላ፥ ዐይኑም በራ:: ከሕዝቡም አንዱ አባትህ ዛሬ መብል የሚበላ ሰው ርጉም የሁን ብሎ ሕዝቡን መሐላ አምሎአቸዋል" አለው:: ሕዝቡ ግን ደከሙ:: ዮናታንም "አባቴ ምድ ሪቱን አስቸረ፤ ከዚህ ማር ጥቂት ብቀምስ ዓይኔ እንደ በራ እዩ:: ይልቅስ ሕዝቡ ካገኙት ከጠላቶቻቸው ምርኮ በልተው ቢሆኑ የፍልስጥኤማውያን መመታት ይበልጥ አልነበረምን? አለ::» 1ሳሙ. 14፥24-30:: በዚህ መሐላ መፍረስ ምክንያት ሳዖል «ፍልስ ጥኤማውያንን ልከተልን? በእስራኤልስ እጅ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለ ህን?" ብሎ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ በዚያን ቀን አልመለሰለትም:: የዚህንም ምክንያት ማለትም በማን ኃጢአት እንዳልመ ለሰለት ለማወቅ ሕዝቡን ሰብስቦ ሲያጣራ በመጨረሻ ጥፋቱ የልጁም የዮናታን መሆኑ ታወቀ:: ዮናታንም ያደረገውን ተናገረ፥ ሳዖልም:

- እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብኝ እንዲህም ይጨምርብኝ፤ ዮናታን ሆይ÷ ፈጽመህ ትሞታለህ" አለ:: ነገር ግን ሕዝቡ ሳዖልን:

- "በውኑ በእስራኤል ዘንድ ታላቅ መድኃኒት ያደረገ ዮናታን ይሞታልን? ይህ አይሁን፤ ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎአልና ሕያው ከእግዚአብሔርን ከራሱ ጠጉር አንዲት በምድር ላይ አትወድቅም አሉት:: ሕዝ ቡም እንዳ ይሞት ዮናታንን አዳነው::» 1ሳሙ. 14፥43-45:: ይህ ሁሉ በሳዖል ላይ የደረሰበት ስለ መሐላው ነው::

እነዚህ ሁሉ ከላይ የተገለጹት ራሳቸውን ለፈተናና ለችግር ያጋለጡት በመሐላ የተነሣ ነው:: በአጠቃላይ መሐላ የሰ ይጣን ወጥመድ ነው:: ስለሆነም ራሳችንን ከዚህ የሰይጣን ወጥመድ እናርቅ፤ «በምንም ፈጽሞ አትማሉ» ያለውን የጌታችንን ትእዛዝ እንፍራ÷ እናክብር:: ሕይወታችንና ንግግራችን ሁሉ እውነት ይሁን:: ከእውነ ተኛነታችን የተነሣ ነገራችን ሁሉ የማይጠረጠርና ተአማኒ ይሁን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አንጥራ:: በምንም ሁኔታ ቢሆን በስሙ አንማል:: በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱሳን በመላእክት፥በሰማዕታትና በጻድቃን ስም በማንም ቢሆን አንማል:: ራሳችንን ከመሐላ ልማድ ነጻ እና ውጣ:: ይህንን ለማድረግ እንድንችል የእግዚአብሔር ቸርነት÷የእመቤታችን አማላጅነት÷የቅዱሳን በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::




www.eotcmk.org

# «ናሁ አነ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኀልቀተ ዓለም»

እነሆ፡- «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። ይላል የእግዚአብሔር ቃል፤ /ማቴ.28÷20/።

ይኸውና ከሚያዝያ 23 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ታላቁን የክርስትና በዐላችንን በዐለ ትንሣኤውን፣ በዐለ ፋሲካውን በማክበር ላይ እንገኛለን፤

በሃይማኖት ትምህርታችን ተስፋ አድርገን የምንኖረው ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ነው፤ «ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን፣ ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም፤ የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ» ይላል የሃይማኖት ምስክርነት መጽሐፋችን።

ሰው ሁሉ ከመንፈሳዊ ሕይወቱ አንጻር፣ የእርሱንም ሆነ፤ የዚህን ዓለም ከንቱነት ሊገነዘብ የሚችለው፣ ራሱን ክዶ መስቀለ ክርስቶስን ተሸክሞ የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ትምህርተ ሃይማኖት የማወቁ ብቃትና ችሎታ ሲኖረው ብቻ ነው።

በዐለ ስቅለቱ፤ በዐለ ትንሣኤውን በማስከተሉ የድል፣ የምሥራች፣ የድኅነት በዐል መሆኑ ተረጋገጠ፤ ከሞት በኋላ ትንሣኤ ያለ፣ የሚኖር መሆኑንም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ያስተምረናል።

ከዚህም የተነሣ «ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ፤ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ፤ አቤቱ ÷ ሞትህንና ትንሣኤህን እናምናለን፤ ወደ ሰማይ ማረግህንና ይህንም ዓለም ለማሳለፍ እንደገና መምጣትህን እናምናለን» በማለት በጸሎተ ቅዳሴያችን እግዚአብሔር አምላካችንን እናመሰግነዋለን።

ስለ ፋሲካ በዐል አከባበር በምናስብበት ጊዜ፣ እስራኤላውያን ከ430 ዘመናት ከግብፃውያን የባርነት ኑሮ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በመልአኩ ተራዳኢነት፣ በታላቁ ሙሴ መሪነት ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ተከታታይ ጠላቶቻቸው ፈርዖናውያን ሰጥመው በማየታቸውና ነጻ በመውጣቸው፡-

«ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ፤ ፈረሰ ወመስተዕዕነ ወረወ ውስተ ባሕር»

«ፈረሱንና ፈረሰኛውን ወደ ባሕር ያሰጠመ፣ አሸቀንጥሮ የጣለ፤ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን» በማለት በነጻነት አደባባይ በኤርትራ ባሕር ዳርቻ ወንዱም ሴቱም ሕፃናቱም ሳይቀሩ እስራኤላውያን በአንድነት ሁነው በእኅተ ሙሴ ማርያም ከበሮ ያኸነት እግዚአብሔር አምላካቸውን አመ ስግነዋል። /ዘጸ.15÷1-2/።

ከዚህ የምስጋና ነጻነት ክብረ በዐል በፊት፣ እግዚአብሔር ውኃውን ወደ ደምነት መለወጡ አንድ ተብሎ ተቈጥሮ፣ እስከ ዐሥረኛው እስከ ሞተ በኵር ድረስ የግብፃውያን የሰውና የእንስሳ ዝርያ የሆነውን በኵር ሁሉ በገደለ ጊዜ፡- «እኔ እግዚአብሔር ያደረግሁላችሁን ሁሉ በማስታወስ ይህ ቀን የሃይማኖት ክብረ በዐል ይሁንላችሁ፣ ይህን የፋሲካ በዐል በሚመጡት ዘመናት ሁሉ ታከብሩታላችሁ» በማለት እግዚአብሔር አምላክ ለእስራኤላውያን የነገራቸው የፋሲካ በዐል አከባበር መነሻው በእስራኤላውያን መኖሪያ ቤት ደጃፍ መቃኖች ላይ የተቀባ የጠቦት በግ ደም ሁኖ እስከ ዛሬ፣ ከዚያም እስከ ዓለም ፍጻሜ በከፍተኛ ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት ይከበራል ማለት ነው። /ዘጸ.12÷14/።

በብሉይ ኪዳን የሆነውን ወይም የነበረውን የቤተ እሥራኤልን ታሪክ አስቀድሞ መናገሩ ብሉይ ኪዳኑ መነሻ፣ ሐዲስ ኪዳኑ መዳረሻ በመሆኑ ለትምህርተ ወንጌሉ አሰጣጥ አመች ነው። ስለዚህም መቅድመ ትምህርቱን ብሉይ ኪዳን ማድረጉ ተገቢ ይሆናል በማለት ከላይ የተነገረውን እንደ መግቢያ ተጠቅመንበታል።

«አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኅልቀተ ዓለም፤ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መነሻ ርእስ አድርገናል።

ይህ ዘይቤ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል ነው።

ሕግ የተሰጣቸው እነርሱ፣ ሕግን መፈጸም ስለ ተሳናቸው፤ ሕጉም እነርሱን ማዳን ስለ ተሳነው፣ እግዚአብሔር አምላክ ሁለቱንም ወገኖች ለማዳን ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ልጁን ወደ ዓለም ላከ፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሁኖ በዳዊት ከተማ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ ተወለደ፣ አደገ፣ በሠላሳ ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ፤ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገባ፤ አርባ መዓልት፣ አርባ ሌሊት ጾመ፣ ተራበ፣ ተፈተነ፤ ፈተናውን ድል አድርጎ ጾሙን፣ ሱባኤውን ፈጽሞ በወጣ በሦስተኛው ቀን በገሊላ አውራጃ በቃና መንደር ከእናቱ ከቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፣ ከሐዋርያቱ ጋር በሰርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን በመለወጥ የመጀመሪያውን ተኣምር በማድረግ የትምህርቱን የተኣምራቱን ሥራ እያከናወነ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ማዕከለ ምድር ቀራንዮ ተጓዘ፤ ሥግው ቃል በማዕከለ ምድር ቀራንዮ በሥጋ ተሰቅሎ በሥጋ ሞቶ ሰው የሆነበትን የማዳን ሥራ ፈጽሞ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎና አድሮ እንደ ተነሣ ለመጀመሪያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን የተገናኛቸው «ሰላም ለኵልክሙ፤ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» በማለት ነበር።

ሃይማኖት ያለው ሕዝብ ሁሉ ሰላም ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ያውቃል፤ ሰላም ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ጸጋ መሆኑንም ይገነዘባል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሞቶ ተነሥቶ ለአርባ ቀናት ሐዋርያቱን ያስተምራቸው፣ መመሪያን ይሰጣቸው በነበረ ጊዜ፡- «ሒዱና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ አስተምሩ፤ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» /ማቴ.28÷19-20/ በማለት የሹመታቸው መታወቂያ፤ አካል ጉዳተኛውን የሚፈውሱበትን፣ ጋኔን የሚያወጡበትን፤ የተለያዩ ተኣምራትን የሚያደርጉበትን፣ ኃጢአትን የሚያስተሰርዩበትን፣ ማሰር፣

መፍታት የሚችሉበትን፣ ምድራውያን አማልክት ሁነው ሰማያዊ ጸጋን የሚያድሉበትን ሥልጣን ሰጥቶ ከማዕከለ ምድር ኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ የክፍላተ ዓለም ሔደው እንዲያስተምሩ ሐዋርያቱን ላካቸው።

በዚሁ መነሻነት ሐዋርያት ወደየአህጉረ ስብከታቸው ተጉዘው እነርሱ እንደ ተማሩ አስተማሩ፤ እነርሱ እንደ አመኑ ኾነው አሳመኑ፤ ያዩትን፣ የሰሙትን ሁሉ በመጽሐፍ ጽፈው ለቤተ ክርስቲያን ልጆች አስተላለፉ፤ ስለዚህ፣ ሃይማኖት በነቢያት፣ በሐዋርያት ብቻ ተወስኖ ሳይቀር በመምህራን፣ በሊቃውንት እየተላለፈ እስከ እኛ ደርሷል፤ የሚቀጥለውም ትውልድ ከእኛ ይረከባል ማለት ነው፤ ወደፊትም በዚሁ ዓይነት እስከ ዓለም ፍጻሜ እንደሚደርስ የታመነ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኀልቀተ ዓለም...፤ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ» በማለት የተናገረው፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን እንደ ሾመ ሁሉ በየጊዜው መምህራንን፣ ሊቃውንትን እየሾመ ሲሠራ፣ ሲያሠራ ይኖራል ማለት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን፣ አንዳንዶቹን፣ አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛም ነቢያትን፣ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፣ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፣ በይቀጥላልም የመፈወስን ስጦታ፣ ርዳታንም፣ አገዛዝንም፣ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳናትንም አድርጓል፤ ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳናት ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ፣ ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድን አሳያችኋለሁ።» ይላል። 1ቆሮ.12÷28-31።

በሌላውም ክፍል «እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ማቴ.28÷20፤ የሐዋ.1÷8። ይላል። በሁለቱም የተነገረው ሁለቱም አባባል ተወራራሽነት ያለው መሆኑ ግልጽ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ድረስ በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት ትመራ እንደ ነበርና ከዚያም የመጀመሪያው መቶ ዓመት በሐዋርያት ዘመን የክርስትናውን ታሪክ መቀበሏን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። /የሐ.8÷26-40/።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአምስቱ ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በትምህርተ ሃይማኖት አንድ የሆነች፤ የኢትዮጵያውያንን ህልውና በሃይማኖት፣ በነጻነት፣ በታሪክ፣ በተቀደሰ ባሕል፣ በትምህርትና በሥነ ጥበብ አንድ አድርጋ ጠብቃ የነበረች፤ ያለችና የምትኖር ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት፣ ታሪካዊት፣ ብሔራዊት እናት ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የምትመራውም ቅዱሳን አበው ሐዋርያትና ቅዱሳን አበው ተከታዮቻቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በወሰኑት ፍትሐ መንፈሳዊና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው። በዚሁ መሠረት በፓትርያርኩ ሰብሳቢነት ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጳሳት በተወሰነ ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ በማድረግ የአበው ሐዋርያትና የአበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ፤ ምእመናን በምግባር፣ በሃይማኖት እንዲጸኑ፣ እግዚአብሔር የሚመሰገንበትን፣ ምእመናን የሚገለገሉበትን ሥርዓት ይወስናሉ።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በዓመት ለሁለት ጊዜያት እንዲሆን በፍትሐ መንፈሳዊ ተደንግጓል። ከዚያ ተያይዞ በመጣው ትውፊት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በየዓመቱ፣ በዓመቱ መጀመሪያ ጥቅምት 12 ቀንና ትንሣኤ በዋለ በኻያ አምስተኛው ቀን በርክበ ካህናት ከሚያደርጋቸው መደበኛ ስብሰባዎች ሌላ በቤተ ክርስቲያናችን አሠራር ጊዜ የማይሰጥ ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥምም ቅዱስ ሲኖዶስ አስቸኳይ ስብሰባ በማድረግ ስለ ሀገራችንና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ደኅንነት፣ ስለ ሕዝበ ክርስቲያኑ አንድነት እየመከረ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በማስተላለፍ ሲሠራ ቆይቷል፤ አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛል።

በዚሁ መሠረት የ1997 ዓ.ም የርክበ ካህናት ጉባኤ፤ ግንቦት 17 ቀን 1997 ዓ.ም በነገው ዕለት የሚጀመር በመሆኑ፣ ይኸው በመንፈስ ቅዱስ የሚመራውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉባኤ ለማካሔድ ከመላ አህጉረ ኢትዮጵያና በውጭ ካሉትም አህጉረ ስብከት ተሰብስበን ሥርዓተ ዋዜማውን በመፈጸም ላይ እንገኛለን።

ከላይ እንደ ገለጽነው፣ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የማስተማር ሥራቸውን የጀመሩት በይሁዳ ምትክ ማትያስን በቅዱስ ሲኖዶስ ከሾሙ በኋላ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። /የሐዋ.1÷26/።

በሌላም በኩል ደቀ መዛሙርት እየበዙ ስለ ሔዱ ከግሪክ አገር በመጡትና በይሁዳ በነበሩት አይሁድ መካከል በአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ተፈጠረ። ስለዚህም ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሁሉንም ጠርተው ለአገልግሎት የሚበቁትን ሰባት ሰዎችን በመምረጥ ሠይመው አገልግሎቱ በሥነ ሥርዓት እንዲመራ አድርገዋል። /የሐዋ.6÷1-15/።

ከዚህም በኋላ በአሕዛብ ምክንያት በሐዋርያትና ከቤተ አይሁድ በተመለሱት ክርስቲያኖች መካከል ልዩነት እንዳይፈጠር በማለት ሐዋርያትና ሌሎችም አርድእት የአይሁድን ሕግና ሥርዓት አልፎ አልፎ ሲሠሩበት ይታዩ ነበር።

የኦሪት ሕግ ለድኅነት ብቁ አለመሆኑን እየደጋገመ በድፍረት ይሰብክ፣ ያስተምር የነበረው መምህረ አሕዛብ ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ፣ አይሁድን ላለማስደንበር ሥርዓተ ኦሪትን ሲፈጽም ይታይ ነበር። /ሮሜ.11÷13/።

ለምሳሌ፡- በታናሽ እስያ በደርቤን ቅዱስ ጳውሎስ ያስተምር በነበረበት ጊዜ ጢሞቴዎስ የተባለውን ወጣት ለማስከተል ሲጠራው በዙሪያው ብዙ አይሁድ ስለነበሩ እነርሱን ለማስደሰት ገዝሮ ማስከተሉን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። /የሐዋ.16÷3/።

ይሁን እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መገዘርም ሆነ አለመገዘር ሁለቱም አንድ መሆናቸውን ይናገራል።

ይሁንና ክርስትናን የተቀበሉት አይሁድ የክርስትና ዓላማ ምሥጢሩ ስላልገባቸው በአረማውያን ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መውረድ ድንጋጤን አሳደረባቸው። /የሐዋ.10÷45/።

ዳሩ ግን በጊዜው፡- «መዳን የሚችሉት የሙሴን ሕግና ሥርዓት የፈጸሙ እንጂ ያለዚያ ግን መዳን አይቻልም» በማለት ሲከራከሩ የነበሩት፤ ሐሳባቸውን በሶርያና በኪልቅያ ለሚኖሩ ለአሕዛብ ወገን ለነበሩት ክርስቲያኖች ማስተማር ጀመሩ።

ይህ ነገር እየተስፋፋ በመሔዱ በአሕዛብ አህጉር የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ሁከት ስለ ደረሰባት መሠረቷ ተናጋ፤ በዚህም ጊዜ ጉዳዩ እየከረረ ሔደ፤ የቤተ ክርስቲያንም መሠረታዊ ዓላማ እንዳይናጋ በኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ በያዕቆብ ሊቀ



www.eotcmk.org

መንበርነት ሐዋርያት የትምህርተ ሃይማኖት ሲኖዶስ አደረጉ:: /የሐዋ.15/::

ሐዋርያት በሚያስተምሩበት ጊዜ ሁሉ በወቅቱ በነበሩት ክርስቲያኖች አለመግባባት የተነሣ የገጠማቸውን ችግር በማስረዳት ሲኖዶሱ ጥናቱን ከአጠናቀቀ በኋላ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊፈጽሙት ከማይገባቸው እንዲጠበቁ መምከርና ማስተማር እንጂ «የሙሴን ሕግና ሥርዓት ጠብቁ» ብሎ ማወክና ተስፋ ማስቆረጥ እንደማይገባ ውሳኔ አሳለፈ::

ይህ ውሳኔ ለአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ ተልኮ ከዚህ በኋላ ወንጌልን ለማስተማር የሚወጡ ሁሉ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና የመዳን ምልክት ከምኩራብ ሕግና ሥርዓት የተለየ መሆኑን በይፋ ማስተማር ጀመሩ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሑሩ ወመሐሩ ኰሎ አሕዛበ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ሒዱና እስከ ዓለም ዳርቻ አስተምሩ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፤ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሩአቸው» ብሎ ሹሞ የሥልጣናቸው መታወቂያ የሚሆን አካል ጉዳተኛ የሚፈውሱበትን፣ ሙት የሚያስነሡበትን፣ ጋኔን የሚያወጡበትን፣ ልዩ ልዩ ተአምራት የሚፈጽሙበትን፣ ኃጢአት የሚያስተሰርዩበትን፣ ማሰር መፍታትሚችሉበትን ምድራውያን ሆነው ሰማያዊ ጸጋ የሚያድሉበትን ሥልጣን ሰጥቶ በመምህርነት፤ በሐዋርያነት ወደ ዓለም አሠማራቸው::

በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል እንደ ተናገርነው እነርሱ እንደ ተማሩ፣ አስተማሩ፤ እንዳመኑ አሳመኑ፤ ያዩትን የሰሙትን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ልጆች በመጽሐፍ ጽፈው አስተላለፉ::

ስለዚህ ሃይማኖት በነቢያትና በሐዋርያት ብቻ ተወስኖ ሳይቀር በሊቃውንት፣ በመምህራን እየተላለፈ እስከ ዛሬ ተጠብቆ ቆይቷል:: ወደ ፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ተጠብቆ ይኖራል::

ከላይ እንደ ተገለጸው «አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኅልቀተ ዓለም፤ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከናንተ ጋራ ነኝ» /ማቴ.28÷20/ በማለት ቀደም ሲል በተናገረው መሠረት:-

ሀ/ ጌታ የተናገረው

ለ/ ሐዋርያት ያስተማሩት

ሐ/ በሦስቱ ጉባኤያት ማለት በኒቅያ፣ በቁስጥንጥንያ፣ በኤፌሶን የተሰጠው ውሳኔ፤

መ/ ከኬልቄዶን ጉባኤ በፊት ቅዱሳን አበው የተናገሩት፣ ያስተማሩት፤

ሠ/ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ከእስክንድርያ መንበር ወራሾች ከማርቆስ ወንጌላዊና ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር የሚተባበሩ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ያስተማሩት ትምህርት፣ ያመኑት እምነት ይገኝበታል::

ከሐዋርያትም በኋላ የተነሡ ቅዱሳን አበው ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በየሀገሩ፣ በየቦታው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲኖዶስ በማድረግ ለማስተማር፣ ሕግን ለመደንገግ፣ ቀኖናን ለማውጣት፣ ቤተ ክርስቲያንን ለመመገብ እየተሰበሰቡ ውሳኔን አሳልፈዋል::

ይኸውም:-

1ኛ. በ325 ዓ.ም ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ቅዱሳን አበው በኒቅያ፤

2ኛ. በ381 ዓ.ም አንድ መቶ ኀምሳ ቅዱሳን አበው በቍስጥንጥንያ፤

3ኛ. በ431 ዓ.ም ሁለት መቶ ቅዱሳን አበው በኤፌሶን፤

ከዚህ በላይ በሦስቱ ጉባኤያት ቁጥራቸው የተጠቀሰው ቅዱሳን አበው በየጊዜያቸው የተነሡ መናፍቃንን ተከራክረው ረትተው፣ ሃይማኖትን አቅንተው፣ ትምህርታቸውንና እምነታቸውን አጽንተው አስተላልፈውልናል::

ከዚህም ጋር በሎካል ደረጃ በየቦታው ማለት በሰሜን አፍሪካና በሌሎችም ቦታዎች የተደረጉ ንዑሳን ጉባኤዎች የነበሩ መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል::

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ምንረዳው ከአራተኛው መቶ ዓመት መነሻ አካባቢ አንሥቶ በሲኖዶስ አሠራር የተጠናከሩ በቢዛንታይን ወይም በሮማውያን ግዛት ማለት በዚያን ጊዜ የሠለጠነው ዓለም እየተባለ ይጠራ በነበረው አምስት መናብርተ ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳት ተመሥርተው ነበር:: በአጀማመሩም ወቅት የቅደም ተከተል ቀኖናውን ጠብቀው የተቀመጡት:-

1ኛ. ሮሜ

2ኛ. እስክንድርያ

3ኛ. አንጾኪያ

4ኛ. ኤፌሶን

5ኛ. ኢየሩሳሌም ነበሩ::

ከጊዜ በኋላም ቁስጥንጥንያ የቢዛንታይን ወይም በምሥራቅ የሮሜ መንግሥት ዋና ከተማ ስትሆን የላይኛው የቅደም ተከተል አቀማመጥ ተፋልሶ አጋጥሞት እንደሚከተለው ሆነ::

1ኛ. አሁንም ሮሜ

2ኛ. የኤፌሶን መንበር ወደ ቁስጥንጥንያ ፍልሰት አጋጥሞት የእስክንድርያን ሁለተኛነት ወስዶ ቁስጥንጥንያ ሁለተኛ፣

3ኛ. እስክንድርያ

4ኛ. አንጾኪያ

5ኛ. ኢየሩሳሌም ሁነው እንዲሠሩ በቅዱስ ሲኖዶስ ቀኖና ተሠርቶላቸው እስከ 451 ዓ.ም ማለት እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ የእግዚአብሔር መንግሥት የሆነችው አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በፖለቲከኞች አሠራር ሁለት እስከ ሆነችበት ጊዜ ድረስ ከላይ የተጠቀሱት መናብርት ተጠናክረው ሰፍተውና ጎልተው ይታዩ ነበር::

በዚያም አሠራራቸው ሮምና ቁስጥንጥንያ በአንድ ወገን ሲሠለፉ፤ እስክንድርያና አንጾኪያም አንድ ግንባር ፈጥረው ይታዩ ነበር::

የኢየሩሳሌሙ አምስተኛው መንበረ ሊቀ ጵጵስና ግን ሚዛኑ ወደ አየለበት ጥገኛ በመሆን ጊዜውን አሳልፏል::

በመሠረቱ የመዋቅሩ ቀኖናዊ አሠራር በፖለቲከኞች ሳይሆን የመንፈሳዊነቷ ታሪክ ታውቆና ዋጋ አግኝቶ በመንፈሳውያን ቅዱሳን አበው ቢቀየስ ኑሮ የአንደኛነቱን የታሪክ መንበር መያዝ የነበረባት ኢየሩሳሌም ነበረች::

ከአምስተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የአብያተ ክርስቲያናት መለያየት እየሰፋ መሔዱን ቀጠለ::

የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ራሱን «ዓለም አቀፍ ፓትርያርክ» ማለቱን ሲቀጥል የሮሜው ፓፓም እያንገራገረ እስከ 1054 ዓ.ም ማለት እስከ 11ኛው መቶ ዓመት ድረስ አንድ ግንባር ፈጥረው ቆዩ:: በኋላ ግን በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርተ ሃይማኖት ምክንያት በ1054 ዓ.ም እርስ በርሳቸው ተወጋግዘው ተለያዩ::



www.eotcmk.org

ከአምስተኛው መቶ ዓመት እስከ 11ኛው መቶ ዓመት ድረስ የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል በሁለት ቡድኖች ብቻ ይታይ የነበረው፤ ከ11ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ግን የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል በሦስተኛ ክፍል ተጠናክሮ ይታይ ነበር። ከጊዜ በኋላም በ16ኛው መቶ ዓ.ም ሉተር፣ ካልቢንና ዝዊንግል ተነሥተው በሦስት ደረጃዎች የነበሩበትን የቤተ ክርስቲያን ክፍፍሎች ወደ ዐራተኛ ተራ ቁጥር ከፍ አደረጉት። ከ16ኛው መቶ ዓመት ወዲህ የተለያየ ስያሜና የጎላ የትምህርተ ሃይማኖት ልዩነት ያላቸው በሺ የሚቈጠሩ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች ይገኛሉ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት፤ በመስቀሉ ያጠራት የአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ብቻ ናቸው። ከኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተገንጥለው ወይም ተለይተው የሔዱት ሰባት ጉባኤያት ያሏቸው መሆኑ በዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፤ ኬልቄዶንያኑ ከኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ተለይተው ከሔዱ በኋላ አራት ተጨማሪ ጉባኤያትን አድርገዋል ማለት ነው፤ እነዚህንም አራቱን ጉባኤያት ያካሔዱት ከአምስተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ዓመት ድረስ ነበር።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን መመሪያዋንና ሥርዓተ ትምህርቷን ካሳወቀችበት ከኢየሩሳሌም የሐዋርያት ሲኖዶስ ውሳኔ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ከዚያ ተያይዞ የመጣውን ትውፊት መሠረት አድርጋ እስካሁን ድረስ ባለማቋረጥ ሥራዋን ስታካሒድ ኖራለች፤ አሁንም በመሥራት ላይ ትገኛለች።

ትላንትናም፣ ዛሬም ያልተለወጠው፤ ነገም የማይለወጠው ሃይማኖታችን አንድ በመሆኑ የእግዚአብሔር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም አንዲት በመሆኗ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ኃይል፣ በቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያ ሰጭነት በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተማሪነትና አስተባባሪነት የሕዝበ ክርስቲያኑን አእምሮና ሥነ ልቡና በሃይማኖት አንድ አድርጋ እምነቷን ጠብቃ በመንፈሳዊውም ሆነ በማኅበራዊው አገልግሎት አሰጣጥ ታሪኳ በዓለም ዙሪያ በአድናቆት ሲነገር ይኖራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሦስት ዓመታት በኋላ፤ የሁለት ሺህ ዘመናት ዕድሜ ይኖራታል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ በነዚህ ዘመናት፤ በዚህ ረጅም የታሪክ ዘመኗ በየጊዜው የደረሰባትን ፈተና አልፋ ነው ከዚህ የደረሰችው።

- ቤተ ክርስቲያናችን በዮዲት - ጉዲት፤
- ቤተ ክርስቲያናችን በግራኝ መሐመድ፤
- ቤተ ክርስቲያናችን በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት፤
- ቤተ ክርስቲያናችን በቱርኮችና በግብፆች፤
- ቤተ ክርስቲያናችን በድርቡሾች፤
- ቤተ ክርስቲያናችን በፋሽስት ኢጣልያ
- ቤተ ክርስቲያናችን በደርግ የ17 ዓመታት ድንገተኛ፣ አደገኛና ሥር ነቀል ወታደራዊ አገዛዝ ያጋጠሟትን አስከፊና ከባድ ፈተናዎች በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ በቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን ሰማዕታት ተራዳኢነት አልፋ ከዚህ መድረሷ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ነው፤ እነዚያም ሁሉ የታሪክ አጋጣሚዎች መዘንጋት የለባቸውም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያውያን የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት ምልክት፣ ሐዋርያዊት ሁና እንደ ኖረች ሁሉ፤ ወደፊትም በነበረው ጸንታ እንድትኖር የሐዋርያነቱ፣ የክህነቱ አገልግሎት ከሕዝቡ የዕውቀት ዕድገት ደረጃ ቀድሞና ልቆ መታየት ይኖርበታል።

በዚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ እየተጠናና እየተመከረበት የሚወጣው ሕግና ደንብ ሁሉ ለእምነታችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ህልውና ዋስትናን የሚ ሰጥ ስለሆነ የሥርዓቱ ተከታዮች ሁሉ ለሕጉ ተገዢዎች መሆን ይጠበቅ ባቸዋል።

ስለዚህ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሃይማኖት፣ ሥነ ምግባር እንዲጸና ውሳኔ የሚሰጥበት በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የሐዋርያት ጉባኤ በመሆኑ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ተጠንቶና ተመክሮበት የሚወጣውን ውሳኔና የሚተላለፈውን መመሪያ ሁሉ በአጠቃላይም ዓላማና ተግባሩን በሥራ ለመተርጎም የሁሉንም ጥረት፣ ትጋትና ትብብር ይጠይቃል። ሁላችንም ከጊዜው ሁኔታ አንጻር ቤተ ክርስ ቲያናችን ከእኛ የምትሻውን መንፈ ሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በግንባር ቀደምትነት በአባትነት ደረጃ መፈጸምና ማስፈጸም ይጠበቅብናል። እንደ ዚሁ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ምእመናንና ምእመናት የአፈጻጸሙን ተግባር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በቤተ ክርስቲያናችን መዋቅር መሠረት፣ የሚፈለግባቸውን የሃይማኖት ግዴታ እንዲፈጽሙ ይህን መንፈሳዊ መልእክት እናስተላልፋለን።

*ከአባ ገሪማ*

*የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት*

*የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ*


ሐመር መጽሔት እና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን በተጨማሪም የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በጅምላ ለምትወስዱ

☞ መዘምር ቤቶች
☞ ሰንበት ትምህርት ቤቶች
☞ እንዲሁም ሌሎች

የዋጋ እና የጅምላ ሽያጭ ቁጥር ቅናሽ እናደርጋለን ይጎብኙን!!

ስልክ 23-45-29/23-45-30/22-86-01(09)64-27-28
E-mail MK_distribution@yahoo.com

# ቀደምቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዋፅዖ ዛሬም በዘመናዊ መልኩ

ባለፈው እትም የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልንና የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያንን የልማት እንቅስቃሴ መቃኘታችን ይታወሳል። ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ለሕዝብ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ ድረስ ሕንፃዎችን ገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን ተመልክተናል።

ትምህርት ቤት በመገንባት የመጀመሪያና ሁለተኛ የሆኑትን አርአያ በማድረግ ለትምህርት ቤትና ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ሕንፃዎችን በመገንባት ላይ ከሚገኙ አብያተ መካከል ክርስቲያናት የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንና የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤያት ተከታዩን ሥፍራ ይዘው እናገኛቸዋለን።



ታሪካዊው የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ እምብርት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለኦርቶዶክሳዊ ያው ምእመናንም ኾነ ለሌሎችም አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ሕንፃ በመገንባት ላይ ይገኛሉ። እኛም የልማቱን እንቅስቃሴ አስመልክተን የደብሩን የሰበካ ጉባኤ ሊቀ መንበርና የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳዳሪ አነጋግረናል።

«ትምህርት ቤት ለመገንባት ማንን አብነት አደረጋችሁ» ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄ ንቡረ እድ አባ ገ/ማርቆስ ሲመልሱ፦ «ትምህርት ቤት ለመገንባት አብነት የሆነን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አባታዊ መመሪያ ነው» ይላሉ። በአዲስ አበባም ሆነ በተለያዩ አህጉረ ስብከት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የራሳቸው የሆነ ት/ቤት እንዲኖራቸው የሰጡትን መመሪያ አብነት አድርገን ማኅበረ ካህናቱ ሰበካ ጉባኤው፣ የልማት ኮሚቴው፣ የኦርቶዶክሳዊው ምእመናን በደረጉት ትብብር ግንባታውን ለመጀመር ችለናል። ይሁንና ይላሉ ንብረ እድ አባ ገ/ማርቆስ የትምህርት ቤቱ ግንባታ ከተጀመረ ብዙ ወራት ቢቆጠሩም ግንባታው አልተጠናቀቀም ይኸውም ትልቁ ችግር የገንዘብ እጥረት እንደ ሆነ ንቡረ እድ ይገልጣሉ። አሁን ግን በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነትና በምእመናን ለጋሽነት የተወሰኑትን ለማጠናቀቅ ችለናል፤ የቀረንን ግንባታ ለማፋጠን የተጠናቀቁትን ዘጠኝ ክፍሎች አከራይተን መጠቀም ጨረታ አውጥተናል» ይላሉ። እንደ ንቡረ እድ አባ ገ/ማርቆስ አገላለጽ በዚህ ሥራ ላይ ምእመናን የተጠየቁትን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። ምእመናን ጥላ ሳናዞር ይረዱናል፤ ከጎናችን በመሆን አይዟችሁ ይሉናልና» በማለት የኦርቶዶክሳዊውን ምእመናን ቀና ትብብር ያደንቃሉ።

ሞያ ያላቸው የኦርቶዶክሳዊ ምእመናንን ተሳትፎ በሚመለከት ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ደግሞ፦ «የተለያየ ሞያ ያላቸው ሰዎች ቀርበው እንርዳችሁ ይሉናል፤ ነገር ግን እኛ ማንነታችሁን ማወቅ አለብን» በማለታችን የተደረገልን ሞያዊ እገዛ የለም፤ ምክንያቱም በደብሩ ሰበካ ጉባኤ ተቀጥሮ ደሞዝ የሚከፈለው መሐንዲስ አለን። ለመሐንዲስ ገንዘብ እየከፈልን ሌላ እገዛ የሚያደርግ ባለሞያ መፈለጉ አስፈላጊነቱ ጐልቶ ስላልታየን በዚህ በኩልርዱን ብለን ያቀረብነው ተማፅኖ የለም። ይሁንና ሁለት ባለሞያዎች የልማት ኮሚቴ አባላት በመሆን የሥራው እንቅስቃሴ በቅርበት እንደሚከታተሉ አስረድተውናል።


ትምህርት ቤት መገንባት የአገሪቱን የተማረ የሰው ኃይል በመጨመር ከፍተኛ ሚና አለው። ለአገር ዕድገት ጠቃሚ የሆነ ነገር በመሥራታችሁ በመንግሥት በኩል የተደረገላችሁ ትብብር አለ? ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄ ንቡረ እድ ሲመልሱ፦ «በመንግሥት በኩል ከግንባታው ባሻገር የተደረገልን ትብብር አለ፤ ይኸውም የተደፈነ የመቃብር ቦታ ነበር፤ ቦታው ለሰባት ዓመት በመደፈኑ የአካባቢውን ጽዳት በማጉደፍ ችግር ፈጥሮብን ነበር። ያንን መንግሥት በ500,000 ብር ቦታውን አጽድቶ፣ ሌላ የልማት ሥራ እንድንሠራበት ዲዛይን አውጥቶ ቅዱስነታቸውና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ባሉበት አስረክቦናል። በዚሁ አጋጣሚ ለተደረገልን ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን» በማለት ለተደረገላቸው ቀና ትብብር ምስጋና አቅርበዋል።

ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ተከልሎ የሚገኘውን ቦታ ለማስመለስ ያደረጋችሁት እንቅስቃሴ አለ? ስንል ላቀረብነው ጥያቄ ንቡረ እድ አባ ገ/ማርቆስ ሲመልሱ፦ ቦታው በመሠረቱ ቀደም ብሎ ክፍት እንደ ነበር ይጠቁማሉ። ክፍት በመሆኑ የመንደሩ ህፃናት ኳስ ይጫወቱበት ነበር። በአንድ ወቅት ሙስሊሞች መስጊድ ለመሥራት ሲንቀሳቀሱ በመስማታችን ለሚመለከታቸው አካላት ደብዳቤ ጽፈናል።

ምክንያቱም ቦታው ከዚህ በፊት የታቦተ ጊዮርጊስ ማርገጃ በመሆኑ እንዲሁም ቦታው ጥንተ ታሪክ ያለው በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኒቱ ቢሰጣት የልማት ሥራዎችን ለማከናወን ዝግጅቱም ብቃቱም ስላላት እንዲሰጠን ጠይቀናል። ይሁንና በደርግ ጊዜ ለሰባት ዓመት ያህል የመስቀል በዓልን አክብረንበታል ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ይገባል እንጂ ለሌላ አይገባም። ለቤተ ክርስቲያን ሊሰጣት ይገባል የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር። ይሁንና ላቀረቡት ጥያቄ መልስ አለማግኘታቸውን ንቡረ እድ ሳይጠቁሙ አላለፉም።



www.eotcmk.org



ሌላው ያነጋገርናቸው የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ ፀሐይ አባ ወልደ ትንሣኤ ናቸው። እርሳቸውም በበኩላቸው ለትምህርት ቤትና ለተለያዩ የአገልግሎት ሊውል የሚችል ሕንፃ መገንባታቸውን ጠቁመውናል። እንደ አስተዳዳሪው ገለጻ ሥራቸው የተጠናቀቀውን ለቢሮና ለሱቅ አገልገሎት መከራየታቸውን ገልጸው በሚገኘው ገቢ ደግሞ ቀሪ የግንባታ ሥራዎችን እንደሚያፋጥኑ ገልጸውልናል።

እኛም ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ በልማት ላይ ከተረባረበች የሚጠበቀው ውጤት ምንድን ነው? ስንል ላቀረብነው ጥያቄ አስተዳዳሪው ሲመልሱ፦ « ከእንግዲህ በየክብረ በዓሉ ዥንጥላ መዘቅዘቅ ይቀራል። ለቤተ ክርስቲያን፦ ልጆችም የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤ ድህነት በእግዚአብሔር አጋዥነት በእኛ ጥረት ይጠፋል» በማለት ያላቸውን እምነት ገልጸውልናል።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በገነባችው ት/ቤት የሥነ ምግባር ትምህርት ይሰጡ እንደ ኾነ የተጠየቁት አስተዳዳሪው ሲመልሱ፦ የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋ ማፍራት ነው። ስለሆነም ለወደፊቱ በሥርዓቱ ትምህርት የሥነ ምግባር ጉዳይን ለማካተት ዕቅድ መኖሩን እንዳላቸው ገልጸውልናል።

በመጨረሻም ያቀናነው ለብዙዎች አብነት ወደ ሆነው የምስካየ ኅዙናን የመድኃኔ ዓለም ገዳም ነበር። የገዳሙ አስተዳዳሪ መምህር ጥዑመ ልሳን የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ዘመናዊ ትምህርት ቤት በትምህርት አሰጣጡ ተመራጭ ትምህርት ቤት መሆኑን ገልጸውልናል። ምክንያቱም ሲያብራሩ፦ የምስካየ ኅዙናን ገዳም በሥርዓተ ትምህርቱ የሥነ ምግባር ትምህርት ቀረጻን ያስተምራል። ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን ላላቸውና የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ ማወቅ ለሚፈልጉ ተማሪዎችም የግእዝ ትምህርት ስለሚሰጥ ትምህርት ቤቱ ተወዳጅ ሊሆን እንደ ቻለ መምህር ጥዑመ ልሳን ሳይጠቁሙ አላለፉም።

በቅርቡም የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ለመክፈት የተለያዩ ግንባታዎችን በማካሄድ ላይ እንደ ሚገኝ ገልጸውልናል። ለዚህም ሕንፃ ማስፈጸሚያና ለገዳሙ በውጪ አገር የሚገኙ ምእመናንና በጎ አድራጊዎች ርዳታ እንደ ሚያደርጉላቸው መምህር ጥዑመ ልሳን ይናገራሉ። በዚሁ አጋጣሚ የተጀመረውና የታቀደው ሁሉ ከፍጻሜ እንዲደርስ ምእመናን በገንዘብ፣ በጉልበትና በአሳብ የበኩላቸውን ትብብር እንዲያደርጉ የገዳሙ አስተዳዳሪ ጥሪ አቅርበዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚከናወነው የልማት እንቅስቃሴ ይልቁንም በትምህርት ዙሪያ እየተደረገ ያለው ሥራ ይበል የሚያሰኝ ነው። ከአዲስ አበባ ውጪ የሚገኙ አህጉረ ስብከት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈጽሙ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

አሁን ተሠርተው አገልግሎት በማበርከት ላይ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናትም የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ከመጠበቅ በተጨማሪ ለሚከተሉት ነገሮች ትኩረት ስጥተው ቢሠሩ መልካም ነው እንላለን።

1ኛ. *የግእዝ ቋንቋ ትምህርት መስጠት*፦ የግእዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ መግባቢያ መሆኑ ከተቋረጠ ረዥም ዘመን አስቆጥሯል። ቋንቋው በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ የምንፈጽምበት÷ የምስጋና መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት ከመሆኑም በተጨማሪ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የሕክምናና የመሳሰሉት ጉዳዮች የተጻፈበት ቋንቋ በመሆኑ ትውልዱ እንዲያውቀው የማድረግ ሓላፊነት ቤተ ክርስቲያን አለባት። በኢትዮጵያ ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ግእዝ እንደ አንድ ትምህርት ሲሰጥ ቢቆይም፦ «ፈተናውን የሚወስድ ግእዝ ዐዋቂ የለም፤ ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት አይሰጥም» በሚል ከፈተናዎቹ ውስጥ እንደ አንዱ መቆጠሩ ቀርቶ በአሁኑ ሰዓት ተሰርዟል። ይህን በትውልዱ እና በቋንቋው መካከል ያለውን መራራቅ የበለጠ የሚያሰፋው በመሆኑ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት ቋንቋው ዳግም ወደቆየበት የብሔራዊ ፈተና የትምህርት ዓይነትነቱ እንዲመለስ ማድረግ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል።

2ኛ. *የሥነ ምግባር ትምህርት ተጠናክሮ እንዲሰጥ ማድረግ*፦ ለአንድ ሀገር ዕድገትና ሰላም የዜጐች በሥነ ምግባር መታነጽ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። በዕውቀት ጐልብቶ አዲስ ግኝት በመፍጠር ሀገርን ማሳደግ የሚቻለው ሥነ ምግባሩ ያማረ ትውልድ ሲኖር ብቻ ነው።

ፍርድ እንዳይዛባ፣ እርስ በእርስ መበዳዳል እንዳይኖር በጠቅላላው ሙስና እንዳይንሰራፋ ማድረግ የሚቻለው ትውልድን ከሥር ጀምሮ በሥነ ምግባር ኮትኩቶ በማሳደግ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ባላት መድረክ ይልቁንም በየትምህርት ቤቶቿ በተጠናከረ መልኩ የሥነ ምግባር ትምህርት ብትሰጥ የእርስ በእርስ መዋደድ፣ መከባበር፣ ታማኝ መሆን የዜጐች መለያ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መንግሥትም ሕገ ወጥ የሆነውን በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም ለመቆጣጠር የፀረ ሙስና ኮሚሽን ባላቋቋመ ነበር።

«እንግዳ ተቀባይ÷ ሰው አክባሪ ሕዝብ አላት» ተብላ የሚነገርላት ሀገራችን ኢትዮጵያ ይህ ተወዳጁ ባሕሏ ተጠብቆ ሕዝቦቿ የራሳቸውን ባሕል የሚወዱ በታሪካቸው የማያፍሩ ብሎም «ትላንት አባቶቻችን ምን አቆዩን? ዛሬ እኛ ምን መሥራት ይጠበቅብናል» በማለት ለትውልድ የሚበጅ ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ የሚቻለው በየትምህርት ቤቶች እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት የሥነ ምግባር ትምህርት መስጠት ሲቻል ብቻ ነው።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

ዲ/ን ደሳለኝ ቀለብ

ማስታወሻ፡- በግእዝ የሐላፊ ግሶች ቅጥያዎች አንድ ዓይነት ናቸው:: የግሱ የመጨረሻ ፊደል ቀ፣ ገ፣ በ፣ ገ ከሆነው ውጭ በእንግሊዝኛው ግን ሕጋውያን ግሶች ed /በቀዳማይ- ጊ ዜ ሲጨምሩ/ በኢሕጋውያን ግሶች ጊዜ ግን የተለያየ አካሄድ አላቸው:: በግእዝ ቋንቋ በካልአይ ጊዜ በየቤቱ ይረባል:: ይቀጥላል::

make-made
work-worked
ገብረ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | ገበርኩ | ሠራሁ | I worked /made/ |
| አንተ | ገበርከ | ሠራህ | You worked /made/ |
| አንቲ | ገበርኪ | ሠራሽ | You worked / made/ |
| አንትሙ | ገበርክሙ | ሠራችሁ | You worked /made/ |
| አንትን | ገበርክን | ሠራችሁ | You worked /made/ |
| ንሐነ | ገበርነ | ሠራን | We worked/made/ |
| ውእቱ | ገብረ | ሠራ | He worked/made/ |
| ይእቲ | ገብረት | ሠራች | She worked/made/ |
| ውእቶሙ | ገብሩ | ሠሩ | They worked/made/ |
| ውእቶን | ገብራ | ሠሩ | They worked/made/ |

ለዋጭ ፊደላቱ ገብረ - ሠራ - **worked**

| | ግእዝ | አማርኛ | እንግሊዝኛ |
|---|---|---|---|
| /ልሳን እንግልጣር/ | | | |
| አነ | ኩ | ሁ | ed |
| አንተ | ከ | ህ | ed |
| አንቲ | ኪ | ሽ | ed |
| አንትሙ | ክሙ | ችሁ | ed |
| አንትን | ክን | | |
| ንሕነ | ነ | ን | ed |
| ውእቱ | - | - | |
| ይእቲ | ት | ች | ed |
| ውእቶሙ | ኡ /አናባቢ/ | ኡ/አናባቢ/ | ed |
| ውእቶሙ | ን /አናባቢ/ | ኡ/አናባቢ/ | ed |

ሐ. ሖረ - ሄደ

ሐዊር/ሐዊርተ - መሄድ

ሖረ/ሄደ - ባለሁለት ፊደላት ግስ ነው::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አነ | ሖርኩ | እኔ | ሔድኩ | I went |
| አንተ | ሖርከ | አንተ | ሔድክ | You went |
| አንቲ | ሖርኪ | አንቺ | ሔድሽ | You went |
| አንትሙ | ሖርክሙ | እናንተ | ሔዳችሁ | You went |
| አንትን | ሖርክን | እናንተ | ሔዳችሁ | You went |
| ንሕነ | ሖርነ | እኛ | ሔድን | We went |
| ውእቱ | ሖረ | እሱ | ሔደ | He went |
| ይእቲ | ሖረት | እሷ | ሔደች | She went |
| ውእቆሙ | ሖሩ | እነሱ | ሔዱ | They went |
| ወእቆን | ሖራ | እነሱ | ሔዱ | They went |

ማስታወሻ፡- በውእቱ እና በይእቲ ጊዜ በግእዝ ሖረ የሚለው ፊደል በግእዝ ይነገራል:: በውእቶሙ እና በውእቶን ደግሞ የመጨረሻ ፊደሉ ረ በውእቶሙ ወደ ካዕብ እና በውእቶን ወደ ራብዕ በአናባቢዎች ብቻ ቅርጹን ይለውጣል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ቅጥያ የለም:: ከዚህ ውጭ በአነ፣ አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን፣ ንሕነ የግሱ የመጨረሻ ፊደል የግድ ወደ ሳድስ መለወጥ ይኖርበታል:: እዚህ ላሁን የእንግሊዝኛው ኃላፊ ግሱን goን went ይላል:: በኃላፊ ጊዜ:: በግእዝና በአማርኛ ባለቤቱ በግሱ ይታወቃል:: «እኔ ሔድኩ» በማለት ፋንታ «ሔድኩ» ቢል በቂ ነው:: እኔ የሚለው ባለቤት በውስጠ ተዐውቆ አለና:: በእንግሊዝኛው ግን የግድ ባለቤቱ መገለጥ አለበት::

መ. የኃላፊ ኢሕጋውያን በቀ፣ ገ፣ ስ፣ ነ የማጨርሱ ግሶች ናቸው:: ምሳሌ

ባረከ - አመሰገነ፣ ባረከ /blessed

ባርኮ /ባርኮት - ማመስገን To bless

| | | |
|---|---|---|
| አነ | ባረኩ | I blessed |
| አንተ | ባረከ | You blessed |
| አንቲ | ባረኪ | You blessed |
| አንትሙ | ባረክሙ | You blessed |
| አንትን | ባረክን | You blessed |
| ንሐን | ባረክነ | We blessed |
| ውእቱ | ባረከ | He blessed |
| ይእቲ | ባረከት | She blessed |
| ወእቶሙ | ባረኩ | They blessed |
| ውእቶን | ባረካ | They blessed |

በአምስቱ መራሕያን

አነ ባረክኩ ሳይሆን አነ ባረኩ
አንተ ባረክከ ሳይሆን አንተ ባረከ
አንቲ ባረክኪ ሳይሆን አንተ ባረኪ /ሲነበብ/
አንትሙ ባረክክሙ ሳይሆን አንትሙ ባረክሙ /
አንትን ባረክክን ሳይሆን አንትን ባረክን ይባላል:: ስለሆነም ኩ፣ ከ፣ ኪ፣ ክ ጠብቀው ይነበባሉ:: እንደዚሁ ኹሉ የግስ የመጨረሻ ፊደላት ቀ፣ ገ፣ ከ ሲሆኑ ጠብቀው ይነበቡ:: «ነ» ከሆነ ደግሞ በንሕነ ጊዜ ጠብቆ ማንበብ::

ኮነ ሆነ /Become - ኮነ የሚሰብ ግስ /ገቢር/ ነው::

አነ ኮንኩ ሐኪመ I be come a doctor
አንተ ኮንኮ ሐኪመ You become a doctor
አንቲ ኮንከ ሐኪሚተ You become a doctor
ንሕ ነኮ ነ ከመ አባግዕ እንደ በጐች ሆን::

አጥመቀ
አክለነ
ሰበከ
ባረከ

ሖነ እነዚህን የመሰሉ ግሶች የኃላፊ አንቀጽ ኢ ሕጋውያን ናቸው::

ሠ. አእመረ - አወቀ – knew

To know /knewing

አእመረ - ባለ አራት ቀለማት ግስ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| አነ | አእመርኩ<br>አወቅኩ | I knew |
| አንተ | አእመርከ<br>አወቅክ | You knew |
| አንተ | አእመርኪ<br>አወክሽ | You knew |
| አንትሙ | አእመርክሙ You knew | አወቃችሁ |
| አንትን | አእመርክን<br>አወቃችሁ | You knew |
| ንሐነ | አእመርነ<br>አወቅን | We knew |
| ውእቱ | አእመረ<br>አወቀ | He knew |
| ይእቲ | አእመረት<br>አወቀች | She knew |
| ውእቶሙ | አእመሩ<br>አወቁ | They knew |
| ውእቶን | አእመራ<br>አወቁ | They knew |

ረ. ይቤ፡- በግእዝ ለየት ያለ ግስ በኃላፊም በካልአይም የራሱ አካሄድ ያለው ኢ ሕጋዊ ግስ ይቤ አለ ነው:: የይቤን



www.eotcmk.org

ዝርዝር በሌላ ጊዜ የምናየው ሲሆን ላሁኑ በኃላፊ ጊዜ እንዴት እንደተለየ እናስተውል:: ይቤ ለየት ያለበት የሚጀምረው በሳድስ ሲሆን የሚጨርሰው በኃምስ ስለሆነ ነው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| አን | እቤ | አልኩ | I said |
| አንተ | ትቤ | አልክ | You said |
| አንቲ | ትቤሊ | አልሽ | You said |
| አንትሙ | ትቤሉ | አላችሁ | You said |
| አንትን | ትቤለክን | አላችሁ | You said |
| ንሕን | ንቤ | አልን | We said |
| ውእቱ | ይቤ | አለ | He said |
| ውእቲ | ትቤ | አላት | She said |
| ውአቶሙ | ይቤሉ | አሉ | They said |
| ውእቶን | ይቤላ | አሉ | They said |

<u>ምልምድ</u>

የሚከተሉትን ግሶች ወደ ካልአይና ወደ ዘንድ ለውጥ

ምሳሌ ወደሰአመሰገነ /የጠበቀ ነው/

ይዌድስ ያመሰግናል

ይወድስ ያመሰግን /ያመሰግን ዘንድ:: ቤቱ ቀደሰ ነው

የጠበቀ ምልክቱ /•/ ነው

| | ካልአይ | ዘንድ | ቤቱ |
|---|---|---|---|
| 1. ዘመረ | ______ | ______ | ______ |
| 2. ነጸረ | ______ | ______ | ______ |
| 3. ወፅአ | ______ | ______ | ______ |
| 4. ቀደመ | ______ | ______ | ______ |
| 5. ጌሠ | ______ | ______ | ______ |
| 6. ጸመ | ______ | ______ | ______ |
| 7. ረከበ | ______ | ______ | ______ |
| 8. ኖመ | ______ | ______ | ______ |
| 9. ኮነ | ______ | ______ | ______ |
| 10. ሰምዐ | ______ | ______ | ______ |
| 11. ተንበለ | ______ | ______ | ______ |
| 12. ከሰበበ | ______ | ______ | ______ |

*ይቀጥላል*

# ዜና ልሳነ ግእዝ
## የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር ተመሠረተ

ባሳለፍነው ሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመሥርቷል:: ማኅበሩ ከ200 በላይ አባላት ሲኖሩት÷ አባልነቱ ተማሪዎችንና መምህራንን ያካተተ ነው:: ማኅበሩ ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሣው አባላቱ በግእዝ ቋንቋ ማንበብ፣ መጻፍና መናገር ይችሉ ዘንድ ነው:: በቀጣይነትም በዚህ ቋንቋ የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍትን በመመርመር ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲደርስ ማድረግ ዋነኛ ግቡ ነው::

የማኅበሩ ሰብሳቢና በአ.አ.ዩ የሥነ ልሳን /Philology/ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ ተማሪ የኾኑት መምህር ደሳለኝ ቀለብ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኰሌጅ መምህር ናቸው:: መ/ር ደሳለኝ ስለ ማኅበሩ አመሠራረት ሲያብራሩ «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ክበብ» በሚል እንደ ተጀመረ ገልጸዋል:: አክለውም «የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክና ቅርስ በግእዝ ቋንቋ በብራና ላይ በተጻፉ የጥበብ፣ የሃይማኖት፣ የፍልስፍና፣ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ መጻሕፍት ውስጥ ተካብተው ይገኛሉ:: ይህን ጥንታዊ ቋንቋ አሁን ብንመረምረው በዚህ ዘመን አስተሳሰባችን ላይ ማለፊያ ግንባታንና ድንቅ መሠረትን መተው ስለምንችል የቀደመ ማንነታችንን መፈለግ ጀመርን:: ፊደሎቻችንን፣ ቋንቋችንን በአጠቃላይ ግእዙን የኋሊት ተጉዘን ብንመረምረው ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካችን ኩራት ነው የሚኾነው::» ብለዋል::

አያይዘውም:- «ግእዝ አቅፎ የያዛቸው በርካታ ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጽሑፎች በጋራ የመፈተሽና ለብሔራዊም ሆነ ለሌሎች አገር አቀፍ ቋንቋዎቻችን የዕውቀት ግብዓት ማቅረብ አንዱ ዓላማ ነው:: ያንን ለማድረግ አባሎቻችን የግእዝ ቋንቋን መናገር÷ መጻፍና የመመርመር አቅሙ እንዲኖራቸው እናደርጋለን::» በማለት የማኅበሩን ዓላማ አስረድተዋል:: ግእዝ በአያሌ ሰዎች ዘንድ ሃይማኖታዊ ቋንቋ ብቻ ተደርጐ መወሰዱ ትክክል አለመሆኑን የሚገልጹት መምህር ደሳለኝ ቋንቋው ዘርፈ ብዙ ዕውቀት በመያዙ የማኅበሩ አባላት የገበዩትን ዕውቅት ለሌሎች እንዲያካፍሉ ማድረግ ሌላው ትልማቸው መሆኑን ገልጸዋል:: ስለዚህም ሲያብራሩ:- «ይህን ዕውቀት በመላ አገራችን ለማስፋፋት አባሎቻችንን በአገር ዓቀፍ ደረጃ እንዲሰባሰቡ እናደርጋለን:: ደብዳቤዎችን የመለዋወጡ፣ በራሪ ወረቀቶችን የማዘጋጀቱና መጻሕፍትን በዚሁ ልሳን አዘጋጅቶ ብዙኀኑ ሐሳቡን እንዲለዋወጡበት ማድረጉ ታላቁ ትልማችን ነው:: ትምህርቱን በሚቀጥለው ዓመት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመመካከር መስጠት እንጀምራለን:: መጀመሪያ ለአባሎቻችን ትኩረት የምናደርግ ቢሆንም፤ በሂደት ሁሉም የቋንቋው አፍቃሪ እንዲገበይ እንጥራለን:: በአሁኑ ጊዜ ከ200 በላይ ተማሪዎችና ታላላቅ የዩኒቨርሲቲው መምህራን በማኅበሩ አባልነት ታቅፈዋል:: በእምነት ደረጃ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ የእስልምና፣ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የማኅበራችን አባላት ናቸው::» መግለጫቸው ሲያጠቃል ሉም:-

«በሂደት በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር እንዲሁም ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ከማኅበረ ቅዱሳንና በዚህ ረገድ ሊያግዙን ከሚችሉ አካሎች ጋር ሁሉ መልካም ግንኙነት ይኖረናል» ሲሉ የተናገሩት መ/ር ደሳለኝ ቀለብ:- «መጪው ትውልድ አንድ እርምጃ ወደፊት ለመሄድ በሚያደርገው ጥረት ተቋማቱ ያላቸውን በመስጠት እንደ ሚተባበሩን እምነታችን ነው» በማለት ቀጣይ ተስፋቸውን ገልጸዋል::

*<u>ከአዘጋጁ</u>:- የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤን በጉዳዩ ዙሪያ ተከታታይ ጽሑፎችን ማስነበቡ ይታወሳል:: ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የአንባብያንን አስተያየት መሠረት ባደረገ መልኩ ባካሄደው ጥናት «አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» የተሰኘ ዓምድ መክፈቱ ይታወቃል:: «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» በሚል ስያሜ በ1997 ዓ.ም ሚያዝያ ወር የተመሠረተው ማኅበር ሰብሳቢ መምህር ደሳለኝ ቀለብ በዓምዱ ዝግጅት ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: በመኾኑም ምእመናን የማኅበሩ አባላት በመሆን ለክቡር ዓላማው መሳካት የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ዝግጅት ክፍላችን መልእክቱን ያስተላልፋል:: ከማኅበሩ ጋር ለመገናኘት ለምትሹ:- የልሳነ ግዕዝ አፍቃሪዎች በሙሉ የሚከተለውን አድራሻ መጠቀም የምትችሉ መኾኑን እንገልጻለን::*

<u>አድራሻ:-</u>

ስልክ:- 251-01- 55 63 28

ኢ-ሜይል:- geezaau@ yahoo.Co.Uk

የመ.ሣ.ቁ:- 150141 አ.አ.ዩ

ገለታ ማርያም
/ውዳሴ ማርያም/
**Galata Maariyaam**
በኦሮምኛ
በድጋሚ ታትሞ
በሥርጭት ላይ ውሏል !!



www.eotcmk.org

# መንገደኛው

እግዚአብሔር ይመስገን ለዛሬ ደርሻለሁ:: ዝናሙ ብርዱ በእኔ አቆጣጠር ቀደም ብሎ ቢጀምርም ተስማምቶኛል:: ክረምቱ ብቻ አይደለም የተስማማኝ፤ የዘመነ ፋሲካ መፈጸምም እንጂ:: ዘመነ ፋሲካ ሲመጣ ይጨንቀኛል:: ለምን በሉኝና ልንገራችሁ::

ጠዋት ቁርስ፣ አራት ሰዓት ሲሆን ሻይ፣ ስድስት ሰዓት ምሳ፣ ዘጠኝ ሰዓት ሻይ፣ ዐሥራ አንድ ሰዓት መክሰስ፣ ማታ እራት:: እነዚህ የዘመነ ፋሲካ የመብል መርሐ ግብራት ናቸው:: ኀምሳ አምስት ቀን የጾምነውን ማካካሻ ይመስላል:: ሌላም አለ:: ማክሰኞ ሰርግ፣ ኀሙስ ሰርግ፣ ቅዳሜና እሑድ ሰርግ፤ ሰኞ መልስ፣ ማክሰኞ መልስ ኀሙስ ቅልቅል:- /ሰዎቹ በጋብቻ ቢቀላቀሉም/ የወንድም፣ የእኅት፣ የአኅት፣ የአክስት፣ የአያት... የአብሮ አደግ፣ የሥራ ባልደረባ ጥሪ ተጋቢዎችን:: ሙሽሮች በየተጠሩበት ቦታ ሲሆን ሲሆን ሙክት፣ በግና ውስኪ፣ ካልሆነም ውስኪ እርሱም ካልተቻለ ድፎ ዳቦ ከብሔራዊ የአልኮልና የአረቄ ፋብሪካ ምርቶች መካከል አንዱን ገዝቶ መሄድ የሰርግ «ሥነ ምግባር» ነው::

ታድያ በመንገድ ያዩኝ ሰዎች ሁሉ በጋብቻቸው ሰሞን ይጠሩኛል:: እኔ መንገደኛው መንገዱን ማን ይሂድለት ብለው ነው:: ለፋሲካ ሰሞን የምግብ መርሐ ግብራት የሥራ ሰዓቴን ማቃጠሌ ሳያንስ በየሰርጉ ሰበብ ጊዜዬን መጨረሴ ይገርመኛል::

ኢትዮጵያ ድኻ ናት ይባላል:: ለመንገደኛው ግን:- «አገሪቱ እንጂ ሰዎቹ ድሆች ናቸው::» የሚለው ነገር አይስማማውም:: ምሳ በልቶ እራት መድገም የሚያቅተው ስንት ኢትዮጵያዊ እያለ እንዳትሉ:: መንገደኛው በዚያ ማእዘን አይደለም ያየው:: ከሰርግ ድግስ አንጻር እንጂ የመንገደኛው ጓደኛ ነው:: አሁን ለታ ሥርዓተ ጋብቻውን በቤተ ክርስቲያን ፈጽሟል:: መንገደኛው በመንገድ አገኘውና ጠየቀው:: «ስንት አወጣህ?» «ትንሽ ናት::» «ምን ያህል?» «አሥራ ሰባት ሺህ ብር!!» መንገደኛው አንድ ነገር ትዝ አለው::

ሁለት ዘመዳሞች ይገናኙና ስለ ገንዘብ ያወራሉ:: አንደኛው «አንድ ሺ ብር ምን አላት÷ ትንሽ ናት» ይላል:: ዘመድየው በመገረም «በእናንተ ዘንድ አንድ ሺ ብር ሴት ናት ወይ? እኛስ ዐሥሩንም ብር አንቱ ነው የምንለው» አለው:: ዐሥራ ሰባት ሺ ብር ትንሽ ናት ሲባል ይገርማል:: «ግን እኮ መቶ ሺ÷ ሁለት መቶ ሺ በሚያወጡ÷ በታላላቅና ውድ ሆቴሎች የሚደግሱ አሉ::» እንዳትሉኝ:: እነርሱና መንገደኛው ከነ መኖራቸውም አይተዋወቁም:: የሚገርመው በየወሩ ሁለት መቶና ሦስት መቶ ብር የቤት ኪራይ መክፈል የሰለቻቸው ለሰርግ ግን ኻያ÷ ሠላሳና አርባ... ሺ ሲያወጡ ነው::

የሚያገባት ሳይሆን የሚገዛት የሚመስል አግቢታም አለ:: ሽማግሌ ሲላክ ቪዲዮ፣ ለቀለበት ቪዲዮ፣ ጥሎሽ ሲላክ ቪዲዮ፣ ለጋብቻው ዕለት ቪዲዮ፣ ለመልስ ቪዲዮ፣ ለቅልቅል ቪዲዮ፣ ልጅ ሲወለድ ቪዲዮ፣ ለክርስትና ቪዲዮ፤ ቪዲዮው ባለበት ሁሉ ፎቶ ግራፍ መኖሩንም አትርሱ:: አንድ የመንገደኛው ጓደኛ ለሰርጉ የተነሡት ፎቶ 20 ፊልም ነበር:: ሒሳቡን አስሉት:: ቪዲዮው «እንዲህ ነበር» ብሎ ታሪክ ማጉላቱ÷ ማውሳቱ ጥሩ ቢሆንም እንደ አክሱም ሐውልት አለያም እንደ ቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የጎላ ታሪክ ይዞ በትዝታ ብቻ መቅረቱ ያሳዝናል:: ልጆቻቸው እናትና አባታቸው የተጋቡ ዕለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ሲቆርቡ ከማየት በቀር በአካል ሲቆርቡ አያይዋቸውም ይባላል:: ጉድ ነው:: የአማርኛው::

የሚገዛት የሚመስል አግቢታ ያልኳችሁ ደግሞ ለሙሽሪት «ክብር» ሲባል ለልብሷ፣ ለጌጧ ዐሥር ሺ ብር ያወጣውን ነው:: ምናልባት ሰው ለወደደው እንዳትሉ መንገደኛው ፍቅር እንዲሁ መውደድ÷ ልባዊ አክብሮትን መስጠትና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማሟላት እንጂ አፍአዊ በሆነ ጌጥ የወደዷትን በማዥጎርጎር አያምንም::

እናንተ÷ ዕድሜ ልኩን ከገንዳ የተጣለ ትራፊ እንጀራ እየለቀመ የሚኖር፣ የላስቲክ መጠለያ እንደ ፎቅ የተወደደበት፣ በሬ መግዣ አጥቶ ከአንድ በሬ ጋር በቀንበር ተጠምዶ ደረቅና ድንጋያማ መሬት ለማረስ የሚጥር ዜጋ ባለበት አገር ለአንድ ቀን ድግስ ኻያ ሺ÷ ሠላሳ ሺ ለሰርግ ማውጣት ኃጢአት አይሆንምን?


መቼም የሰርግ ነገር ከተነሣ ሌላም ልንገራችሁ:: መንገደኛው ሰርግ ይወዳል:: በተለይም በተክሊል ሰዎች ሲጋቡ ማየትን:: ሰው እንዳይሰማን ቀስ ብለን እናውራና÷ «በ1996 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት ከተጋቡት ሰባት ሺህ ሰዎች መካከል ከሦስት ሺህ በላይ የሆኑቱ ተፋተዋል» አሉ:: ያጋባችሁ÷ ጆሮአችሁን ያዙ÷ «አውጣን÷ አውጣን» በሉ:: ያላገባችሁ:- «ምን ይሆን ምክንያቱ?» ስትሉ ተጠያየቁ::

ዉይ ረስቼው÷ ለካ ሌላ ልንገራችሁ ብዬ ነበር:: ይኸውላችሁ ሁለት ሰርግ ላይ መንገደኛው እኔ ያየሁትን ልንገራችሁ:: ተጋቢዎቹ ቪዲዮ ቀራጭ በገንዘብ ተዋውለው ያመጣሉ:: ሥራውን ጀምሯል:: ሙሽራው ክብርት ሙሽሪትን ይዞ በሚዜዎቹ ታጅቦ ቤተ ክርስቲያን ደረሱ:: ወደ ውስጥ ሊገቡ ነው:: ቪዲዮ ቀራጩ ይቀርፃል:: ከነጫማው ቤተ ክርስቲያን ሊገባ! ዲያቆኑ ልጁ የዘነጋው መስሎት «ጫማህን አውልቅ» ይለዋል:: ቪዲዮ ቀራጩ «አላወልቅም:: ለምን? አላምንበትም:: ኢ-አማኒ ከሆንክማ ቤተ ክርስቲያን አትገባም::» ክርክር ግጭት:: ሙሽሮቹ ድንግጥ:: ጠላታቸው ሰይጣን ይደንግጥና:: ነገሩ ሲጣራ ቪዲዮ ቀራጩ መናፍቅ ኖሯል:: አይ መንገደኛው! ሌላውም የእስልምና እምነት ተከታዩን ቪዲዮ ቀራጭ ይዋዋልና ያመጣል:: ... መቼም ሰው አይጠፋ ነገሩ በአጭሩ ተስተካከለ::

ይህ ሁሉ የዘመነ ፋሲካ የመንገደኛው የሰርግ ትውስታ ነው:: እናንተስ ያያችሁት የለም? መቼም በተክሊል በቁርባን ጋብቻቸውን በፈጸሙበት ዕለት «የሙሽራ ወግ አድርሱ» የተባሉ ሰዎች አላጋጠሟችሁ ይሆናል:: ሰውረን በሉ:: ዘመነ ፋሲካ አልፎ ዘመነ ጰራቅሊጦስ ደግሞም ዘመነ ክረምት ተተክቷል:: ዘመነ መርዓዊ /ወርኀ ጥር/ ዘመነ ፋሲካም ዞረው ይመጣሉ:: የእርስዎስ ሰርግ እንዴት ይሆን? ኀምሳ አምስት ቀን ከጾሙስ በኋላ በዘመነ ፋሲካ ጾም የለም ብለው ጊዜዎትን ሁሉ የመመገቢያ ያደርጉት ወይስ በመጠን ይሆኑ? ይብቃኝ:: ክረምቱን አልሄድም:: ሰሚ ነው የምሆነው:: እርስዎስ እንደ ዘመሚት ወይስ እንደ ተርብ ይሆኑ ይሆን?

'







እነዚህንና ሌሎች መንፈሳዊ ፖስተሮችን
በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ
ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል

## የማኅበረ ቅዱሳን መዝሙር ቁጥር ፮
## በሥርጭት ላይ ውሏል!




# አስደሳች ዜና ለምእመናን

ቅዱስ ሉቃስ የሣለውና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የጠበቀው
ጥንታዊው የእመቤታችን ሥዕል ታትሞ ቀረበላችሁ።



የሥዕሉ መጠን:-
30 ሣ. ሜ x 42 ሣ. ሜ


አከፋፋይ:-
ዲ/ን ወንድወሰን ሶርሣ
ስልክ:- (09) 65 17 46

የሥዕሉ ዋጋ ብር 4.00


ሥዕሉን:-

- በማኅበረ ቅዱሳን ማከፋፈያዎች
- በቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኙ የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ መደብሮች
- በሌሎችም መዝሙር ቤቶች ውስጥ ያገኙታል።


# ዜና መጻሕፍት




አዘጋጅ:- ያዕቆብ ሰንደቁ




አዘጋጅ:- አቡነ ሺኖዳ
ትርጉም:- አያሌው ዘኢየሱስ




አዘጋጅ:- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ
ትርጉም:- አያሌው ዘኢየሱስ

መጻሕፍቱን በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ
ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል
ወይም 09-63 63 93 ✉ 20 04 38 ይደውሉ
E:mail:yyakob zz @yahoo.com P.O. Box 1243 ይጻፉ

ዋጋ ብር 3.50

©

!" #$ %

& ' ( ) * $++